

«የቅራኔውን እርሻ የሚያርሱት ምሁራኑ ናቸው»

- አቶ ማሞ አፈታ
የቀድሞ ሰራዊት አባልና ደራሲ

ገጽ 6

ንቁ አእምሮ፤ ለሥራ የተጉ እጆች ለውጤት ያበቃሉ

ገጽ 13


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

81ኛ ዓመት ቁጥር 218 ሚያዝያ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## «ሠራዊቱ የኢትዮጵያ የመጨረሻ ምሽግ እንጂ ከፓርቲ ጋር የሚጣበቅ አይደለም»



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-የአገር መከላከያ ሠራዊት የኢትዮጵያ የመጨረሻ ምሽግ እንጂ ከፓርቲ ጋር የሚጣበቅ መሆን የለበትም ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ለመከላከያ ከፍተኛ መኮንኖችና ለደህንነት ተቋማት አመራሮች አገራዊ፣ ቀጠናዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ ገለጻ ሰጥተዋል። በወቅቱ እንደተናገሩት፤የአገር መከላከያ

«ሠራዊቱ የኢትዮጵያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## ሕዝቡን የሚያጋጩ ልሂቃን ከጥፋት ጎዳናቸው ሲመለሱ እንደሚገባ ተጠቆመ

- አቶ ማሞ አፈታ የቀድሞው ሠራዊት አባልና ደራሲ

**ማህሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- በአገሪቱ ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ከተፈለገ ጎራ ፈጥረው ሕዝቡን የሚያጋጩ ልሂቃን ከጥፋት ጎዳናቸው ሊመለሱ እንደሚገባ የቀድሞ ሠራዊት አባልና ደራሲ አቶ ማሞ አፈታ አስታወቁ።

አቶ ማሞ አፈታ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ለሚስተዋሉ አብዛኞቹ ግጭቶች መነሻ የተማረው የኅብረተሰብ ክፍል በሚያዛምተው ሐሰተኛ ወሬና ቅስቀሳ መሆኑን ገልጸዋል። ምሑራኑ በኅብረተሰቡ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት በመጠቀም ለራሳቸው የሚጠቅማቸውን የግጭት አጀንዳ እየፈጠሩ ለዘመናት ተከባብሮና ተቻችሎ የኖረውን ማኅበረሰብ እያቃረኑ ነው የኖሩት። በመሆኑም ትክክለኛ እና ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ልሂቃኑ ከዚህ ተግባራቸው መታቀብ ይገባቸዋል።

በተለይም በአሁኑ ወቅት እየተበራከተ ለመጣው ግጭት መነሳትም ሆነ መባባስ ዋነኛ ተጠያቂ ምሑራኑ መሆናቸውን አንስተው፤ ‹‹ለምሳሌ አንድ የሌላ ብሔር ተከታይ ገበሬና ሌላ ደግሞ የሌላ ብሔር ተከታይ ገበሬን ፊት ለፊት በማስቀመጥ በጋራ እረሱና ብሉ ቢባሉ ሳያመንቱ ነው የሚቀበሉት፤ ያላቸውንም አብቃቅተው ይጠቀማሉ እንጅ አይገዳደሉም፤ ምክንያቱም ቁርሾውና ጥላቻው ያለው በልሂቃኑ መካከል እንጂ በተራው ሕዝብ ባለመሆኑ ነው። የቅራኔውን እርሻ የሚያርሱትም ልሂቃኑ ናቸው›› ብለዋል።

አውቀናል የሚሉት እነዚህ ጥቂት ግለሰቦች የመሰላቸውን እየፃፉና የመሰላቸውን እየተናገሩ በተለይም ወጣቱን ትውልድ ወደአላስፈላጊ የጥፋት መስመር እየከቱት በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም አቶ ማሞ አመልክተዋል። ‹‹በአሁኑ ወቅት ያለው ወጣትም ሆነ ያልተማረው ሕዝብ እየተመራ ያለው በእነዚህ ጨለምተኛ አስተሳሰብ ባላቸው ልሂቃን ነው፤ እነሱ የተናገሯት ትንሽ ሃሳብ ብዙ ችግር አቀጣጥላ አገር እስከማጥፋት የሚደርስበት ሁኔታ አለ›› ሲሉም አስረድተዋል።

በመሆኑም እዚህች አገር ላይ ሰላም እንዲሰፍንና የሕዝብን እርስ በርስ መጨራረስ ለመታደግ ይቻል ዘንድ ልሂቃኑ ከጥፋት ጎዳናቸው ለመመለስ ቁርጠኛ ሊሆኑ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ‹‹አሁንም ቢሆን ለደረሰው ጥፋት ሁሉ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ቆመው ይቅርታ መጠየቅ ያለባቸው ልሂቃን ናቸው። ለዚህ ደግሞ ደፋሮች መሆን አለባቸው›› ብለዋል።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ በኢትዮጵያ ትክክለኛ ልማትና ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ሁሉም የየራሱን የቤት ሥራ መሥራት ይገባዋል። በተለይም ልሂቃኑ ያላቸውን እውቀትና ልምድ ተጠቅመው ሕዝቡን ማቀራረብና የቆየውን የመቻቻል እሴት ማስቀጠል ይገባቸዋል። ልዩነቶችን ከማስፋት ይልቅም የሚያግባቡ የመፍትሔ ሃሳብ በማመንጨት ኃላፊነታቸውን መወጣት

ሕዝቡን የሚያጋጩ ልሂቃን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ



አቶ ምትኩ ካሳ

## በትግራይ የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሶችን በተረጂዎች ዝርዝር መሠረት እንደሚከፋፈል ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፍ ረጂ ድርጅቶች በትግራይ ክልል የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሶችን በተረጂዎች ዝርዝር መሠረት እንደሚያከፋፍሉ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ምትኩ ካሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ወደ ትግራይ ክልል ድጋፍ እያቀረቡ ያሉ ድርጅቶች መብትና ግዴታ ያላቸው ናቸው ። መብትና ግዴታቸው መሠረት አድርገውም ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን በየብስ አጓጉዞ ትግራይ ክልል የማድረስና

በትግራይ የምግብና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ዜና

# ኤጀንሲው ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን ወጣቶች እየደገፈ እንደሚገኝ ገለጸ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን ወጣቶች በመደገፍ አቅማቸውን የሚያሳድጉበትንና ራሳቸውም ሆነ አገራቸው የሚጠቅሙበትን ምቹ ዕድል ለመፍጠር እየሠራ መሆኑን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ አስታወቀ። የሥራ እድል ፈጠራ ላይ የሚሠሩ ድርጅቶችና ተቋማት ለወጣቶቹ ድጋፍ ሊያደርጉ እንደሚገባም አመልክቷል።

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሹመቴ ግዛው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኤጀንሲያቸው በሳይበር ደህንነት ዘርፍ ፍላጎትና ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን ልጆች በማሰልጠን እንዲሁም ከስራው ጋር ትውውቅ እንዲያደርጉ እድል በመስጠት ላይ ይገኛል። ወጣቶች በመደገፍ አቅማቸውን የሚያሳድጉበትንና ራሳቸውንና አገራቸውን የሚጠቅሙበት ሁኔታ እንዲፈጥሩ እየሠራ ነው።

የፈጠራ ባለሙያዎችን የመደገፍ ሥራ ለመንግሥት ብቻ የሚተው አይደለም ያሉት ዶክተር ሹመቴ ፤የሚመለከታቸው አካላትና ባለሀብቶች ልዩ ተሰጥዖና ችሎታ ያላቸውን ሰዎች በመደገፍ በጋራ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ሊፈጥሩ ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በሳይበር ደህንነት ዘርፍ ላይ ተስፋ የሚጣልባቸው ፈጠራዎችን በመሥራት ላይ እንደሚገኙ የጠቆሙት ዶክተር ሹመቴ፤ በጤና፣ ግብርና፣ በኢንዱስትሪና በሳይበር ነክ መስኮች የሚሠሩ ወጣቶችን ችሎታቸውንና ፈጠራቸውን መተግበር የሚችሉበት እድል ሊመቻችላቸው እንደሚገባም ገልጸዋል።

በመንግሥት በኩል ወጣቶችን ማበረታታትና የመደገፍ ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው መሆኑን የሚናገሩት ዶክተር ሹመቴ፤ ኤጀንሲያቸውም በሳይበር ደህንነትና ተዛማጅ ዘርፎች ላይ ፍላጎት ያላቸውን በየትኛውም የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ ወጣቶች በማሰጠልንና በማስተማር የማበረታታትና የመደገፍ ተግባራትን መጀመሩን ተናግረዋል።

ዶክተር ሹመቴ እንደገለጹት፤ ቢሯቸው ሳይበር ቻሌንጅ በሚባል ፕሮግራሙ አማካኝነት የኢንተርኔት እድል ያላቸውን ወጣቶች የማብቃት ሥራ እየሠራ ይገኛል።

የሳይበር ደህንነት ዘርፉ ተለዋዋጭና መገመት የማይችል እየሆነ እየመጣ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ጦርነት፣ እገታ፣ ዲፕሎማሲ እንዲሁም የማኅበራዊ ስነ-ተግባቦት በሙሉ ዲጂታል እየሆኑ በመምጣታቸው ምክንያት ከስር መሠረቱ መረጃ ሀብት የሆነበት ዘመን በመሆኑ በዘርፉ ያሉትን ተዋናዮች ማበረታታት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመዝለቅ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለውም ገልጸዋል።

ኤጀንሲያቸው በትምህርት ደረጃ ያልተገደበ ፕሮግራሚንግ ፣ሀኪንግና ሌሎችም ዘርፎች ላይ ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች ተሰጥዖን የማልማት ሥራ በመከወን ላይ ይገኛል ያሉት ዶክተር ሹመቴ፤ በመጀመሪያው ዙር 42 እንዲሁም በሁለተኛው ዙር 37 ሰልጣኞችን ማሰልጠኑን ተናግረዋል።



ዶክተር ሹመቴ ግዛው

በቢሯቸው የሰለጠኑት ወጣቶች በዓለም አቀፍ ተቋማት በሳይበር ደህንነት የሥራ መስኮች ተቀጥረው የመሥራት እድል ሊኖራቸው እንደሚችል የጠቆሙት ዶክተር ሹመቴ፤ ለማይክሮሶፍት፣ ጎግልና በአገር ውስጥም በባንኮችና በኢንሹራንሶች የመቀጠር እድል እንዳላቸውም ተናግረዋል።

# መኢአድ በሚያካሂደው ዓመታዊ ጉባኤ ታሪካዊ ውሳኔዎችን እንደሚያሳልፍ ይጠበቃል

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- መኢአድ ከዛሬ ጀምሮ ለሁለት ቀናት በሚያካሂደው ዓመታዊ ጉባኤው ታሪካዊ ውሳኔዎችን እንደሚያሳልፍ ይጠበቃል፡፡

የመኢአድ አገራዊ የፖለቲካ ድርጅት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ በቃሉ ደሳለኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ለአገራዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባኤቻውን እንዲያደርጉ ማሳሰቡን ተከትሎ ድርጅቱ ዛሬና ነገ ጉባኤውን ያካሂዳል።

ፓርቲው በጉባኤው አሁን ኢትዮጵያ ያለችበትን የጸጥታ ሁኔታ በጥልቀት ይገመግማል።

እንደ አገርና የፖለቲካ ድርጅትም በአገራዊው የጸጥታ ሁኔታ እና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ የጠቅላላ ጉባኤው ግምገማን ተንተርሶ ድርጅቱ የራሱን አቋም ይይዛል ብለዋል።

ዛሬ በሚያካሂደው ዓመታዊ ጉባኤም በፖለቲካ ድርጅቱ በኩል ለአገር የሚበጁና አሁን ያለውን አገራዊ ሁኔታ አንድ እርምጃ ሊያራምዱ የሚችሉ ታሪካዊ ውሳኔዎች ይወሰናሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

ፓርቲው በጉባኤው ነባሩን የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ ተሻሽሎ እንዲጸድቅ ይደረጋል ያሉት አቶ በቃሉ፤ አጠቃላይ የድርጅቱ ሥራ አስፈጻሚም እንደ አዲስ ይዋቀራል ብለዋል።

እንደ አቶ በቃሉ ገለጻ፤ በጉባኤው በመኢአድ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ የተጓደሉ የማዕከላዊ ምክር ቤት አባላትና የሥራ አስፈጻሚ አባላት እንዲሟሉ ይደረጋል።

በኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጁን ለማስፈጸምና ቦርዱ ባወጣው መመሪያ መሠረት ፓርቲዎች በመተዳደሪያ ደንባቸው ላይ ሕጉ በሚያዘው መሠረት ማስተካከያዎችን በማድረግ እንዲያቀርቡ ተገልጾ እንደነበር ያስታወሱት አቶ በቃሉ፤ ፓርቲው መመሪያውን ተከትሎ ከዛሬ ጀምሮ ለሁለት ቀናት ጠቅላላ ጉባኤውን ያደርጋል።

ከጉባኤው በኋላ በጠቅላላ ጉባኤው ቃለ-ጉባኤ፣ ማሻሻያ የተደረገባቸውን እና በጉባኤ የጸደቀውን አዲሱን መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም ሌሎች ማሻሻያ የተደረገባቸውን የድርጅቱን ሰነዶች በተጠየቀው መሠረት ለኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ እንደሚያቀርብም ተናግረዋል።

# የአምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂዩማን ራይትስ ዎች የጋራ ሪፖርት ፍጹም ሐሰት መሆኑን በወልቃይትና አካባቢው በመገኘት ለማየት ችያለሁ

አዲስ አበባ፡-አምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂዩማን ራይትስ ዎች በወልቃይት ዙሪያ ያወጡት የጋራ ሪፖርት ፍጹም ሐሰት መሆኑን በቦታው ላይ ተገኝቼ ለማየት ችያለሁ ስትል ትውልደ-ኢትዮጵያዊቷ ጋዜጠኛ ቤቲ ተከስተ ገለጸች።

በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት የተገኙትን የጅምላ መቃብሮች መመልከቷንና አሁንም ተጨማሪ ምርመራ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተናግራለች።

በቨርጂኒያ ግዛት የምትኖረው የፑሽ ስታርት ሚዲያ ጋዜጠኛ ቤቲ ተከስተ ከአሜሪካዊቷ ጋዜጠኛ አን ጋሪሰን እንዲሁም አሜሪካዊው የፎቶ ጋዜጠኛ ጀማል ካውንተስ ጋር በመሆን በአማራ ክልል በጦርነቱ የደረሰውን የጉዳት መጠንና ዜጎች ያሉበትን ሁኔታ ለማየት ወደ ተለያዩ አካባቢዎች መጓዟን ገልጻለች።


በጉዟቸውም ‘በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ላይ የተፈጸመውን ግድያና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን አስመልክቶ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ያወጣው ሪፖርት አለ’ የሚል መረጃ ደርሷቸው ወደ ሥፍራው እንዳቀኑ ተናግራለች።

በአካባቢው የተገኙትን የጅምላ መቃብሮች በአካል እየተመለከቱ እንዲሁም ሕዝቡን እያናገሩ በነበሩበት ወቅት የአምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂዩማን ራይትስ ዎች የጋራ ሪፖርት መውጣቱን አመልክታለች።

“በትግራይ ተወላጆች ላይ የደረሰ ጥቃት” በሚል ሐሳብ የወጣው ይህ ሪፖርት ቦታው ላይ ካየሁት ሁኔታ ጋር ፍጹም የተቃረነ ነው ብላለች ጋዜጠኛ ቤቲ።

ምዕራባውያን ጋዜጠኞችም በሥፍራው በመገኘት እውነታውን መመልከታቸውንና፤ ሁለቱ ተቋማት ያወጡት ሪፖርት ሐሰተኛ መሆኑን ማረጋገጣቸውን አብራርታለች።

በወልቃይትና አካባቢው የሚኖሩና የጥቃቱ ቀጥተኛ ሰለባ የሆኑ የአማራ ተወላጆች የደረሰባቸውን እሥራት፣ በደልና ስለ ጅምላ መቃብሮቹ ገለጻ እንዳደረጉላቸው አመልክታለች።



ጋዜጠኛ ቤቲ ተከስተ

“ከአይን እማኞችና ግፉ ከተፈጸመባቸው ሰዎች መረጃ እየተቀበልን ባለንበት ሰዓት የጋራ ሪፖርቱ ይህ በደል በሌላ አካል ተፈጽሟል የሚል ነገር ማውጣቱ በኢትዮጵያ ላይ የሚሰራጩ መረጃዎች ከእውነታ ፍጹም የራቁ መሆናቸውን ያሳያል” ብላለች።

የጅምላ መቃብሮቹን አስመልክቶ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ የጥናት ቡድን ማብራሪያ እንዳገኙም ነው ጋዜጠኛ ቤቲ የገለጸችው።

ጥናቱ ባለመጠናቀቁ የጅምላ መቃብሮቹ ቁጥር ከዚህም በላይ እንደሚጨምርና ተጨማሪ ምርመራ እንደሚደረግ ከጥናት ቡድኑ መረዳት መቻሏንም እንዲሁ።

የጅምላ መቃብሮቹን በተመለከተ የፎረንሲክ ምርመራን ጨምሮ ሌሎች ሳይንሳዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ዝርዝር ጥናት ማድረግ እንደሚያስፈልግም አመልክታለች።

“ከብዙ ዓመታት በፊት ግድያ የተፈጸመባቸው ዜጎች ታሪክ ዛሬ በሌላ አካል እንደተፈጸመ ተደርጎ ነው የሚወራው፤ አሁን ላይ የደረሰው ጉዳት ትክክለኛ መረጃና እውነት እየወጣ ይገኛል” ነው ያለችው ትውልደ-ኢትዮጵያዊቷ ጋዜጠኛ።

“እንደ ጋዜጠኛ ሁልጊዜም እውነትን መናገር አለብን” ያለችው ጋዜጠኛ ቤቲ፤ በወልቃይትና አካባቢው በነበራት ቆይታ የተፈጠረውን ትክክለኛ ነገር መረዳቷን ገልጻለች።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የጥናት ቡድን ቀጣይ ለሚያደርገው ጥናት ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ያላቸውን ባለሙያዎችን በማገናኘት ድጋፍ እንደምታደርግም ኢዜአ ዘግቧል።



# ለጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ማዕከል ምስረታ ድጋፍ እንደሚያደርጉ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ገለጹ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-ለጥቁር ሕዝቦች ታሪክ፣ ቅርስ ማቆያና የትምህርት ማዕከል ምስረታ ድጋፍ እንደሚያደርጉ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ገለጹ።

አቶ ኃይለማሪያም በለንደን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ተገኝተው ከጥቁር ሕዝቦች የሕግ፣ የታሪክና የማኅበራዊ ሳይንስ ምሑራን ጋር ባካሄዱት ውይይት የጥቁር ሕዝቦች የታሪክ፣ የቅርስ ማቆያና የትምህርት ማዕከል በአዲስ አበባ ላይ ለማቋቋም የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ እንደሚደግፉ ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በፓን አፍሪካን እንቅስቃሴ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው በመሆኑና ጉዳዩን በቁርጠኝነት የሚከታተሉት ስለሆነም ለምስረታው ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንደሚያመቻቹ ተናግረዋል።

የጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ስፔሻሊስትና ደራሲ ሮቢን ዎከር በበኩላቸው ከድሕረ ቅኝ አገዛዝ በኋላ ያለው በጥቁር ሕዝቦች ላይ ያተኮረ ትርክት እጅግ የተዛባ ነው። በዚህ ወቅት ግን ምሑራን በሚያደርጉት ያላሰለሰ ጥረት በራስ መተማመን ላይ የተመሠረተ ስነ ልቦና መላበስ ለጥቁር ሕዝቦች ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ መሆኑን ገልጸዋል።

ይህን የጥቁር ሕዝቦች በራስ የመተማመን ስነልቡና ለማጎልበት ቅድመ ቅኝ አገዛዝ የጥቁር ሕዝቦችን ታሪክና ቅርስ መመርመር የሚያስችል ማዕከል አዲስ አበባ ላይ መመስረት ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

በዩናትድ ኪንግደም የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ቡድኑ ማዕከሉን በአዲስ አበባ ለማቋቋም በኤምባሲው ተደጋጋሚ ውይይቶች መካሄዳቸውን አስታውሰው ለስኬታማነቱ የበኩላቸውን ጥረት እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

የቡድኑ አስተባባሪ ትውልደ ኢትዮጵያዊው አቶ ጺጋዬ ጫማ እንደገለፁት ቡድኑ የማዕከሉን ምስረታ ለማቀላጠፍ ወደ አዲስ አበባ በርካታ አባላቱን በመያዝ ይጓዛል። ኤምባሲው ለዚህ ዓላማ ስኬት ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ በመሆኑ ሊመሰገን ይገባዋል ብለዋል።

# የሲዳማ ብሔር ዘመን መለወጫ ፊቼ ጫምባላላ በዘንድሮው ዓመት በድምቀት ይከበራል


አዲስ አበባ፡- የሲዳማ ብሔር የዘመን መለወጫ ፊቼ ጫምባላላ በዓል አከባበርን አስመልክቶ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃጎ አገኘሁ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥተዋል።

ላለፉት ሁለት ዓመታት ፊቼ ጫምባላላ በዓል በኮሮና ምክንያት በጉዱማሌ አልተከበረም። ዘንድሮ በሲዳማ ብሔር ዘንድ አልፎም በአደባባይ በጉዱማሌ ቅድመ ዝግጅት ተጠናቅቋል ብለዋል።

ቀኑን ማስታወቅና ወዘተ እንዲሁም የበዓሉ ቅድመ ዝግጅት ቅቤ በማጠራቀም፣ የተጣሉትን የማስታረቅ፣ የከብቶች የግጦሽ ሳር ማዘጋጀትና የመሳሰሉ ልዩ ልዩ ክንውኖችን በቤተሰብ ደረጃ ይደረጋሉ ብለዋል።

የፊቼ ጫምባላላ በዓል የዓለም ቅርስ ሆኖ በዩኔስኮ የተመዘገበ የማይዳሰስ ቅርስ ነው ያሉት ኃላፊው በዓሉን ለመታደም ከተለያዩ አገራት ለሚመጡ ቱሪስቶችና ለባለድርሻ አካላት ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ፊቼ ጫምባላላ በውስጡ የያዛቸው እሴቶች በመኖሩ ይሄንንም የሚገልጽ የፓናል ውይይት በፊቼ ቀን ይካሄዳል ብለዋል።

የክልሉ መንግሥት በኩል ቅድመ ዝግጅት እየተጠናቀቀ እንደሆነ በመግለፅ ሕዝቡ በዓሉን ያለ



**አቶ ጃጎ አገኘሁ**

አንዳች ችግር እንዲያከብር የተለያዩ ኮሚቴ ተዋቅሮ ሥራውን በመሥራት ላይ እንደሚገኝ ኃላፊው መግለፃቸውን የሲዳማ ርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት መረጃ ያመለክታል።

# ጥራት ያለው የሕክምና አገልግሎት እንዲኖር የሐኪሙን ብቃት ማሳደግ እንደሚገባ ተጠቆመ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ጥራት ያለው የሕክምና አገልግሎት እንዲኖር ከተፈለገ የሐኪሙን ብቃት ማሳደግ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሕክምና ማኅበር አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ሕክምና ማኅበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ተግባር ይግዛው በትናንትናው ዕለት የማኅበሩ 58ኛ ዓመታዊ የሕክምና ጉባኤ ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ጥራት ያለው የሕክምና አገልግሎት እንዲኖር ከተፈለገ የሐኪሙን ብቃት ማሳደግ ይገባል፤ ለዚህም ሲባል ማኅበሩ ከተመሠረተ ጀምሮ የሐኪሞችን ሙያ ማጎልበቻ ሥርዓት ዘርግቶ እየሠራ ይገኛል።

ጥራት ያለው የሕክምና አገልግሎት ኅብረተሰቡ እንዲያገኝ ማስቻል የማኅበሩ ዋና ዓላማ ነው ያሉት ዶክተር ተግባር፤ የሙያ ማኅበር እንደመሆኑ ለሐኪሞች ድምፅ የመሆንና የሐኪሞችን ጥቅም ማስከበር ሥራም ይሠራል። በተጨማሪም ምርምር በማድረግና የባለሙያዎችን አቅም በማሳደግ የሕክምናን ሙያ እያሳደገ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

21ኛው ክፍለ ዘመን አዳዲስና ያልታሰቡ ፈተናዎችን ይዞ እየመጣ መሆኑና የሕክምና ሳይንስም በየጊዜው ተቀያያሪ ሁነቶች ስላሉበት ባለሙያዎችን በሥነ ልቦና ዝግጁ ማድረግና በብቃት መገንባት ግድ የሚል ተግባር ነው። ለዚህም ከጤና ሚኒስቴር፣ ከትምህርት ሚኒስቴር እና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመተባበር ባለሙያዎች ብቁ እንዲሆኑ እና ሙያው እንዲዳብር እየተሠራ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

በየዓመቱና በየጊዜው በርካታ ፈተናዎች ስለሚለወጡ ያሉትን አዳዲስ ነገሮች በማጥናትና የሐኪሞችን ፍላጎት በመጠየቅ አዳዲስ ሥልጠናዎች እንዲኖሩ እየተደረጉ መሆኑን አንስተዋል።

በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የተከሰተው ጦርነት እና የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በጤናው ዘርፍ ያልታሰቡ



**ዶክተር ተግባር ይግዛው**

ፎቶ፡ሑዳሽ አብርሃ

ክስተቶች መሆናቸውን እንደ አብነት ያነሱት ዶክተር ተግባር፤ ለሁለቱም ጉዳዮች በቅንጅት በመሥራት ባለሙያዎችን ፈጣንና ተከታታይ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ተደርገዋል ሲሉ አብራርተዋል።

እንደ ዶክተር ተግባር ገለጻ፤ ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ በቀዶ ጥገና እና ድንገተኛ እርዳታ በማድረግ ዙሪያ ተከታታይ ሥልጠናዎች መሰጠታቸውን እንዲሁም አስገድዶ መድፈር የገጠማቸውን ሰዎች የሥነ አዕምሮ እና የሥነ ልቦና ሕክምና እንዴት መስጠት ይገባል በሚለው ዙሪያ ለሐኪሞች ሥልጠናዎች ተሰጥተው ተግባር ላይ ጥሩ ውጤት ታይቷል።

የኮቪድ 19 ሕክምና እና ክትባቶችን አስመልክቶም የሚወጡ አዲስ ነገሮችን ባለሙያዎች እንዲያውቁ ለማድረግ በተለያየ መንገድ ሥራዎች ተሠርተዋል። ማኅበሩም የመጀመሪያው ኮቪድ 19 ታማሚ ከመገኘቱ አስቀድሞ ጉዳዩን በመሪነት ሲከታተልና መረጃ ሲያደርስ ነበር ተብሏል።

የባለሙያዎችን ብቃት ለማዳበር በተለይ በኮቪድ 19 ወረርሽኝና ክትባት ዙሪያ በአካልና በተንቀሳቃሽ ምስል የተደገፉ ሥልጠናዎች መሰጠታቸው ተገልጿል።

የሕክምናውን ጥራትም ሆነ የሐኪሙ ብቃት የሚረጋገጠው ተከታታይ ትምህርት በመስጠት ነው ያሉት ዶክተር ተግባር፤ ለዚህም ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከጤና ሚኒስቴርና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመሆን የሕክምና ትምህርት ስታንዳርዶችን በማዘጋጀት በኩል ማኅበሩ ትልቅ አስተዋፅዖ አበርክቷል ብለዋል። በዚህም ወደ ሙያው የሚገቡ ሰዎች ጠንካራ በሆነ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ እንዲያልፉ እየሠራን ነው ሲሉም አክለዋል።

የጤና ትምህርት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶችም ራሳቸውን እንዲፈትሹ እና በሌላ አካልም እንዲታዩ ማድረግና ከከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ ጋር በመሆን ትምህርት ቤቶችን የመገምገም ሥራዎች በማኅበሩ እየተሠሩ መሆናቸውን አብራርተዋል።

በተጨማሪም የጤና ባለሙያዎችን የሚያሠለጥኑ ትምህርት ቤቶች የሚገጥሟቸውን የአቅም ግንባታ ችግሮች ለመፍታት በየወሩ በበይነ መረብ የታገዘ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለመምህራን እየሰጡ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

# በዓለም የሥራ ድርጅት የፀደቁ የሠራተኛ ፍልሰት ስምምነቶች በኢትዮጵያ ተግባራዊ እንዲደረጉ ተጠየቀ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በዓለም የሥራ ድርጅት /ILO/ የፀደቁ የሠራተኛ ፍልሰት ስምምነቶች በኢትዮጵያም የሕግ አካል ሆነው እንዲተገበሩ የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን(ኢሰማኮ) ጠየቀ።

የሠራተኞች ፍልሰትን በተመለከተ የጸደቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በኢትዮጵያ ተግባራዊ እንዲደረጉ የሚገፋፋ የግንዛቤ ማስጨበጫ የዘመቻ ፕሮግራም ትናንትና ተጀምሯል።

በወቅቱት የኢሠማኮ ፕሬዚዳንት አቶ ካሳሁን ፎሎ፤ ለፍልሰት የተጋለጡና በአገር ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች መብቶቻቸው ሊጠበቁ እንደሚገባ ጠቁመው፤ መንግሥት ስምምነቶቹን በማጽደቅ መብታቸውን እንዲያስከብር ጠይቀዋል።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ፍልሰተኛ ሠራተኞች፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት በቤት ሠራተኝነት የሚያገለግሉ ጥቃትና ትንኮሳ እንደሚደርስባቸው ገልጸዋል።

ሠራተኞቹ ያሉበት ሁኔታ እጅግ አሳሳቢና ልዩ ትኩረት የሚሻ በመሆኑ ኢሠማኮ ዘመቻ መጀመሩን ተናግረዋል። የዘመቻው ዓላማም ዓለም አቀፍ ሕግጋት እንዲጸድቁ በመገፋፋት የሠራተኞቹ መብት እንዲከበር ማድረግ ነው ብለዋል።

ዓለም አቀፍ ሕጎቹ ተቀባይነት አግኝተው በኢትዮጵያ ቢጸድቁ በሥራ ቦታ ላይ የሚደርሱ ችግሮችን በመቅረፍና የሠራተኛውን መብት በማስከበር ረገድ ትልቅ ሚና እንደሚኖራቸው አቶ ካሳሁን ተናግረዋል።

ስምምነቶቹ ቢጸድቁ የፌዴራል መንግሥትም ከሌሎች የኢትዮጵያን ሠራተኛ ተቀባይ ከሆኑ አገራት ጋር ለመደራደር ትልቅ አቅም እንደሚፈጥርለት አስታውቀዋል።

በመሆኑም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ስምምነቶቹን ማጽደቅና የኢትዮጵያ የሕግ አካል ሆነው ተግባራዊ እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ገልጸዋል።

የግንዛቤ ማስጨበጫ የዘመቻ ፕሮግራሙን የዓለም ሥራ ድርጅት የምስራቅ አፍሪካ ዳይሬክተር አሌክሶ ሙሲንዶ ፣የኢሠማኮ ፕሬዚዳንት አቶ ካሳሁን ፎሎና የኢትዮጵያ አሠሪዎች ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ታደለ ይመርና በጋራ በመሆን ዘመቻውን በይፋ አስጀምረውታል።

በዘመቻው ማስጀመሪያ ላይ አራት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የተዋወቁ ሲሆኑ፤ በሥራ ቦታ ላይ የሚደርስ



አቶ ካሳሁን ፎሎ

ፎቶ በሃዲስ አብርሃ

የጥቃትና ትንኮሳ ስምምነት ቁጥር 190 ከተዋወቁት መካከል አንዱ ነው። በተጨማሪ የቤት ሠራተኞች ላይ የሚደርስ የመብት ረገጣና እንግልት ስምምነት ቁጥር 189ና አጠቃላይ የፍልሰተኛ ሠራተኞችን በቀጥታ የሚመለከቱ ስምምነት ቁጥር 97ና 143 ከተዋወቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መካከል ይገኙበታል።

ዘመቻው ስምምነቶቹ ጸድቀው በሥራ ላይ እስከሚውሉ ድረስ እንደሚቀጥልም ታውቋል።

# ‹‹ሠራዊቱ የኢትዮጵያ..

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሠራዊት የኢትዮጵያ የመጨረሻ ምሽግ እንጂ ከፓርቲ ጋር የሚጣበቅ መሆን የለበትም።ብልጽግና ከሠራ ያልፋል ካልሠራ ይወድቃል።ከዚህ አኳያ መከላከያ ሠራዊቱ ኢትዮጵያ የመጨረሻ ዘብ እንጂ ከብልጽግና ፓርቲ ጋር የሚጣበቅ መሆን የለበትም።

የአገር መከላከያ ሠራዊት የኢትዮጵያ የመጨረሻ ምሽግ እንዲሆን በሰነድና በሃሳብ የማዘጋጀት ሪፎርም ተዘጋጅቷል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በኋላም ሕብረብሔራዊ እንዲሆን በቴክኖሎጂ እንዲዘምንና አደረጃጀቱ እንዲስተካከል ሰፊ ሥራ ተሠርቷል። ይህ በመረጃና መረብ ደህንነት ኤጀንሲ፣ በመከላከያ ፣ በሪፐብሊካን ጋርድ እና በሌሎቹም የጸጥታና ደህንነት ተቋምት ተግባራዊ የተደረገ ጉዳይ ነው ብለዋል።

በጭንቁ ጊዜ የተዋጋችሁት፤ ሕዝብን ያወያያችሁትና ያረጋጋችሁ እንዲሁም በፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ውሃ ያጠጣችሁት እናንተው ናችሁ ሲሉ ለመከላከያ ጀኔራሎችና መኮንኖች የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ካድሬው በችግር ጊዜ ጥሎ እየሸሸ በሰላሙ ጊዜ እናንተን የመከላከያ ሠራዊት አመራሮች ሊገመግም ይፈልጋል። ይሄ ከካድሬው ጋር የተያያዘው አንዱ በሽታ ነው ።ካድሬው መከላከያ ሠራዊቱ ጋር ተጣብቆ ስርቆቱን ሊሸፍን ይፈልጋል። ይህን ሠራዊቱ መፍቀድ የለበትም ሲሉ ገልጸዋል።

መከላከያን ሪፎርም በማድረግ ሂደት ካጋጠሙን ችግሮች አንዱ መከላከያና ፖለቲካው የነበራቸው መጋባት ነው ሲሉም አስታውቀዋል።

ካድሬ የእራሱን ሥራ ሳይሠራ በሙስና ሕዝብ እያስለቀሰ መከላከያ ጋር ተለጥፎ ይደበቃል። ይህን አሁን መፍቀድ የለባችሁም ሲሉም ለመከላከያ አመራሮች መልዕክት አስተላልፈዋል።

ወታደር ናችሁና የትኛውም ካድሬ በሥራው የእናንተን ሩብ እንኳን አያክልም ። ካድሬው ግን ሰርቆ ያከማችና መከላከያውን መጠቀሚያ ያደርጋል፤በብሔር ሰበብም እየገባ ይጫወታል። እናንተ ከዚህ በራቀ መንገድ በመንቀሳቀስ ክብራችሁን መጠበቅ አለባችሁ ሲሉ አሳስበዋል።

ሌላው ወታደሮች በጣም ጥንቃቄ እንድታደርጉ የምለምናችሁም የምመክራችሁም በብሔር ኮንቴይነር ውስጥ ወርዳችሁ የምታስቡ ከሆነ ከሕወሓት ጋር መገዳደል ሕወሓትን መታገል አስፈላጊ አልነበረም ማለት ነው ብለዋል።

ምክንያቱም ሕወሓትም ሲያደርገው የነበረው ይህንኑ ነው። ሕወሓትን ጠልታችሁ የእሱውን ተግባር የሚደግም ነገር ማድረግ የለባችሁም ሲሉ አስረድተዋል።

ለሚመጡ ችግሮች ሁሉ እራስን እንደግለሰብ እንዲሁም እንደ አገርም ማዘጋጀት ያስፈልጋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ወታደር በሰላሙ ጊዜ የሚያደርገው ዝግጅት በመከራው ጊዜ ውጤታማ እንደሚያደርገው ገልጸዋል።

በትልማችን መሠረትም እ.ኤ.አ. በ2050 ከዓለም ጠንካራ ኢኮኖሚ 20ዎቹ ውስጥ ኢትዮጵያ መግባት አለባት። ምክንያቱም ከአፍሪካ ናይጀሪያ ብቻ ነው በሕዝብ ቁጥር ከእኛ የምትበልጠው፤ ይህን በአግባቡ መጠቀም አለብን ብለዋል።

መከላከያና የደህንነት ተቋማትን ጨምሮ የአገሪቷን ተቋማት እራሳቸውን የሚያፈርሱ ሳይሆን ትውልድ የሚያስቀጥሉ ተቋማትን መገንባት ከቻልን ያለምንም ጥርጥር የኢትዮጵያ ቀጣዮቹ የ30 ዓመታት ታሪክ የኮርያን ታሪክ የሚደግም መሆኑን ገልጸዋል።

እኛም ያ አቅም አለን። ይህ አቅም እንዳይፈጠር የሩቅ ጠላቶቻችንም ሆነ የቅርብ ኃይሎች ይፈልጋሉ። እኛ የቅርቦቹን ታሳቢ አርድገን ከተዘጋጀን አናድግም። የቅርቦቹን የሚልኳቸውን ታሳቢ አድርገን ከተዘጋጀን ግን እናድጋለን ብለዋል።

ለዚህም የሚመጥን ብቃትና ሥራ ያስፈልጋል፤ እንደአጠቃላይም የራዕያችን መንገደኛ እንጂ የችግሮቻችን እስረኛ መሆን የለብንም ሲሉ ተናግረዋል።

የመከላከያ ሠራዊት ተቋም፣ ደህንነቱን፣ ፖሊስና ሌሎች ተመሳሳይ ተቋማት ለአገር በጣም ወሳኝ ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዚህ ረገድ ተልዕኮ ያላቸውና ሥራቸውን የሚያውቁ እንዲሁም ወዴት መሄድ እንዳለባቸው የሚገነዘቡ ተቋማት ያስፈልጋሉ፤ ለዚህም ሁሌም ተግተን መሥራት ይኖርብናል ሲሉ ተናግረዋል።

# በትግራይ የምግብና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በተጠቃሚዎች ዝርዝር መሠረት ምግብ የማከፋፈል ሥራ ይሠራሉ።

በትግራይ ክልል ምግብ በማቅረብ ረገድ የዓለም የምግብ ፕሮግራም፣ ኬቬ ኢንተርናሽናል፣ ሲአር ኤስ፣ ወርልድ ቪዥንና የዓለም የምግብ ፕሮግራም ሥራቸውን እየሠሩ እንደሚገኙ ጠቅሰው፤ ዩኒሴፍ፣ የዓለም የጤና ድርጅትና መሰል ድጋፍ አድራጊ ተቋሞች ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን የሚያቀርቡ ሲሆን ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ውል ገብተው እየሠሩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ድርጅቶች ለተጠቃሚዎች ያከፋፈሉትን ምግብም ይሁን ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን ለኢትዮጵያ መንግሥት ሪፖርት እንደሚያደርጉ ኮሚሽነሩ አመልክተው፤ በሪፖርቱ መሠረት የኢትዮጵያ መንግሥት እርዳታው በትክክል ለተጠቃሚዎች እንደሚደርስ ይቆጣጠራል ብለዋል።

ረጂ ድርጅቶች እርዳታ የሚያደርጉት ገለልተኛ በመሆን፣ ባለማዳላትና መሰል ዓለም አቀፍ መርሆችን መሠረት አድርገው ኃላፊነቱን ሙሉ ለሙሉ ወስደው ይሠራሉ ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት በሚፈለገው ልክ እርዳታ አቅርቦት የለም ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በነበረው ጦርነት ዓለም አቀፍ ረጂ ድርጅቶች ትኩረታቸው በትግራይ ክልል ሆኖ መቆየቱን አስረድተዋል። በተመሳሳይ በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸው የአፋርና የአማራ አካባቢዎች ተዘግተው መቆየታቸውን አውስተው፤ዓለም አቀፍ ረጂ ድርጅቶች ትኩረታቸውን በአማራና በአፋር ክልልም እንዲያደርጉ በተደረገው ጥረትም መሻሻሎች መኖራቸውን ገልጸዋል።

አሁንም በሚፈለገውና በእርዳታ ፈላጊዎች ልክ ባይሆንም በአማራና በአፋር ክልል እርዳታ እየሰጡ መሆኑን ገልጸው፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በሩሲያና በዩክሬን ጦርነት ምክንያት ዓለም አቀፍ ረጂ ድርጅቶች ትኩረታው ወደ ዩክሬን በመሆኑ በኢትዮጵያ የሚደረገው ድጋፍ አመርቂ ነው ብሎ መናገር እንደማይቻል ገልጸዋል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ከትናንት በስቲያ ባወጣው መግለጫ፣ ባለፉት ሁለት ቀናት 47 የምግብ ድጋፍ የያዙ እና 3 ነዳጅ የጫኑ ከባድ ተሽከርካሪዎች በድምሩ 50 የጭነት መኪኖች ከሰመራ ተነስተው ወደ መቀሌ ጉዞ እያደረጉ መሆኑ ተገልጿል።

ተጨማሪ 10 የምግብ እርዳታን የያዙ የጭነት ተሽከርካሪዎችም ከሰመራ ጉዞ መጀመራቸውም ተገልጿል።

ከዚህ ቀደም በየብስ ትራንስፖርት በመጀመሪያው ዙር የምግብ ድጋፍን የያዙ 21 ተሽከርካሪዎች ወደ ትግራይ መግባታቸው ይታወሳል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በትግራይ ክልል በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ዜጎች አስፈላጊው ድጋፍ እንዲደርሳቸው ለማድረግ የገባውን ቃል በማክበር ምቹ የሰብዓዊ ዕርዳታ ማጓጓዣ ሁኔታን ለመፍጠር እየሠራ እንደሚገኝ ይታወቃል።

# ሕዝቡን የሚያጋጩ ልሂቃን ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

‹‹በየምክንያቱ በሃሳብ ተከፋፍለን የተለያዩ አገሮችን ብንፈጥር ማደግ አንችልም፤ ንግድ እንኳን የተሳለጠ የሚሆነው በጋራ ስንኖር ነው። ለምሳሌ ወለጋ የሚኖር አንድ ገበሬ ምርቱን የፈለገውን ያህል ቢያበዛ በሰላም ጊምቢ ማድረስ ካልቻለ ምርቱ ይባክንበታል እንጂ ተጠቃሚ አይሆንም››ብለዋል። በመሆኑም ለመቀራረብ በንፁህ ልቦና ከታሰበበትና ልብን ለፍቅርና ለእርቅ መክፈት ከተቻለ ሁሉም ለአገሩ የሚመኘውን እድገት ማምጣት አይሳነውም›› በማለት አስረድተዋል።

ሁሉም ሰው ልቡን ክፍት አድርጎ ወንድማማችነትን ሲያስብ ሰላምና ልማት ሩቅ እንደማይሆኑ ጠቅሰው፤ ለዚህ ደግሞ ተቀራርቦ መወያየትና መደማመጥ እንደሚያሻ አመልክተዋል። ‹‹ሰላም በብስለት መመካከርን፤ መቀራረብን ይጠይቃል፤ ለዚህ ደግሞ መጀመሪያ ከራስ ጋር መታረቅና ውስጥን ማዳመጥ ያስፈልጋል›› በማለት መክረዋል።

አስቀድሜ እንዳልኩሽ አንድነት ለመፍጠር ፍቅር ያስፈልጋል። ፍቅር ደግሞ ከንቃተ ሕሊና ጋር ይሄዳል። አንዱ መሠረታዊ ችግር ብዬ የማምነው የማኅበረሰቡን ንቃተ-ሕሊና ማሳደግ ያለመቻሉ ነው። ያወቅን እየመሰለን መድረኮች እየዘለልን ሄድን እንጂ ብዙ ያላወቅነው ነገር አለ። ዓለም አሁን ወደ አንድ መንደር በመጣበት ጊዜ እኛ በሰበብ በአስባቡ እርስበርስ እየተገዳደልን በመሆናችን በእውነት ከልብ ነው የሚያሳዝነኝ። ከግድያ ምንም አይገኝም። ከግድያ ምንም የማይገኝ መሆኑን፤ ታግሶ ማለፍንና ሆደ ሰፊ መሆኑን ከኤርትራውያን መማር እንችላለን። እንዳልኩሽ እንደእኔ አይነቱን ገዳዮቻቸውን በፍቅር ተቀብለው ማኖር የሚችሉ ሰዎች መሆናቸውን በሕይወት ያለሁ ምስክራቸው ነኝ። እኛ ደግሞ ከእነሱ በላይ አንድ የሚያደርጉን ነገሮች በመኖራቸው እርስበርስ መከባበርና መፈቃቀድ አለብን።

የቅዳሜ መጽሄት

# አገልግል



ንቁ አእምሮ፤ ለሥራ የተጉ እጆች ለውጤት ያበቃሉ

- አቶ ዳዊት ሞገስ

ገጽ 13

«የቅራኔውን እርሻ የሚያርሱት ምሁራኑ ናቸው»

- አቶ ማሞ አፈታ
የቀድሞ ሰራዊት አባልና ደራሲ

ገጽ 6





ትኩረት የሚሻው ዘገምተኛው ወረርሽኝ

ገጽ 8

ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ ርምጃዎች

የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የአሥራ ስምንት ዓመት ጉዞ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ የቤት ልማት ፕሮግራም ሲነደፍና ወደ ተግባር ሲገባ በመጀመሪያ በዝቅተኛ ደረጃ ለሚገኙ ነዋሪዎች ታስቦ ነው። ከዛም እየሠፋ መጥቶ መሐል ላይ ለደሃ ደሃ የሆኑ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ከስድስት ሺ በላይ 10/90 ቤቶች ተገንብተው እንዲተላለፉ ተደርጓል። በቀጣይ በ2005 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ያላቸውን ነዋሪዎችን ጭምር የቤት ባለቤት ለማድረግ በተነደፈው ስትራቴጂ መሠረት የ40/60 ቤት እንዲገነባ ተደርጓል። በነዚህ ሁሉ ዓመታት ሥራዎች ሲሠሩ የተለያዩ ተግዳሮቶች አጋጥመው ነበር። እንደ አጠቃላይ ሥራው ከ317 ሺ ቤቶች በላይ ተገንብተው ለማኅበረሰቡ ተላልፈዋል። እንደ ከተማ ይሄ ሁሉ ቤቶች ገንብቶ ሲያስተላልፍ በርካታ ችግሮች ተስተውለዋል። አጠቃላይ በአዲስ አበባ ከተማ እየተካሄደ ስላለው የቤቶቹ ግንባታና ያለበትን ደረጃ በሚመለከት የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር ቶማስ ደበሌ የሰጡንን ማብራሪያ የመጀመሪያውን ክፍል እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

የመጀመሪያው ለቤቶቹ ግንባታ የኮንትራት አሰጣጡ በራሱ ችግር ነበረው። በቤት ልማቱ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ ኮንትራክተሮችን ማሳተፍ ላይ ክፍተቶች ነበሩ። ከለውጡ በኋላ በተደረገው ግምገማ የቤት ኮንትራት አሰጣጡ ምን ይመስላል የሚለው ታይቷል። በ2011 ዓ.ም መመሪያው እንዲሻሻል ተደርጎ መዋቅር እንዲሠራ ተደረገ። በዚህም ተቋሙ ከነበረበት ዝቅተኛ ነዋሪውን ተጠቃሚ የማድረግ እቅድ እንዲሁም መካከለኛውን ነዋሪ ተጠቃሚ ለማድረግ የተነደፉ እቅዶችን አንድ ላይ በማድረግ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን በሚል እንዲጠቃለል ተደረገ። የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የአሥራ ስምንት ዓመት ታሪክ ጠቅልሎ ከተመሠረተ ሁለት ዓመት ሆኖታል።

በሁለት ዓመት ውስጥ ቀደም ብሎ የጉልበት ዋጋ ብቻ በማስቀመጥ ሥራ ተቋራጭንና ጥቃቅንና አነስተኛ ማኅበራትን ጭምር ወደ ተቋሙ በቀጥታ በማሳተፍ የሥራ እድሎችን ይፈጥር ነበር። ይህንን አሠራር በመገምገም መንግሥት የመሥሪያ እቃ እያቀረበ ግንባታዎች በስድስትና በስምንት ዓመት በመንግሥት እጅ ሳይጠናቀቁ ይቆያሉ። ግንባታዎቹን ለማጠናቀቅ የነበረውን የውል ሂደት በመቀየር ኮንትራት የወሰደው ድርጅት ከጉልበት ዋጋ በዘለለ ግብዓት እንዲያቀርብ የማድረግ ሥራ ተከናውኗል። በነበረው ነባራዊ ሁኔታ ፕሮጀክቱ የሚመራበት ሂደትና የሚሰጡ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ትክክል ባለመሆናቸው ግንባታዎች አሁን ያለበትን መልክ እንዲይዝ አድርጎታል።

ይሄን ለመቀየር ኮንትራት የሚይዙ ድርጅቶች ወደ አቅርቦት አሠራር እንዲገቡ ሲደረግ ከፍተኛ ጥናት ተካሂዷል። በዚህም የሚኖረው ትርፍና ኪሳራን ለማወቅ ረድቷል። በመንግሥት እጅ ሲቆዩና ወደዚህ አሠራር ሲገባ የሚኖሩትን ክፍተቶችና እድሎች በመገምገም ወደ አሠራሩ ለመግባት ተወሰነ። የሠራተኛ ክፍያ፣ የአማካሪ ክፍያ፣ የግብዓት ብክነት እንዲሁም ሌሎች ነገሮች ሲታዩ ለኪሳራ ስለሚዳረግ ወደ ኮንትራት የሚወስዱ ድርጅቶች ወደ አቅርቦት አሠራር እንዲገባ ሆኗል። ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ የተጀመሩ ግንባታዎች ያሉ ሲሆን ነባር ግንባታ ተብለው አምስትና ስድስት ዓመት የቆዩም ይገኛሉ። በግንባታው ዘርፍ በርካታ ሥራ እየተከናወነ ነው። በዚህም ክፍተቶችን ለመድፈን ብዙ ርቀት ተጉዘናል። እስከ 2013 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ሙከራ ተደርጓል።

ከ2011 እና ከ2013 ዓ.ም መካከል ለተጠቃሚዎች የተላለፉ ቤቶች አሉ። አንድ ሺ 229 ቤቶች በእጣ የተላለፉ ሲሆን 22 ሺ 215 ቤቶች ደግሞ ለልማት ተነሺዎች ተሰጥተዋል። በአጠቃላይ ከ139 ሺ በላይ በይደር የነበሩ የቤት ልማት ፕሮግራሞች ውስጥ 80 ሺ የሚሆኑት ቤቶች ለኅብረተሰቡ ተላልፈዋል። እነዚህ 80 ሺ ቤቶች ለነዋሪው ቢተላለፉም በግንባታቸው አለመጠናቀቅ ሰው መግባት አልቻለም። በቀጣይ ግን ሥራዎችን አጠናቆ ለማስረከብ እቅድ አለ።

ሥራው ስትራቴጂካዊ ሆኖ ለመመልከት የአሠራር ለውጥ ተደርጎም የቤቱ ችግር ምን ነበር የሚለው መታየት አለበት። ለችግሩ መነሻ ደግሞ ሆነው ኮንትራት የወሰዱት ድርጅቶች እቃ ወደ ማቅረብ ከገቡ በኋላ ችግሩ ለምን አልተፈታም የሚለው ነገር ትኩረት ተሰጥቶታል። በተደረገው ግምገማ ዋነኛው ነገር የፋይናንስ ችግር ነው። ፋይናንስ ከለውጡ በኋላም በቤቶች ኮርፖሬሽን ከፍተኛ ችግር ሆኗል። ፋይናንስ በአገርና በከተማ ደረጃ ቤቶችን መሠረት አድርጎ መደልደል አለበት። የተፈጠረውን ችግር ለመሻገር የግዴታ የፋይናንስ ጉዳይ መመለስ መቻል አለበት። በነባር ፕሮጀክቶች ላይ ይታይ የነበረውን የፋይናንስ እጥረት ለመፍታት ሥራዎችን በፕሮግራም መመራት ያስፈልጋል። ምክንያቱም አገሪቱ ባለችበት ነባራዊ ሁኔታ በፕሮግራም መመራት ካልተቻለ ግንባታዎቹን ማጠናቀቅ አይቻልም። ሁለት ሺ 222 ህንፃዎች በከተማ አስተዳደሩ ደረጃ ለመኖሪያነት እየተገነቡ ናቸው። ህንፃው ከመሬት ወለል አራት ተነስቶ እስከ አሥራ ስምንት የሚደርስ ግዙፍ ፕሮጀክት ነው። የነዚህን ግንባታ ቀሪ ሥራዎች ሊያጠናቅቅ የሚችል ፋይናንስ ያስፈልጋል።

ሌላው ቤቶቹ ለነዋሪዎች የተደለደሉ ቢሆንም ለማስረከብ መጠናቀቅ ያለባቸውን ሥራዎች ለመጨረስ ቅድሚያ ቀሪ ሥራዎቹ መታወቅ አለባቸው። ለዚህ ደግሞ ምን ያክል ገንዘብ እንደሚያስፈልግ እንዲጠና ተደረገ። በሳይትና የሕንፃው ሥራ በምን መልኩ መጠናቀቅ እንዳለበት ተለየ። በሕንፃው ሥራ በተለይ 40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ የአሳንሰርና ሌሎች የፊኒሺንግ ሥራዎች ለማጠናቀቅ እንዲሁም 20/80 የጋራ መኖሪያ ቤቶች የውሃ ፓምፕ ሌሎች ሥራዎች ለመጨረስ 19 ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ እንደሚያስፈልግ ታውቋል። ይህንን መሠረት በማድረግ በምን መልኩ በተያዘው በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ እቅድ ተቀመጠ።

ቤቶች ኮርፖሬሽን ከባንክ የተበደረውን ገንዘብ መክፈል ስላልቻለ ተጨማሪ የቦንድ ብድር መበደር አይችልም የሚል አቋም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ተይዞ ነበር። ይህን ሁኔታ ለመፍታት የረጅም ጊዜ ጥናት እንዲካሄድ ተደርጓል። አዲሱ የለውጥ አመራር ሲመጣ ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ተመድቦ ነበር። ይሄን ብር በምን መልኩ አብቃቅቶ ቤቶቹን መጨረስ ይቻላል የሚለው ውይይት በማድረግ ሥራ ተከናውኗል። በገንዘቡም 68 ሺ 490 ቤቶችን ለማጠናቀቅ እቅድ ተያዘ። ቤቶቹ ያሉበት ሁኔታ ምን ይመስላል፣ ምን ምን ሥራዎችን ይፈልጋሉ የሚሉትና ሌሎች ጉዳዮች ተለይተው ወደ ተግባር ተገብቷል።

በቀጣይ ዕትማችን ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ተሠሩ ሥራዎች በተመለከተ ይዘን እንቀርባለን።


ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «የቅራኔውን እርሻ የሚያርሱት ምሁራኑ ናቸው»

**- አቶ ማሞ አፈታ**
**የቀድሞ ሰራዊት አባልና ደራሲ**

ማህሌት አብዱል


ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ

**የዛሬው የዘመን እንግዳችን ምስራቅ ወለጋ ሆሮ ጉድሩ አውራጃ ጊዳ አያና ሲርበቡልቱም ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ነው የተወለዱት። እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ ጊዳ አያና ፤ ገሊሳ ፣ ሻምፖ በተባሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተምረዋል። ዘጠነኛ ክፍል ሲደርሱ ግን በአቅራቢያቸው ትምህርት ቤት ባለመኖሩ የሶስት ቀን የእግር መንገድ በምታስኬደው ሻምቡ ከተማ ለመሄድ ተገደዱ። ይሁንና ወላጅ እናታቸው የሚቋጥሩላቸውን እህል ጭነው እየተመላለሱ ቂጣ እየጋገሩ በብዙ መከራ ውስጥ መዝለቅ ከበዳቸው። በመሆኑም ትምህርታቸውን አቋርጠው አዲስ አበባ ለሥራ መጡ። እንዳሰቡት ግን ሥራ ማግኘት ባለመቻላቸው ወታደር ቤት ተመልምለው ተቀጠሩ። የውትድርና ስልጠናውን ባጠናቀቁ ማግስት ወደ ኤርትራ ተመድበው ለሁለት ዓመታት በጦር ሜዳ አሳለፉ። ይሁንና በሻቢያ ወታደሮች ተማርከው ሳህል በርሃ ውስጥ በእስር ለአምስት ዓመታት ቆዩ።**

**ለትምህርት ልዩ ፍቅር የነበራቸው እኚሁ እንግዳችን በወህኒ ቤትም ሆነ ከእስር ከተፈቱ በኋላ እንደእርሳቸው በምርኮ የሚኖሩ አግኝተዋል። በዚህ ብቻ አላበቁም፤ ከ15 ያላነሱና በትግርኛ የተፃፉ የመማሪያ መጽሐፍትን ወደ አማርኛ በመተርጎም ታሪካዊ ሥራ በመሥራት ኢትዮጵያውያን ከቀለም ትምህርት እስከ ፖለቲካ ድረስ በማስተማር ንቃተ ህሊናቸውን የማሳደግ ሥራ በራሣቸው ተነሣሽነት ሰርተዋል። ለሁለት ዓመታትም በምርኮ በሄዱባት አገር አካውንቲግ ሰልጥነው የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ነጥብ ማምጣታቸው ይጠቀሳል።**

**በምርኮ በቆዩባቸው 18 ዓመታት ከኤርትራውያን ጋር በፍቅርና በሰላም የኖሩት እኚሁ ሰው አንዲት ኤርትራዊ ወታደር አግብተው አራት ልጆችን አፍርተዋል። ቤተሰባቸውን ይዘው ወደ እናት አገራቸው ከተመለሱ በኋላ የሚወዱትን ትምህርታቸውን በመቀጠል ከአልፋ ዩኒቨርሲቲ በአካውንቲንግ ዲፕሎማ ማግኘት ችለዋል።**

**እንግዳችን ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር ሬዲዮ ፋና ኦሮምኛ ፕሮግራም ላይ ከፍተኛ አዘጋጅ ሆነው ከመስራት ጀምሮ በተለያዩ ተቋማት እየተዘዋወሩ አገልግለዋል። በተለይም ሬዲዮ ፋና በነበሩበት ወቅት አጫጭር ድራማዎችን በመፃፍ ከፍተኛ እውቅና ማግኘት ችለውም ነበር። አሁን ደግሞ በገምሹ በየነ ህንፃ ተቋራጭ ድርጅት ውስጥ የሰውኃይል አስተዳደር ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ። በቅርቡ በኤርትራ በርሃ በምርኮ ያሳለፉትን ውጣ ውረድና በአጠቃላይ የሁለቱን አገራት ህዝቦች ግንኙነት የሚዳስስ «አንቱ በእናት»የተሰኘ መጽሐፍ ለንባብ አብቅተዋል። በዚህ መጽሐፍና በሌሎች አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከአቶ ማሞ አፈታ ጋር ያደረግነውን ቃለምልልስ እንዲህ አሰናድተናል።**

**አዲስ ዘመን፡- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በሚማሩበት ወቅት የተለየ ገጠመኝ እንደነበሮት ሰምተናል። እስቲ ስለዚህ ገጠመኝ ያስታውሱንና ውይይታችን እንጀምር?**

**አቶ ማሞ፡-** የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ ሳለን እኔና ጓደኛዬ በወቅቱ በትምህርታቸው ጎበዝ ከሚባሉ ተማሪዎች መካከል አንዱ ስለነበርን በአንድ ዓመት አምስተኛንና ስድስተኛ ክፍልን ለመማር ጥያቄ አቅርበን ነበር። ሆኖም ይህ «ደብል ፕሮሞሽን» የተባለው ስርዓት በዚያ ትምህርት ቤት ስለማይሰጥ ጥያቄያችን ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። በመሆኑ ሌላ ሊሙ በተባለ ወረዳ ውስጥ በሚገኝ ገሊላ በተሰኘ ትምህርት ቤት ለመማር አመለከትን። ይሁንና የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር እኔ ከነበርኩበት ትምህርት ቤት ጋር ክስ ላይ ስለነበሩ አናስገባም ብለው ብዙ አጉላሉን። እኛ ግን ተስፋ ሳንቆርጥ የግል መኖሪያ ቤታቸው ድረስ እየተመላለስን ጭቅጨቃችንን ቀጠልን።

ከብዙ መመላለስ በኋላ ግን አንድ ቀን በአጋጣሚ ከተማ መሃል ላይ አንድ ባላባት የሆኑ አጎቴ መጥተው ተገናኘን። የሚገርመው ቆመን ከእሳቸው ጋር እያወራን የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር በአጠገባችን አለፉ። በዛ ጊዜ ወደ እርሳቸው እየጠቆምኩኝ ያደረጉኝን ሁሉ ለባላባቱ ዘመዴ ወቀሳ አቀረብኩኝ። እርሳቸውም ደግሞ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ይፈሩና ይከበሩ ስለነበር የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ከእርሳቸው ጋር ሲያዩን ተደናገጡ። እርሳቸውም ጠርተውት እኔንም ሆነ ጓደኛዬን እንዲመዘገቡን ትዕዛዝ ሰጡልንና ከሳምንታት መንከራተት በኋላ መመዝገብ ቻልን። ነገር ግን ያን ቀን ባይመዘግቡን ኖሮ እኔና ያ ጓደኛዬ እቅዳችን ወደ አባይ ተሻግረን ጎጃም ልንጠፋ ነበር። ምክንያቱም ከመጀመሪያው ትምህርት ቤት መልቀቂያ አስገብተን ደብዳቤ ተሰጥቶን ስለመጣን መመለስ አንችልም ነበር። ሌላው የጓደኞቻችን መሳቂያ እንሆናለን የሚል ስጋት ስለነበር ወደማናውቀው አገር ለመጥፋት አስበን ነበር። ግን ተፈቀደለንና እንዳሰብነው በአንድ ዓመት ውስጥ አምስተኛና ስደስተኛ ክፍል ማለፍ ቻልን።

ይሁንና በአቅራቢያችን ሰባተኛ ክፍል ባለመኖሩ ሶስት ቀን በእግር በሚፈጀው የሆረጉድሩ አውራጃ ዋና ከተማ በሆነው ሻምቡ ድረስ ሄዶ መማር ግድ ሆነብን። የምንማረው ከቤተሰብ ርቀን ቤት ተከራይተን ቂጣ እየጋገርን ነበር ። እህል የሚጫነው ከወላጆቻችን ነው ። የእኔ ደግሞ ወላጆች ተለያየተው ስለነበር እኔ ከእናቴ ጋር ሆንኩኝ። አባቴ ሌላ ሚስት አግብቷል። ስለዚህ እናቴ ለእኔ ቀለብ እየጫነች ለማስተማር በጣም ተቸገረች። የምታስተምረኝ ብዙ ጊዜ ሰው እየለመነች፤ እምቢ ሲሏት እያለቀሰች ነበር ። ለእኔ ይህንን ለመቀበል በጣም ከባድ ሆነብኝ። እናቴን ለመርዳት ስል ስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ለመውሰድ ሁሉንም ዝግጅት ካጠናቀቅኩኝ በኋላ ሁለት ወር ሲቀረኝ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ፖሊስነት ለመቀጠር ወደ ነቀምቴ ተያይዘን ጠፋን።

ስንደርስ ምዝገባው ከአንድ ቀን በፊት መጠናቀቁን ሰማን። በዚህም ምክንያት ዳግመኛ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ነውር ሆኖ ተሰማን። ጓደኛዬ ተስፋ ቆርጦ ወደ አገሩ ለመመለስና ቡና ለመትከል ወሰነ። ለጓደኛዬ እኔ ግን ወደ ገጠር ተመልሼ ከእኔ ኋላ ላሉ ልጆች ተስፋ እንዲቆርጡ ምክንያት አልሆንም ብዬ እንደማልመለስ ነገርኩት። እናም አንገር ጉትን በተባለ የሆላንዶች እርሻ ልማት ወዛደር ሆኜ ተቀጠርኩኝ። እስከ ሰኔ ድረስ በቁፈራ ሥራ ቆየሁ። ሰኔ ላይ የፈተና ወቅት ሲደርስ ማልቀስ ጀመርኩኝ። የሚገርምሽ እዛ የሚቀጠረው ባለትዳር ብቻ ነበር፤ እኔም የተቀጠርኩት ቡቱቱ ለብሼ ባለትዳር ነኝ ብዬ ነበር። አንድ ቀን ቁጭ ብዬ ሳለቅስ የሚያሰራን ካቦ አየኝና ምን ሆኜ እንደሆነ ጠየቀኝ። አንድ ባልደረባዬ ተማሪ መሆኔና የሚኒስትሪ መውሰጃ ጊዜ ስለደረሰ እንደማለቅስ ነገረው። ዋናው ሥራ አስኪያጅ አስፈቅዶልኝ ተፈተንኩ።

የሚገርመው ያንን ፈተና ለመፈተን በጣም የሚያስፈራውን እና ዘወትር በማዕበል የሚናወጠውን አንገር የተባለውን ወንዝ በዋና ለማቋረጥ ተገድጄ ነበር። ሁለት ጊዜ ለሞት አፋፍ ደርሼ የነበረ ቢሆንም፤ ከሌላው እኩል ቁጭ ብዬ ለመፈተን የበቃሁት ትምህርቴን ለመቀጠል ከፍተኛ ቁጭትና እልህ ስለነበረኝ በፅናት ከማዕበሉ ጋር ተፋልሜ ነበር። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ በዚያው ሰሞን ወባ በሽታ ይዞኝ ሁለት ቀን ተኝቼ ነበር ሄጄ የተፈተንኩት። ግን በጣም ጎበዝ ተማሪ ስለነበርኩኝ በዚያ ውጣ ውረድ ውስጥ ባልፍም ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ወደ ዘጠነኛ ክፍል ተሸጋገርኩ።

**አዲስ ዘመን፡- እንደዚያ ዋጋ የከፈሉለት ትምህርትዎን አቋርጠው ደግሞ ወደ ውትድርና ገብተውም ነበር። ወደ ውትድርና የገቡበት ምክንያት ምን ነበር?**

**አቶ ማሞ፡-** እንዳልኩሽ በነበረብኝ የኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ዘጠነኛ ክፍል ከገባሁኝ በኋላ መቀጠል የበለጠ ከባድ እየሆነብኝ መጣ። በተለይም እናቴን እያሰቃየሁ መኖር አልፈለኩም ነበር። እየሰራሁኝ ለመማር ስል የተላከልኝን እህል ሽጬ ወደ አዲስ አበባ ኮበለልኩኝ። አንድ የአክስቴ ልጅ ጋር ባርፍም እርሱም ተማሪ ስለነበር ያለሥራ እዛ መቆየት ከባድ ሆነብኝ። የገጠሩ ባህል ገና ያለቀቀኝ በመሆኑ እንዳሰብኩት ቶሎ ሥራ ለማግኘትና ለመማር አልቻልኩም።

በመጨረሻ ከዘመዴ ጋር ተማክረን ለውትድርና ለመመልመልና ለመቀጠር ወሰንኩኝ። የሚገርመው ልክ እኔ እንደተመዘገብኩኝ ምልመላው ተጠናቀቀ። ደብረብርሃን ላይ ስድስት ወር ከሰለጠንኩኝ በኋላ አስመራ ተመድቤ ስለነበር አንድ ሌሊት ብቻ አዲስ አበባ አድረን በአውሮፕላን በቀጥታ ወደ አስመራ ሄድኩኝ። ሁለት ዓመት ካገለገልኩኝ በኋላ በ1969 ዓ.ም አፋቤት የሚባለው ካምፕ ሲደመሰስ ከ165 ሰዎች ጋር ተማረኩኝ። ከዚያ ጊዜ ወዲህ ለ18 ዓመታት ኑሮዬ ከሻቢያዎች ጋር ሆነ።

ለአምስት ዓመታት እስር ቤት ቆይቻለሁ። ቀሪውን ጊዜ ያሳለፍኩት እንደማንኛውም ሰው ከጠመንጃ አፈሙዝ ጥበቃ ውጭ ነው። በእስር ቤት ቆይታችንም ቢሆን የተለያዩ ሥራዎችን እንሰራ ነበር። ከጉልበት ሥራ በተጨማሪ እርስ በእርስ የቀለም ትምህርት እንዲሁም የፖለቲካ ትምህርት እንማማር ነበር። በዚህ ምክንያት እስር ቤቱ ለእኛ በሚያስደንቅ ሁኔታ የሆነልን እንደ ኮሌጅ ነበር። በኢትዮጵያ መንግሥት ወንበዴና መቀነት በጣሽ የሚባለውን የሻቢያን ታጋይ ቡድን ለመግደል ሄደን የጠበቀን መስተንግዶ የሚገርም ነበር። እኛ አዕምሮ ላይ የተቀረፀው ከአረቦች ጋር ያበረ እና ወንበዴ ቡድን ነው የሚለው አስተሳሰብ ነበር ። እኛ እንዳውም ስንሰለጥን ጀምሮ እንፎክር የነበረው «ምንአለ ደርጉ ምን አለ፤ አገሬን ለአረብ አልሰጥም አለ፤ ኤርትራን ለአረብ አልሰጥም አለ» እያልን ነበር። የደርግ ስርዓት እስከወደቀበት ጊዜ ድረስ «የኤርትራ ወንበዴዎች» የሚል ስያሜ ነበር የሰጣቸው። እንደአንድ ትልቅና በዲሲፕሊን የሚመራ ድርጅት ተደርጎ አይቆጠርም ነበር።

ያገኘነው ግን በተቃራኒው ሆኖ ነው። እኛ ልንገድላቸው ሄደን በእጃቸው ላይ ስንወድቅ ሊገድሉን ሲችሉ፤ አላደረጉትም። የወንድማቸውን ሬሳ አስቀምጠው እኛን «እንኳን ፈጣሪ አተረፋችሁ» አሉን። እኛም በሕይወት ያቆዩናል የሚል እምነት አልነበረንም። እንደውም ለተወሰነ ጊዜ እንጠራጠራቸው ነበር። እነሱ ግን ከጭቁን ኢትዮጵያውያን ጋር ምንም አይነት የጠላትነት ስሜት እንደሌላቸው ደጋግመው ይነግሩን ነበር። ነፃነታቸውን ብቻ የሚፈልጉ ስለመሆናቸው ይነግሩን ነበር። ያንን ሁሉ ዓመት ያቆዩንቃላቸውን አክብረው ነው። ከ10 ሺዎች በላይ ኢትዮጵያውያን ምርኮኞችን ያስተናገዱት በዚህ መልክ ነው። በጊዜ ሂደት ምርኮኛው እየባዛ ሄዶ የሳህል በርሃ የአማርኛ ተናጋሪዎች መንደር ወደ መሆን ሄዶ ነበር።

የሚገርመው ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት አንድም ምርኮኛ የለኝም ብሎ ክዶን ነበር። ስለዚህ የእኛ እጣፈንታ የወደቀው በፈጣሪና በኤርትራ ታጋዮች እጅ ነበር። ቤተሰቦቻችን ሳይቀር በጦር ሜዳ እንደሞትን ተረድተው እርማቸውን አውጥተው ነበር። እኛ ግን በዚያ በርሃ የኖርነው የህዝባችን ናፍቆት እያቃጠለን ነበር። በዚያ ላይ እነሱም ትግል ላይ ስለነበሩ ለእኛ በቂ ምግብ ማቅረብ አይችሉም ነበር። የምንበላው የጫካ ጎመን ነበር ። ስለዚህ ከረሃቡ ባሻገር ወባ፤ ታይፎይድና መሰል በሽታዎች በተደጋጋሚ እንጠቃ ነበር። ብዙ መከራና ውጣ ውረድ አሳልፈናል። እንዲያም ሆኖ በሕይወት ቆይተን ዛሬ እንደታሪክ ለማውራት በመብቃታችን ፈጣሪዬን ላመሰግን እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ምርከኞችን የቀለምና የፖለቲካ ትምህርት ወደ ማሰልጠን ገብተውም እንደነበር ይታወቃል፤ እስቲ ይህ አጋጣሚ እንዴት እንደተፈጠረ ያስታውሱን?**

**አቶ ማሞ፡-** እንዳልኩሽ እነሱ ነፃነታቸውን ከመፈለግ ውጭ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር የጠላትነት ስሜት እንደሌላቸው በተግባር አሳይተውናል። በጣም የሚገርመው «ዳግመኛ እንኳን ተማርከን ብንሄድ ይዘን እናስተምራችኋለን እንጂ አንገላችሁም» ይሉን ነበር። እንዳሉትም ተመሳሳይ እጣ የገጠማቸውን ሰዎች በፍቅር ተቀብለው አኑረዋቸዋል። እዛም ሆነው «ኤርትራ መገንጠል የለባትም!» ብለው ሽንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩ ነበሩ። ይህንን በማለቱ ጥቃት የሚደርስበት የለም። ከአምስት ዓመት እስር በኋላ መጀመሪያ ላይ የተማረክነው ሰዎች በነፃ ተለቀቅን። ይህም ማለት ያልታጠቀ፤ በጠመንጃ አፈሙዝ የማይጠበቅ ማለት ነው። እንቅስቃሴያችን በዲሲሊን ስር ያለ ቢሆንም ዝም ብሎ መሄድ አይቻልም።

ለእስረኞች ከቀለም ትምህርቱ ጎን ለጎን የፖለቲካ ትምህርት አስተምር ነበር። በነገራችን ላይ ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ መማር አለብን ብዬ ጠፍጣፋ ድንጋይ ከወንዝ አምጥቼ፤ ባትሪ ድንጋይ ከታጋዮች ለምኜ ፊደላትን በመፃፍ ያልተማሩ ምርኮኛ ወገኖቼን በጋዛ ፍቃዴ አስተምር ነበር። እነሱም የሚፅፉበት ወረቀት ስላልነበር ሰፋፊ ቅጠል በጥሰን እንደ ደብተር፤ አፈርን በጥብጠን ደግሞ እንደብዕር እንጠቀም ነበር። የቤት ሥራቸውን የሚሰሩት ቅጠል ላይ ነበር። ብዙዎቹ ግን ይነቅፉኝና ያሾፉብኝ ነበር። እኔ በዚህ ተስፋ አልቆረጥኩም፤ እንዳውም በዚህ መልኩ የተጀመረው ትምህርት እየሰፋ ሄደ። ከፊደል አልፈው ቃላት ማንበብ ሲጀመር ግን ችግር

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

ሆነብን። በኋላ ላይ ድርጅቱ የውጭ ሚዲያዎች ጋብዞ በቪዲዮ እንዲቀረፅ በማድረጉ በዓለምአቀፍ ቀይመስቀል መታወቅ ጀመርን።

በዚህ ምክንያት የዱቄት ወተት መጣልን። ወተቱን ከጠጣን በኋላ የታሸገበትን ወረቀት ሰፍተን እንደደብተር መጠቀም ጀመርን። ከዚያ ደግሞ ከቃላት አልፈው አጫጭር ታሪኮችንና መግለጫዎችን እየፃፍኩኝ እንዲያነቡ አደርግ ነበር። ያቺን አጭር መግለጫ ደጋግመው ከማፃፌ የተነሳ ያልደረሰችው ሰዎች ጥቂት ነበሩ። ተማሪው ቁጥሩ እየበዛ በሄደ ቁጥር ግን መጽሐፍ ማግኘት የግድ ሆነብን። ስለሆነም ከትግርኛ መጽሐፍ ጋር መታገል ያዝኩኝ።

የትግርኛ መጽሐፍ ከታጋዮቹ እየተዋስኩኝ እየተተረጎምኩኝ ማቅረብ ጀመርኩኝ። ከዚህ በመነሳት በርካታ መማሪያ መጽሐፍቶችን ተርጉሜ ለህትመት አብቅቻለሁኝ። የድርጅቱ ታዋቂነት በዓለም ላይ እየጎላ ሲመጣ የምርከኞችም ታዋቂነት በዚያው ልክ ጨመረ። በዚህ ምክንያት በዓለም ቀይ መስቀል ማህበር አማካኝነት አልባሳትና ደብተር በገፍ መጣልን። ከዚያ በኋላ የወተት ወረቀቱን መጠቀም አቆመ። በፊት ሲያሾፉብኝ የነበሩ ሰዎች ራሳቸው መማር ጀመሩ።

ፊደል ከመቁጠር የጀመሩ ሰዎች ደግሞ ሰባተኛ ክፍል ደረሱ። ከዚያም አልፈው ግጥምና ድረሰትም የሚፅፉ ነበሩ። እኔ ብቻዬን እንኳን 15 መጽሐፍትን ተርጉሜያለሁ። በሌላ በኩል በምርኮ የሄድን ሁሉ ስንተሳሰብ የነበረው እንደአንድ ሆነን ነው። ይህም እዚህ አሁን እርስ በርስ የምንገዳደልበትን የጎሳ ልዩነት አጥፍተን ትንሿን ኢትዮጵያ መስርተን ነበር ማለት ይቻላል። አንዳንዴ እንደውም የምንመኛትን ኢትዮጵያ ለመገንባት መማረክ ይኖርብናል እንዴ? እያልኩኝ ራሴን እጠይቃለሁኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ምንአልባት ሁላችሁም በችግር ውስጥ በባዕድ መካከል መሆናችሁ ይሆን አንድ ያደረጋችሁ?**

**አቶ ማሞ፡-** በዚህ ምክንያት አይመስለኝም። ሲጀመር እንደተናገርኩት ሻቢያዎቹ ምንም እንኳን የአመለካከት ልዩነት ቢኖረንም ያደረሱብን ጉዳትና ጫና አልነበረም። በሌላ በኩል ደግሞ ሁላችንም ኢትዮጵያኖች በፍቅርና በመከባበር ለመኖር ወሰነን ይህንንም በመተግበራችን ይመስለኛል ህብረታችንን ያጠናከረው። በነገራችን ላይ አሁንም ድረስ በርሃ አብረን ከነበሩት ጓደኞቼ ያለን ግንኙነት ጥብቅ ነው። ለእኔ እንደውም ከዘመድ በላይ የሚረዱን የበርሃ ጓዶቼ ናቸው ብዬ አምናለሁ። ደግሞም ውስጣችን የገባው ንቃተ-ህሊና ለየት ያለ ስለሆነ እንደሆነም እረዳለሁ።


ኤርትራውያን እዛ በርሃ ላይ ለየት ያለ ትውልድ ፈጥረዋል። ከህዝብ አስተሳሰብ ወጣ ያለ ግንኙነት፤ እርስ በርስ መተሳሰብ፤ መከባበር፤ የሴቶች እኩልነት የተረጋገጠበት ነበር። በዲሲፕሊን የታነፀ ሰራዊት ነበረ፤ በዚያ ላይ በሂስና ግለሂስ የምንወቃቀስበት መድረክ መኖሩ ራሳችንን ለማረቅና በትክክለኛው መንገድ እንድንቀረፅ አድርጎናል ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በምርኮ በተሰደዱበት አገር ደግሞ ትዳር መስርተው ልጆችም አፍርተዋል፤ ይህ እንዴት ሲሆን ቻለ?**

**አቶ ማሞ፡-** ነፃ ከተለቀቅኩኝ በኋላ በሥራ አጋጣሚ ከአሁኗ ባለቤቴ ጋር የመተዋወቅ እድል ገጥሞኝ ነበር። እሷ ታጋይ ነበረች፤ እኔ ደግሞ ምርኮኛ። ፍቅር ስንጀምር ግን እኔ ከእስር ተፈትቼ ነፃ ሰው ነበርኩኝ። የምኖረው ከብዙሃኑ ጋር ተዋህደን ነበር። ብዙዎች የማደርገውን ጥረት ያደንቃሉ፤ እሷ ግን ከሌላው በተለየ ታበረታታኝ ነበር። ቀስ በቀስ ግን ቅርበታችን ወደ ፍቅር ተለወጠ። እኔ በወቅቱ አፍር ነበር፤ ምክንያቱም አንደኛ እኔ በእነሱ እጅ የወደኩኝ ምርኮኛ መሆኔና እሷ ታጣቂ ሆና ሳለ ግንኙነታችን በዚህ መልክ መቀየሩ ያስፈራኝ ነበር። ሁለተኛ ህብረተሰቡ ራሱ አይቀበለንም የሚል ስጋት ነበረኝ።

የታጋዮቹ ንቃተ-ህሊና ከፍተኛ ነው። ብዙዎቹ ታጋዮች እሷን ጨምሮ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ጠላት አይደለንም የሚለው አመለካከት ይዘው ነበር። አንዳንድ ጠማማ አስተሳሰብ የነበራቸውም ነበሩ። ሊያስፈራሯት የሚሞክሩ፤ በጥላቻ የሚያዩን ነበሩ። እንዴት ጠላት ከነበረ ጋር ትወግኚያለሽ? ብለው የሚሞግቷት ነበሩ። እሷ ግን ይህንን ሁሉ ዛቻና ማስፈራሪያ ከምንም አልቆጠረችውም። «እኔ ያፈቀርኩት የሰውን ልጅ ነው ፤ ድርጅቴ የህንን አስተሳሰብ ቀይሮታል፤ ግንኙነታችንን እስከተቀበለው ድረስ ማንም ሊያግደኝ አይችልም» አለች። ምክንያቱም በወቅቱ የሴቶች መብት ሻቢያ ውስጥ የተከበረ ነው። ስለዚህ መብቷን ተጠቅማ ግንኙነታችንን ቀጠለን። ግን ደግሞ ግንኙነታችን የቀጠለውበዲሲፕሊኑ መሰረት በማመልከቻ ለድርጅቱ ፈቃድ ጠይቀን ነው ።

ከሁለት ዓመት የእጮኝነት ጊዜ በኋላ የፖለቲካ ድርጅቱ ራሱ ሞቅ ያለ ሠርግ ደግሶ 36 ጥንዶች ጋር በአንድ ቀን ዳረን። ከእዚያ ሁሉ ውስጥ ግን ኢትዮጵያዊው እኔ ብቻ



ነበርኩኝ ። በሰርጋችን ላይ ደግሞ ከከፍተኛ ባለስልጣናት ጀምሮ ፤ በርካታ ምርኮኞችና ተፈናቃዮች በሙሉ ታድመውበታል። በሠርጉ ላይ የታደሙት አንድ ከፍተኛ ባለስልጣን በህዝባዊ ሃርነት ኤርትራ ታሪክ ውስጥ በዚህ ያህል መጠን ሰዎች የተጋቡበት ትልቅ ሰርግ መሆኑና ከሁሉ በላይ ሰርጉን ታሪካዊ የሚያደርገው ኢትዮጵያዊ ምርኮኛ ኤርትራዊ ታጋይ መጋባታቸው መሆኑንና ድርጅታቸው በዚህ ታሪክ እንደሚኮራ ተናግረዋል።

አንድ ሊገድል የመጣ ወታደር ማርኮ፤ አስተምሮ፤ ንቃተ ህሊናውን አሳድጎ፤ አመለካከቱን ቀይሮ ከወገናችን ጋር መቀላቀሉ ድርጅቱ የሚኮራበት መሆኑንም ገልፀዋል። ህዝቡም የዳረን ቆሞ አጨብጭቦ ነበር። የተጋባነው ናቅፋ በምትባል ታሪካዊ ቦታ ላይ ነው። ከዚያ በኋላ በርሃ ላይ ሁለት ልጆች አፈርተን ነበር፤ ደርግ ወድቆ አስመራ ከገባን በኋላ ደግሞ አንዴት ሴት ልጅ ወልደን፤ ቤተሰቤን ይዤ ወደ አገሬ ከገባሁኝ በኋላም ተጨማሪ ሴት ልጅ ወለደን።

**አዲስ ዘመን፡- የእርሶና የባለቤትዎ ታሪክ ለሁለቱ ህዝቦች አንድነት ማሳያ ነው ማለት አንችልም?**

**አቶ ማሞ፡-** እንዳልሽው በጦርነት ታሪክ ውስጥ በፍቅር የተጣመርን ከጥቂቶቹ አንዱ ብንሆንም፤ ብዙዎች ከዚያም በፊትም ሆነ በኋላ ተጋብተው ተዋልደዋል። ይህም የሁለቱን አገራት ህዝቦች ግንኙነት የበለጠ እንዳጠናከረው አምናለሁ። በነገራችን ላይ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ጥላቻ እንደሌላቸው በደንብ ያውቃሉ። አሁን በደንብ ያልተነገረው የሚመስለኝ በኢትዮጵያ በኩል ነው። እነሱ ለነፃነታቸው የታገሉበት ትክክለኛ ምክንያት በእኛ በኩል ይታወቃል ብዬ አላስብም። ከዚህ ጋር ተያይዞ በደንብ ያልተነገረ የሚመስለኝ ስለኢትዮጵያ ሰራዊት ጀግንነት ነው። በወቅቱ ሰራዊቱ አቅም ስላልነበረው የተሸነፈ እንደሆነ የሚያስቡ ብዙዎቹ ናቸው። እውነታው ግን ይህ አልነበረም። ሰራዊቱ ከየትኛውም ኃይል የላቀ አቅምና ብቃት እንዲሁም ወኔ የነበረው ነው። ኤርትራውያን ራሳቸው ይመሰክሩለታል። ወታደራዊ ሳይንስን አኝከው የበሉ መኮንኖች የነበሩት ሰራዊት ነው። የተሸነፉበት ራሱን የቻለ ፖለቲካዊ ምክንያት እንዳለው እሙን ነው።

ከዚያ ባሻገር ኤርትራውያን በንጉሱ ጊዜ ነፃ ሆነው የኖሩበት ታሪክ ተገልብጦ ለአረቦች አሳልፎ ለመስጠት ተደርጎ ይወራ የነበረውም ፈፅሞ ከእውነት የራቀ ነበር። ኤርትራ የአፍሪካ አገራት በአውሮፓውያን ሲቃረጡ አገር ሆና ተመስርታለች። አሁን ይህንን ታሪክ የኢትዮጵያ ህዝብ በብዛት አያውቅም። ከዚያ በኋላ ደግሞ በ1945 ዓ.ም ከእናት አገሯ ጋር በፌዴሬሽን ተቀላቀለች። ይህንን የነፃነታቸውን ታሪክ መቀበል ብዙዎቻችን አንፈልግም። እኔ ለአገሬ አንድነት ብታገልም እዛ በኖርኩበት ጊዜ የኤርትራውያን ስነልቦና በደንብ ተረድቻለሁ። እንዳልኩት ለእኛ ምንም አይነት ጥላቻ የላቸውም፤ ግን ደግሞ ነፃነታቸውን እንድናከብርላቸውም ይፈልጋሉ። ስለዚህ እኛ ባይዋጥልንም፤ ሁለት አገራት ከሌሎች የአፍሪካ አገራት በተለየ የሚያቀራርባቸው የሚያመሳስላቸው ብዙ ነገር ቢኖራቸውም ጎረቤት መሆናቸው እሙን ነው።

ግንኙነታችንን ማጠናከር የምንችለው ሉዓላዊነታቸውን አክብረን በሰላምና በፍቅር ስንኖር ነው። እንደጎረቤት አገራት የንግድ ልውጥ ማድረግ፤ ማዳበር ያለብን የባህር ወደቦችን በጋራ የመጠቀም ልምድ ነው። ምክንያቱም ከየትኛውም ባህር በላይ ቀይባህር ለእኛ ይቀርበናል። በመሆኑም በሁለቱ አገራት መካከል የተዘራውን ጥላቻ እንዴት ማስወገድ እንደምንችል መወያየት አለብን። በተለይም የሁለቱም አገራት ምሁራን ተቀራርበው መወያየት አለባቸው። በነገራችን ላይ በቅርቡ ለንባብ ያበቃሁት «አንቱ በእናት» የተባለው መጽሐፍ ሙሉ ታሪኩ የሚያጠነጥነው በእኔ የሕይወት ታሪክ ላይ ቢሆንም ስለሁለቱ ህዝቦች ጠንካራ ግንኙነት የሚዳስስ ነው። ይህ መጽሐፍ አሁንም የሁለቱ አገራትን ህዝቦች ይበልጥ እንዲቀራረቡ ያግዛል ብዬ አምናሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ወደ አገርዎ የተመለሱበትን አጋጣሚ ያስታውሱንና ከተመለሱ በኋላ ደግሞ የሁለቱ አገራት ግንኙነት ወደ ጦርነት ማምራቱ የፈጠረበትን ስሜት ያስረዱን?**

**አቶ ማሞ፡-** በመሰረቱ እኔ ከአገሬ ርቄ የኖርኩት ህዝቤንና አገሬን ጠልቼ አልነበረም፣ ተገድጄ እንጂ! በሌላ በኩል ለእናቴ አንድ ልጅ እንደመሆኔ ለእናቴ መኖር ነበረብኝ። ወደ አገሬ የተመለስኩት ህዝቡም ደግሞ በጣም ናፍቆኝ ስለነበር ነው ። ከምንም በላይ ደግሞ 18 ዓመት ሙሉ «ልጄ ሞቷል» ብላ ስታለቅስ የኖረችውን እናቴን በእድሜ እየገፋችና እየደከመች በመምጣቷ መደገፍና መንከባከብ ስላለብኝ ነው የመጣሁት። እኔ በሕይወት ስለመኖሬ እናቴም ሆነች ሌላው የቤተሰብ አካል አያውቅም ነበር። እዚህ ስመጣም አዲስ አበባን በቅጡ ስለማላውቅ ወደ ወለጋ የሄድኩት አንድ ሌሊት አድሬ ነው ።

መኪና ውስጥ ሆኜ እጅግ በጣም የምወዳት እናቴ ሞታ ብትቆየኝ ምን አደርጋለሁ የሚል ጥያቄና ስጋት ተፈጥሮብኝ ነበር። እዛ ከደረስኩኝ በኋላ ደግሞ ቤታችን ጠፋኝ። ምክንያቱም በከተሞች መስፋፋት ዳር የነበረው መሃል ሆኗል። ቤታችን ፊት የነበረው ፖሊስ ጣቢያ ፈርሶ መናሃሪያ ሆኗል። እንግዳ መሆኔን የተረዳች አንዲት ልጅ ጠይቄ ቤቱን ካሳየችኝ በኋላ ግን ዘው ብዬ ድንገት ብገባ እናቴ በድንጋጤ ትሞትብኛለች ብዬ ሰጋሁ። ብዙዎቹ ጓዶቼ እንደእኔ ቆይተው ሲመለሱ በድንጋጤ የሞቱባቸው መኖራቸውን ስለሰማሁ ወደ ቤት የገባሁት በጥንቃቄ ሌላ ሰው መስዬ ነው። እናቴ ስታየኝም አላወቀችኝም፤ እኔም የልጇ ጓደኛ መሆኔን እንጂ ልጇ መሆኔን አልነገርኳትም። ምክንያቱም የእኔ ዋና አላማ በሕይወት መኖሯን ማወቅና ስትረጋጋ ማንነቴን መንገር ብቻ ነው። ጓደኛው ነኝ ብዬ ነግሪያት እንኳን በጣም አለቀሰች። በኋላ ከሰዎች ጠይቄ እንደተረዳሁት በሄደችበት ሁሉ ስሜ ሲጠራ ስታለቅስ ነው የኖረችው። ደግሞም እኔ ብቻ ሳልሆን ብዙዎቹ ሞተዋል ተብለው ተስካራቸው ተበልቷል።

የኋለኛው ጦርነት ለእኔ እጅግ አሳዛኝ ነበር። ምክንያቱም እዛም እዚህም ለኖረ ፤ ለተዋለደ ሰው ህመሙ ከባድ ነው። ያንን ሁሉ ዓመታት በጦርነት መቆየታችን አልበቃ ብሎ እንደገና አዲሱ ትውልድ እንዲያልቅ መደረጉ ያሳዝናል። እውነቴን ነው በዚህ ደረጃ ደም መቃባታችን አሁንም ድረስ የሚፈጥርብኝ ትልቅ ቁስል ነው። ምክንያቱም ልዩነቶች ቢኖሩም በሰላም መፍታት የሚቻልበት እድል ነበር። ይህንን ደግሞ ከለውጡ መምጣት ጋር ተያይዞ እንደሚቻል አይተናል። በዚህ ረገድ ዶክተር ዐቢይ በሁለቱ አገራት መካከል እርቅና ሰላም እንዲወርድ ላደረጉት ጥረት ላመሰግናቸው እወዳለሁ። በፊትም ይቻል ነበር።

በተለይም የኤርትራውያንን ስነልቦና ስለማውቅ ለእርቅ በራቸውን ማንኳኳት ከባድ አልነበረም። ለፍቅር ልባቸውን የከፈቱ መሪ መጡና የዘመናት ቁጭታችንን ፈቱልን። ተነፋፍቆ የኖረን ማህበረሰብ እምባ ጠረጉ። ኤርትራውያን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚያ መንገድ የተቀበሏቸው ለዚህ ነው ። ያ ፍቅር እኛ ለዓመታት ያየነው እንጂ አዲሳችን አይደለም። ግን ደግሞ የጥላቻ ግድግዳ ፈርሶ እንደአንድ ህዝብ መኖራቸው ለእኔ ዳግም እንደመወለድ እቆጥረዋለሁ። አሁንም ይህንን ግንኙነት ማጠናከር ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ ጎሳን፤ ቋንቋንና ሃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች መበራከታቸው ከምን የመነጨ ነው ብለው ያምናሉ? መፍትሄውስ?**

**አቶ ማሞ፡-** አስቀድሜ እንዳልኩት አንድነት ለመፍጠር ፍቅር ያስፈልጋል። ፍቅር ደግሞ ከንቃተ ህሊና ጋር ይሄዳል። አንዱ መሰረታዊ ችግር ብዬ የማምነው የማህበረሰቡን ንቃተ-ህሊና ማሳደግ ያለመቻሉ ነው። ያወቅን እየመሰለን መድረኮችን እየዘለልን ሄድን እንጂ ብዙ ያላወቅነው ነገር አለ። ዓለም አሁን ወደ አንድ መንደር በመጣበት ጊዜ እኛ በሰበብ በአስባቡ እርስበርስ እየተገዳደልን በመሆናችን በእውነት ከልብ ያሳዝናል። ከግድያ ምንም አይገኝም። ከግድያ ምንም የማይገኝ መሆኑን፤ ታግሶ ማለፍንና ሆደ ሰፊ መሆኑን ከኤርትራውያን መማር እንችላለን። እንዳልኩሽ እንደእኔ አይነቱን ገዳዮቻቸውን በፍቅር ተቀብለው ማኖር የሚችሉ ሰዎች መሆናቸውን በሕይወት ያለሁ ምስክራቸው ነኝ። እኛ ደግሞ ከእነሱ በላይ አንድ የሚያደርጉን ነገሮች በመኖራቸው እርስ በርስ መከባበርና መፈቃቀድ አለብን። ስለዚህ ለግጭት መነሳትም ሆነ መባባስ ተጠያቂ የማደርገው ምሁራኑን ነው።

ለምሳሌ አንድ ገበሬ አማራና ገበሬ ኦሮሞ ፊት ለፊት አስቀምጠው እረሱ ብትያቸው አብረው ሰርተው በጋራ ለመብላት እያናቸውን አያሹም። አይገዳደሉም። ምክንያቱም ቁርሾውና ጥላቻው ያለው በምሁራኑ መካከል እንጂ ተራው ህዝብ ጋር ባለመሆኑ ነው። የቅራኔውን እርሻ የሚያርሱት ምሁራኑ ናቸው። ምሁራኑ አውቀናል የሚሉት እንደየመሰላቸው እየፃፉና እንደመሰላቸው እየተናገሩ ህዝቡን ያቃርኑታል። እዚህ አገር ውስጥ ምሁራኑ እየፈጠሩ ያሉት ችግር ሊተኮርበት ይገባል። ያልተማረው ህዝብ እየተመራ ያለው በእነዚህ ጨለምተኛ አስተሳሰብ ባላቸው ምሁራን ነው። ወጣቱም ቢሆን የሚከተለው እነሱን ነው። እነሱ የተናገሯት ትንሽ ሃሳብ ብዙ ነገር ታቀጣጥላለች። ስለዚህ እዚህች አገር ላይ ሰላም እንዲሰፍን ከተፈለገ እነዚህ ምሁራን ከጥፋት ጎዳናቸው ሊመለሱ ይገባል።

የምናድገው ህብረት ስንፈጥርና አንድነታችንን ስናስጠብቅ ነው ። ተከፋፍለን የተለያዩ አገሮችን ብንፈጥር ማደግ አንችልም። ንግድ እንኳን የተሳለጠ የሚሆነው በጋራ ስንኖር ነው። ለምሳሌ ወለጋ የሚኖር አንድ ገበሬ ምርቱን የፈለገውን ያህል ቢያበዛ በሰላም ጊምቢ ማድረስ ካልቻለ ምርቱ ይባክንበታል እንጂ ተጠቃሚ አይሆንም። ስለዚህ አሁንም ቢሆን ለደረሰው ጥፋት ሁሉ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ህዝብ ፊት ቆመው ይቅርታ መጠየቅ ያለባቸው ምሁራኑ ናቸው። ለዚህ ደግሞ ደፋሮች መሆን አለባቸው። በንፁህ ልቦና ካሰብንበት የምንመኘው ሰላምና ልማት እናመጣዋለን።

ልባችን ካሰፋነው የማይመጣ አንድነትና ፍቅር አይኖርም። ፍቅር ቋንቋ የለውም፤ ጎሳ የለውም። ስለዚህ ሁሉም ሰው ልቡን ክፍት አድርጎ ወንድማማችነትን ሲያስብ ሁሉም ነገር ሩቅ አይሆንም። የእዚህች አገር ሰላም እርግጥ ነው፤ ውይይት ይፈልጋል። ከልብ የመነጨ መቀራረብ ይፈልጋል፤ በብስለት መመካከርን ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ መጀመሪያ ከራስ ጋር መታረቅና ውስጥን ማዳመጥ ይጠይቃል። ምክንያቱም ከራሴ ጋር ካልታረቅኩኝ ከጎረቤት ጋር መታረቅ አልችልም። መጀመሪያ ውስጤ የሚንተገተገውን ቅራኔና ጥላቻ ልቤ ውስጥ መግደል አለብኝ። ይህንን ማድረግ ሲቻል ዘላቂ ሰላምና ልማት ማምጣት ይቻላል። ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በያለበት ከራሱ ጋር መታረቅ አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ማሞ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## ትኩረት የሚሻው ዘገምተኛው ወረርሽኝ

**አስናቀ ፀጋዬ**

በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ስጋት እየሆኑ ከመጡ አስር የጤና ችግሮች ውስጥ አንዱ የፀረ-ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች መለመድ ነው። የፀረ ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች እየተለመዱ መምጣታቸውን ተከትሎም በዚህ ፈርጅ የሚመረቱ መድሃኒቶች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። መድሃኒቶቹ አምራቾችን ለኪሳራ ስለሚዳርጉ ወደፊት ከነጭራሹ የማይመረቱበት እድል እንዳለም ይነገራል።

በቅርብ ጊዜ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ700ሺህ በላይ የሚሆኑ ሰዎች ከፀረ-ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች መለመድ ጋር በተያያዘ በየዓመቱ ለህለፈተ ሕይወት ይዳርጋሉ። ከነዚህም ውስጥ በደቡብ ምእራብ እስያና ከሰሃራ በታች ባሉ ሀገራት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ። እ.ኤ.አ በ2050 ደግሞ ይህ ቁጥር ወደ 10 ሚሊዮን ያሻቅባል ተብሎ ይጠበቃል። በኢትዮጵያም የፀረ-ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች መለመድ ቀስ በቀስ አሳሳቢ የጤና ችግር እየሆነ መጥቷል።

በጤና ሚኒስቴር የመድኃኒትና ህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ውስጥ የአንቲ ማይክሮባያል ሬዚስታንስ ፕሪቬንሽንና ኮንቴ ይንመንት አስተባባሪ አቶ ይድነቃቸው ደገፋው እንደሚያብራሩት መድሃኒቶች ጀርሞችን ለመግደልና የጀርሞችን እድገት ለመግታት ዓላማ ይፈበርካሉ። ይሁንና ለነዚህ ሁለት ዓላማዎች መድሃኒቶች ሲፈበረኩ ጀርሞች መድሃኒቶች ሥራቸውን በአግባቡ እንዳይሰሩ ይላመዷቸዋል። ከዚህ አንፃር መድሃኒቶች ጀርሞችን ለመግደል ወይም የጀርሞችን ርቢ ለመግደል ሲሳናቸው የፀረ-ተህዋሲያን የመድ ሃኒቶች በጀርሞች መለመድ ይከሰታል።

የመድሃኒቶች በጀርሞች መለመድ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰት ሲሆን በተለይ ጀርሞች የተለያዩ ነገሮችን በመጠቀም ለአብነት ኬሚካሎችን



ፎቶ፡- አስናቀ ፀጋዬ፤

አቶ ይድነቃቸው ደገፋው፤

በማመንጨት የመድሃኒቱ ኬሚካል እንዳይሰራ በማድረግ፣ ቅርፃቸውን በመለዋወጥና መድሃኒቱ ወደ ሰውነት ሴሎች ውስጥ ሲገባ ተመልሶ እንዲወጣ በማድረግና ሌሎችንም ሥራዎች በመስራት መድሃኒቶች እንዳይሰሩ ያደርጋሉ። በዚህ ጊዜ የፀረ-ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች ይለመዳሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ መድሃኒቶችን በአግባቡ ለታለመው ዓላማ አለመጠቀም ማለትም መድሃ ኒቶችን በሐኪም ከታዘዘው መጠን አሳንሶ መውሰድ፣ ከፍ አድርጎ መውሰድ፣ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ መውሰድ የፀረ- ተህዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች መለመድን ያስከትላል።

በተመሳሳይ እንስሳቶችን ለማደለብ ሲባል የተለያዩ መድሃኒቶች ይሰጣሉ። እነዚህ መድሃኒቶችን የተላመዱ ጀርሞች ከእንስሳት ወደ ሰው የሚመጡበት እድል አለ። የመድሃኒት ፋብሪካዎች መድሃኒት በሚያስ ወግዱበት ጊዜ እነዚህ ጀርሞች ወደ እንስሳና ወደ ሰው የመተላለፍ እድል ይኖራቸዋል።

እንደ አቶ ይድነቃቸው ገለፃ የፀረ- ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች መለመድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም ትልቅ አሳሳቢ የጤና ችግር ነው። እ.ኤ.አ በ2022 በቅርቡ የወጡ መረጃዎችም የፀረ-ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች መለመድ ከኤች. አይቪ/ኤድስና ከወባ በሽታዎች በልጦ ትልቁ የሞት ምንጭ እንደሆነ አመላክተዋል። እ.ኤ.አ በ2019 በዓመት ወደ 4 ነጥብ 92 ሚሊዮን የሚጠጉ የዓለም ሰዎች ከፀረ- ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች መለመድ ጋር በተያያዘ ህይወታቸውን አጥተዋል። ከዚሁ ጋር በተያያ ዘም በዓለማችን በደቂቃ አንድ ሰው እንደሚሞት ተረጋግጧል።

ምንም እንኳን አልፎ አልፎ የጥራት ችግር ቢኖርባቸውም በሀገር አቀፍ ደረጃም የፀረ-ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች መለመድን በተመለከተ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በኩል የተለያዩ ጥናቶች ይደረጋሉ። የነዚህ ጥናት ውጤቶችም ችግሩ ቀስበቀስ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱንና ብዙ መሰራት እንዳለበት ያመላክታሉ። በርካታ ሴክተሮችም በጋራ መስራት እንዳለባቸውም ይጠቁማል።

አሳሳቢ እየሆነና ቀስበቀስ ወደ ወረርሽኝ ደረጃ ላይ እየደረሰ ያለውን የፀረ-ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች መላመድ ችግርን ለመቅረፍ እንደሀገር የተለያዩ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። ከነዚህም ውስጥ አንዱና ትልቁ ሀገሪቷ የፀረ-ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች መለመድ ችግርን ለመከላከል ያዘጋጀችው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ነው። ስትራቴጂክ እቅዱም እ.ኤ.አ ከ2021 እስከ 2025 ባለው ጊዜ ውስጥ ችግሩን ለመቅረፍ የተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ምን መስራት እንዳለባቸው አስቀምጧል።

ለእቅዱ ተግባራዊነትም የጤና ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴርና የአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ተፈራርመው ወደ ሥራ ገብተዋል። በሌላ አቅጣጫ ደግሞ የፀረ-ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች መላመድ ችግርን ለመቅርፍ ለህብረተሰቡ፣ ለጤና ባለሙያዎችና ለመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።

ለህክምና ባለሙያዎች፣ ለፋርማሲስቶችና ለነርሶችም በፀረ-ተዋሲያን መድሃኒቶች በጀርሞች መላመድ ዙሪያ በየጊዜው ስልጠናዎችን እየሰጠ ይገኛል። በተጨማሪም በጤና ተቋማት ስልጠናውን የሚሰጥ ቡድን በማቋቋም በሰላሳ ሆስፒታሎች ላይ ሥራ ተጀምሯል። ይህ ቡድን በጤና ተቋሙ ውስጥ ላሉ ባለሙያዎች ስልጠናዎችን ይሰጣል። ለህብረተሰቡም የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን ይሰ ጣል። አግባብነት ያለው የመድሃኒት አጠቃ ቀምና አስተዛዘዝ ላይም ተመሳሳይ የግንዛቤ ማስጨ በጫዎችን ለህብረተሰቡ ይሰጣል።

ዋናውና ትልቁ ሥራ ግን ከሚመለከታቸው ሶስቱ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችን በየሩብ ዓመቱ በጤና ሚኒስቴር በኩል በሚዘጋጅ መድረክ እየተገመገመ "ምን መሰራት አለበት?" በሚል ትላልቅ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። ሆኖም ከችግሩ አሳሳቢነት አንፃር ብዙ መስራት ይጠይቃል። ከመድሃኒት ሽያጭና አጠቃ ቀም ጋር ያለውን የቁጥጥር ሥራም ማጠንከር ያስ ፈልጋል።

# ለጤንነትዎ

## የጨጓራ ባክቴሪያ መንስኤና መፍትሄ

**አስናቀ ፀጋዬ**

የጨጓራ ባክቴሪያ /Helicobacter pylori/ በምግብ ልመት ስርዓት ውስጥ የሚፈጠር አንዱ የባክቴሪያ አይነት ሲሆን በአብዛኛው የውስጠኛውን የአንጀት ክፍል ያጠቃል። እ.ኤ.አ በ2018 እንደ ተሰራው አሀዛዊ ትንተና በዓለም አቀፍ ደረጃ 44 ከመቶ ያህሉ ህዝብ የጨጓራ ባክቴሪያ አለበት።

ምንም እንኳን ይህ ባክቴሪያ ጉዳት አልባ ቢሆንም በሆድ እቃ ውስጥና በትንሿ አንጀት ውስጥ ለሚፈጠር የጨጓራ አልሰር /ነቀርሳ/ ዋነኛ ምክንያት ነው ይላሉ ጠበብት።

የጨጓራ ባክቴሪያ /Helicobacter pylori/ በአብዛ ኛዎቹ ሰዎች ላይ ቁስለት ወይም ሌሎች ምልክቶችን አያስከትልም። ሆኖም ምልክቶች ቢያጋጥሙ እንኳን ባክቴሪያውን ለመግደልና ቁስሉን ለመፈወስ የሚረዱ መድኃኒቶች አሉ። በጥሩ የጤና ልማዶች እና ትክክለኛ የንፅህና አጠባበቅ እራስን እና ቤተሰብን ከባክቴሪያው መያዝ መከላከል እንደሚቻልም ሐኪሞች ይመክራሉ።

ብዙ ሰዎች በልጅነት ጊዜ የጨጓራ ባክቴሪያ / Helicobacter pylori/ ኢንፌክሽን ይይዛቸዋል። ነገር ግን አዋቂዎችም ሊያዙ ይችላሉ። ምልክቶቹ ከመጀመራቸው በፊት ጀርሞቹ በሰውነት ውስጥ ለዓመታት ይኖራሉ። አብዛኛዎቹ ባክቴሪያው ያለባቸው ሰዎች ግን በጭራሽ ቁስለቱ አይሰማቸውም። በዚህም የተነሳ የህክምና ባለሙያዎች አንዳንድ ሰዎች ከባክቴሪያው ኢንፌክሽን በኋላ ለምን በጨጓራ ቁስለት እንደሚያዙ እርግጠኛ አይደሉም።

**የባክቴሪያው አጋላጭ ምክንያቶች፡-**


- **ንፁህ ካልሆኑ ምግቦች፣ ውሃ፣ ወይም የመመገቢያ እቃዎች**
- **ንፁህ ውሃ ወይም ጥሩ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች አለመኖር**
- **በበሽታው ከተያዙ ሰዎች በሚወጣ ምራቅ ወይም ሌሳ የሰውነት ፈሳሽ ጋር ንክኪ መኖር**
- **በሰው የተጨናነቀ አካባቢ መኖር**

**ምልክቶቹስ፡-**

በዚህ ባክቴሪያ የተጠቁ አብዛኛዎቹ ሰዎች የህመም ምልክት ላይታይባቸው ይችላል። ነገር ግን ባክቴሪያው በሂደት የጨጓራውን የውስጠኛ ክፍል ሊጎዳ ወይም ሌላ በሽታ ሊያስከትል ይችላል። የባክቴሪያው ዋና ዋና ምልክቶች ግን የሚከተሉት ናቸው።

የመድከም ወይም ሆድ ማቃጠል ስሜት /በተለይ ሆድ ባዶ ሲሆን/

- **እብጠት**
- **ማቅለሽለሽ**
- **ባልተለመደ መልኩ የሰውነት ክብደት መቀነስ**
- **ማስታወክና**
- **ደካማ የምግብ ፍላጎት መኖር ናቸው።**



**እንዴት ይታከማል?**

እርስዎ በጨጓራ ህመም ተጠቅተው ኤች ፓይሎሪ ባክቴሪያ /H.pylori/ በሰገራ ወይም በደም ምርመራ ከተገኘብዎት ባክቴሪያውን ለመግደል የሚረዱ የአንቲባዮቲክ ጥምረት ይታዘዝልዎታል። ከዚህ በተጨማሪም የህመም ስሜቶችን ለማስታገስ የሚረዱ መድሃኒቶችም ጎን ለጎን ይሰጥዎታል። ከዚህ ባለፈ ግን ይህ ከመከሰቱ በፊት አስቀድሞ መጠንቀቅ ነውና ጤናዎን ይጠብቁ።

**ምንጭ፡- /i-tena/አይ ጤና**

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# «ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል»

**ለእኛም ለዛሬዎቹ የሳባ ልጆች የሚያስፈልጉን መሪዎችና ፖለቲከኞች ተፈጥሯዊ ችግሮቻችንን እየነቀሱ የኢኮኖሚያችንን፣ የማሕበራዊ ተራክባችንን ቁስልና የህመምተኛ ፖለቲካችንን እባጭ እንዲያፈርጡልን እንጂ በብልጭልጭ አርቴፊሻል ፖሊሲና መመሪያ እንቆቅልሻችንን እንዲያወሳስቡብን አይደለም። አርቴፊሻሉንና ተፈጥሯዊውን እውነታ እያምታቱም «እሳት ካየው ምን ለየው» እያሉ እንዲፈላሰፉና እንዲመጻደቁ አንፈቅድላቸውም**

## የብሂሉ ዳራ፤

ሰውዬው ሹም ነበሩ አሉ። ስማቸው ማን ነበር? ጊዜውስ መቼ ነው? አድራሻቸውና የሥልጣን እርከናቸውስ? ወዘተ. ለሚሉት ጥያቄዎች ሕዝባዊው የሥነ ቃል ምንጫችን መልስ ስለሌለው ታሪኩን የምናስታውሰው ከአፍ አፍ እያቀባበሉ በነበር ያስተላለፉልንን ተራኪዎቻችንን በማመን ብቻ ይሆናል። ታሪኩን እንደተፈጸመ ለሚያምኑ ልበ ቅኖች "እሰየው" ብለን እናመሰግናቸዋለን። "ምንጭ የሌለው አፈ ታሪክ ነው" በማለት ሙግት ለሚገጥሙትም መልሳችን "ሰውን ሰው ያሰኘው ዴሞክራሲ ነው" የሚለውን ሕግ ተጋፍተን ስለማንጋፋቸው መብታቸውን እናከብርላቸዋለን። ለማንኛውም ታሪኩን ወደመተረክ እንዝለቅ።

እኒህ ለሰማይ ለምድር የከበዱ የታሪካችን ገጸ ባሕርይ ሹም በአንድ ወቅት በግዛታቸው ውስጥ ርሃብና ችጋር ገብቶ ሕዝባቸውና ቤተሰባቸው ጭንቅ ላይ ወድቆ ነበር አሉ። ይህን መሰሉ ያልተዘጋጁበት የተፈጥሮ "በላ"(መከራ) ግራ ያጋባቸው እኒያ ጎምቱ ወንበረተኛ ቢቸግራቸውና መላው ቢጠፋቸው ለሥልጣን እርከናቸው ቁብ ሳይሰጡና በይሉኝታ ሳይግደረደሩ ጓሯቸው ያፈራውን የዱባ ምርት ገበያ ወስደው በመሸጥ ያንን ክፉ ቀን ለማሳለፍ ወሰኑ ይባላል።

ነገር ግን የዱባ ምርቱ የሚያወላዳ ስላልሆነ ምኑን ከምን እንደሚያደርጉት ግራ በገባቸው ሰዓት እኩል የተጨነቁት ባለቤታቸው በጉዳዩ ላይ አስበውበት ኖሮ "ምን ያስጨንቅዎታል? የዱባው ቁጥር ካነሰ ለምን በሀረግ ላይ የተንዠረገገውን ቅል ለቅመን "ከዱባው" ቀላቅለን አንሸጥም? ከነአባባሉም እኮ ‹በዘመነ መከራ የተፈጸመ ግፍ ከወንጀል አይቆጠርም›" በማለት ስላበረታቷቸው ባልየው እንደተመከሩ ዱባና ቅሉን ቀላቅለው ገበያ መሃል በመዘርጋት ገዢዎችን መጠባበቅ ጀመሩ ይባላል።

እውነትም ገበያው እንደደራ አንዱ ገዢ ወደተደረደሩት የዱባ ምርቶች ቀረብ ብሎ ሲያስተውል ከዱባው ጋር ቅል እንደተቀላቀለበት ያስተውላል። ይሄን ጊዜ ያ ከመታለል የዳነው ገበያተኛ ድምጹን ከፍ አድርጎ "አቤቱ ፈጣሪ ሆይ ምኑ ዘመን ላይ ደረስን! እዝጊዮ አቤት! አቤት! የሕግ ያለህ የፍትህ ያለህ! የፈጣሪ ቁጣ ወርዶብን በርሃብና በቸነፈር መቀጣታችን አንሶ ምን ‹ቅል ባገኘ ብንሰኘ› (ቅል ባገኘ ማለት ሙልጭ ያለ ድሃ ማለት ነው) መንግሥት ባለበት አገር "ቅልን ዱባ" ብሎ መሸጥ ግፍ አይሆንም?" ብሎ በንዴት በመጦፍ ፊቱን ወደ ሻጩ ዞር ሲያደርግ ለካስ ተራ ነጋዴ የመሰሉት የራሱ ጉድ - የአገሩ ገዢ ናቸው። ይሄኔ በአፍ እላፊው ተደናግጦና አንደበቱን አለስልሶ፤ "ማለቴ ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል" ለማለት ፈልጌ ነው" በማለት ለሹሙ እጅ ነስቶ ራሱን ከችግር ታደገ ይባላል።

ሁለተኛው ገበያተኛም እንዲሁ ዱባውን ለመግዛት ቀረብ እንዳለ "ሻጭ ለዋጩ" እኒያው የአካባቢው ጌቶች መሆናቸውን ሲያውቅ ፍርሃት እያንዘረዘረው ቀልብ እንደነሳው ወፌፌ ወዲያ ወዲህ እየተንጎራደደ፡-

**«እረ ምረር ምረር፣ ምረር እንደ ቅል፣**
**ስላልኮመጠጠ ስላልመረረ ነው ዱባ እሚቀቀል።»**

በማለት ገበያውንና ገበያተኛውን በብሶት ቀረርቶ አናወጠው ይባላል። በዚያው ገበያ ላይ "ዱባ ባገሩ ጋን ያህላል አሉ።"፤ "ዱባና ቅል አብሮ ይበቅላል፤ አበቃቀሉ ግን ይለያል" በማለት የሹሙን ድርጊት በጥበበ ቃላት አራክሰው የተዘባበቱም በርካቶች ነበሩ - ይለናል ሥነ ቃላዊ ትረካው።

**ዱባና ቅሉን እንዳንለይ ግራ ያጋቡን ኑሯችንና አኗኗሪዎቻችን፤**

ከምንጊዜውም ይልቅ ዛሬ በኑሯችን ጅራፍ የተገረፍ ንበት ጫንቃችንና ጀርባችን ቁስሉ እያገረሸ በርትቶብናል። ማመርቀዙም ከፍቶብናል። በሁሉም የኑሯችን ዘይቤ ውስጥ "ዱባና ቅሉ" እየተቀላቀለ ሕይወታችንን መራራ አድርጎታል። የፖለቲካውና የመንግሥት ጉልበት የራደ እየመሰለን ስንባንን ውለን ማደርንም ተላምደነዋል። ሥልጣነ በትሩን የያዙት "ሙሴዎቻችን" ተደራርቦ የተጋረጠብንንና በቀይ ባሕር የሚመሰለውን ፈተናችንን በሥልጣነ በትራቸው በመምታት ከፍለው በድል ሊያሻግሩን የቻሉ አልመስል ብሎን "በኤሎሄ!" እየቃተትን ወደ ፀባኦት መቃተታችንን አላቋረጥንም።

በየደረጃው ያሉ ገዢዎቻችንና ዘመንኞቹ ሹመኞች ቀላቅለው እያቀረቡልን ያለው የዱባና ቅል ውሳኔያቸውና አተገባበራቸው እንደማያዋጣ በሕዝብ የእምባ መዋጮ ጭምር እየለወስን "አቤቱታ" ብናቀርብም ሰሚ ያገኘን አልመስል ብሎን ግራ መጋባታችን ጨምሯል።

የቢሮክራሲው ዘዋሪዎች የስብሰባ ውሎ አምሽቶማ ተነግሮም ሆነ በኡኡታ ተገልጾ ሰሚ በመጥፋቱ፤ "ምን ዕንቁላል ድፍን፤ ማያችሁን እምዬ ማርያም ድፍን" ብለን የልጅነታችንን እርግማን በማዥጎድጎድ "የውሾን ነገር ያነሳ ውሾ" በማለት በሕዝባዊ ልብ ለልብ መናበብ ተግባብተን በ"ተው ቻለው ብሶት" ማንጎራጎር እንደሚሻል የጋራ ውሳኔ አሳልፈናል። "ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል" ብሂል አርጅቶ ያፈጀው ከማእረጉና ከማእረግተኞቹ ጋር አንድ ላይ ተደምሮ ነው። በአንፃሩ ዜጎች ሁሉ እንደ አዲስ አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብሂሎች "ዝም አይነቅዝም፣ ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባም" የሚባሉትን ዓይነቶች ነው። ተናግሮ ጥርስ ከሚነከስ ስሜትን አምቆ ውስጥ ቢነቅዝ ይበጃል።

በድምጻችን ተመርጠው በላያችን ላይ ያነገሥናቸው አብዛኞቹ ሹመኞች ውለው ሳያድሩ በሾህ ልምጭ ይጠበጥቡን ጀምረዋል። የሙስና ሰንሰለታቸውን አርዝ መው የሥልጣናቸው ጀንበር ሳትጠልቅ "ቅርሳቸውን" ለመቋጠር ደህና አድርገው መጋጡን ጀምረዋል። መቶ ሺህ ብር ጉቦ ሲቀበል፣ በሚሊዮን ብር ሲደራደር እየተባለ በሚዲያ የሚለፈፈው በናሙናዎቹ ላይ ካልሆነ በስተቀር ወደ ላይም ወደ ጎንም ጠለቅ ብሎ ቢፈተሽ ቅርናቱና ክርፋቱ አያድርስ የሚያሰኝ ነው። ገና ዓመት ሳይሞላ እንዲህ ካደረጉን ዘንዳ ሆዳቸውና ደረታቸው ሰፋ ሰፋ ማለት ሲጀምርማ ምን ሊያደርጉን እንደሚችሉ ለመተንበይ ነብይነት ግዴታ አይደለም። እኛ ለመኖር ወይም ላለመኖር በግብግብ ተሸንፈን ስንወድቅ፤ እነርሱ ለነገ "ቅርስ ለመቋጠር" ፍልሚያውን አጧጡፈውታል። የት ቁጭ ብለው እንደሚበሉት ግን ያሰቡበት አይመስልም።

ገበያው ሊያሳብደን ኪሳችንን መፈተሽ ገና እንደጀመረ፤ "ለከርሞ የሚያብድ ሰው በመስከረም ሱሪውን ከፍ ከፍ ማድረግ ይጀምራል" እያልን በተካንንበት ብሂል "ቀንድ ማቆጥቆጥ" በጀመረው ገበያ መካከል ቆመን ታደጉን እያልን ስንጮኽ አልሰማ ብለውን ጆሯቸውን ደፍነውብን ነበር። እነሆ የፈራነው ደርሶ የኢኮኖሚው አብሾ አናታችን ላይ ወጥቶ ጨርቃችንን አስጥሎ አእምሯችንን ስለሰወረን "ዱባና ቅሉን" መለየት ተስኖን በብእራችንም በአንደበታችንም መለፍለፍን ሥራዬ ብለን ተያይዘነዋል። እንደተለመደው በድምጻችን ለወንበር ያበቃናቸው ገዢዎቻችን ዛሬም እያወቁ የደፈኑትን ጆሯቸውን አልከፍት ብለው "ይለፍልፉ ምን እንዳያመጡ ነው" የሚሉን ከሆነ "የሚመጣውን" አብረን ስለምናይ እምባችንን ወደ ፈጣሪ እየረጨን የፍርዱን ቀን በጋራ እንጠባበቃለን።

ለነገሩ በዚህች ምስኪን አገሬ ውስጥ ማን ያልባለገ ይገኛል። የሚኖር ከሆነ ሙት ተስፋችንን ስለሚያንሰራራ በግልጽ የሚያመላክቱን ብጹዓን ናቸው። ፖለቲካው ባልጓል። ያባለጉትን ባለጊዜዎች ነቅሰን በአደባባይ እንዳናጋልጥ ወይንም "ባለጌን ከወለደ የገደለ ይጽድቃል" ብለን በድፍረት እንዳንናገር "ሕጉ አሟረታችሁ" በማለት በአፍ እልፊት የክስ ቻርጅ ከፍቶ ከርቼሌ እንዳይወረውረን እንሰጋለን። "ለጥብቅና አግዘን የምንለው ዴሞክራሲውም" ሁሌም ችግር ሲገጥመን "ሥራችሁ ያውጣችሁ" በማለት ፊት እንደሚነሳን አልጠፋንም።

እንዲህ ዓይነቱን የአገር መከራ በጨዋታ እያዋዛን ብሶታችንን ስንገላለጥ አንዱ ዘመናዊ ገበሬ ነኝ ባይ ቃንቄ ጎረምሳ፤ "የባለገው መች ፖለቲካው ብቻ ሆኖ። የገበሬው ማሳም ያለ ኬሚካል ማዳበሪያ ጉቦ ምርት አልሰጥም ብሎ ካደመብን ሰነባብቷል" በማለት ከጨፍጋጋ ስሜት አውጥቶ ፈገግ እንድንል አድርጎናል። ባለሥልጣኖችም ሆኑ ተፈጥሮ ባልገው ያለ ጉቦ ኃላፊነታቸውን የማይወጡ ከሆነ ወደ ማን አቤት እንበል? "ግራ የገባው ግራ" አሉ ወይዘሮ ወርቄ። እያረርን እንሳቅ እንጂ ምን ማድረግ ይቻላል?

**ጠቢብ ሹም ሆይ ወዴት አለህ!?**

ከብሶትና እሮሮ ጨፍጋጋ ስሜት ወጣ ብለን ፈገግ የሚያደርግ አንድ አፈ ታሪክ እንከፋፈል። የአፈ ታሪኩ መነሻ ሃሳብ የተወሰደው ከቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ (1ኛ ነገሥት ምዕ. 10) ይመስላል። ታሪኩ የሚያጠነጥነው በእስራኤሉ ንጉሥ በሰሎሞንና በአበሻዋ ንግሥት በሳባ ላይ ነው። ንግሥተ ሳባን "የእኛ ናት! ማን የእነ እከሌ አደረጋት?" የሚሉ ሞጋቾች ብዙ ስለሆኑ ለጊዜው ለታሪኩ እንጂ ለእነርሱ አታካራ ፊት አንሰጥም። እንደ ወዳጅ እንምከራቸው ካልን ግን ይህቺን ታላቅ ንግሥት የምንጠራት በሦስት ስም ንግሥተ ሳባ፣ ንግሥተ ማክዳ፣ ንግሥተ አዜብ እያልን ስለሆነና ምስክርነት ደግሞ በሦስት ስለሚጸና "እመቤት ሆይ ሳባ የእኛና የእኛ ብቻ ስለሆነች" የራሳቸውን ጠበቅ የእኛን ለቀቅ እንዲያደርጉልን ማሳሰቢያ አኑረን እናልፋለን።

ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ዝና ሰምታ ልትጎበኘው ከምድረ ኩሽ ተነስታ ወደ ኢየሩሳሌም እንደገሰገሰች ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚከተለው ይተርክልናል። "የሳባም ንግሥት በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች። በግመሎችም ላይ ሽቱና እጅግ ብዙ ወርቅ የከበረም ዕንቁ አስጭና ከታላቅ ጓዝ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ገባች።...ሰሎሞንም የጠየቀችውን እንቆቅልሽ ሁሉ ፈታላት። ሊፈታላት ያልቻለውና ከንጉሡ የተሰወረ ነገር አልነበረም።"

አፈ ታሪኩ የተቃኘው ይህንን የቅዱስ መጽሐፍ እውነታ መሰረት አድርጎ ነው። እናም ንግሥት ሳባ ወደ ሰሎሞን እንደቀረበች ሰባት ያህል እርምጃ ራቅ በማለት በቅርጽም ሆነ በይዘት ተመሳሳይ የሆኑና አንዱን ከአንዱ በፍጹም መለየት የሚያስቸግር የአበባ እምቡጦች እያሳየችው፤ "ንጉሥ ሆይ! ሺህ ዓመት ንገሥ! ከያዝኳቸው ከእነዚህ ሁለት የአበባ እምቡጦች መካከል የተፈጥሮው አበባ የትኛው ነው? አርቴፊሻሉ?"

ጠቢቡ ንጉሥ ሰሎሞን በእንቆቅልሽ ጥያቄዋ ትንሽ ግር ተሰኝቶ ከቆየ በኋላ ለፈታኟ ንግሥት እንዲህ ሲል መለሰላት። "አንቺም ንግሥት ሆይ ሺህ ዓመት ንገሺ! የተፈጥሮው አበባ የቱ እንደሆነ የምነግርሽ በእጅሽ የያዝሻቸውን አበቦች እዚያ መስኮቱ ደፍ ላይ ሄደሽ አስቀምጪ" በማለት አዘዛት። እርሷም እንደታዘዘችው አደረገች።

አበቦቹን አስቀምጣ ገና ዞር ከማለቷ አንዲት ቀሳሚ ንብ ጢዝዝዝ እያለች ሄዳ የተፈጥሮው አበባ ላይ አረፈች። ይሄን ጊዜ ንጉሥ ሰሎሞን ወደ ንግሥት ሳባ ዞር በማለት "እነሆ የተፈጥሮ አበባ የቱ እንደሆነ መልሱን አገኘሽ?" በማለት እንቆቅልሹን ፈታላት ይባላል። እርሷም ከመደነቋ የተነሳ እንዲህ አለችው ይላል የአፈ ታሪኩ መደምደሚያ ሳይሆን የቅዱስ መጽሐፉ እውነታ። "ንጉሡንም አለችው፡ - ስለ ነገርህና ስለ ጥበብህ በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና እውነት ነው። እኔም መጥቼ በዓይኔ እስካይ ድረስ የነገሩኝን አላመንኩም ነበር። እነሆም እኩሌታውን እንኳን አልነገሩኝም። ጥበብህና ሥራህ ከሰማሁት ዝና ይበልጣል" (1ኛ ነገሥት 10፡6 -7)።

ለእኛም ለዛሬዎቹ የሳባ ልጆች የሚያስፈልጉን መሪዎችና ፖለቲከኞች ተፈጥሯዊ ችግሮቻችንን እየነቀሱ የኢኮኖሚያችንን፣ የማሕበራዊ ተራክቧችንን ቁስልና የህመምተኛ ፖለቲካችንን እባጭ እንዲያፈርጡልን እንጂ በብልጭልጭ አርቴፊሻል ፖሊሲና መመሪያ እንቆቅልሻችንን እንዲያወሳስቡብን አይደለም። አርቴፊሻሉንና ተፈጥሯዊውን እውነታ እያምታቱም "እሳት ካየው ምን ለየው" እያሉ እንዲፈላሰፉና እንዲመጻደቁ አንፈቅድላቸውም።

የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚስቶቹን ያረጀና ያፈጀ ፍልስፍና እየተነተኑ "ማልተስ እንዳለው፣ ማርክስ እንደተፈላሰፈው፣ ሚልተን ፍሬድማን፣ አስቴር ዱፍሎ እንደጻፉት ወዘተ." እያሉ ግራ እንዲያጋቡንም ፊት ልንሰጣቸው አይገባም። ዓለም ባንክ እንዳዘዘው፣ አይ.ኤም.ኤፍ እንደተነበየው የሚለው ዲስኩርም እጅ እጅ ብሎናል። በፖለቲካው ሠፈርም ቢሆን በሕልማቸው የቃዡትን ሁሉ ማለዳ ላይ እየዘረገፉ ሸክም እንዲጭኑብን ልንፈቅድላቸው አይገባም። በየመድረኩና በየሚዲያው "ቅሉን ዱባ ነው" ሲሉን "አበቃቀሉ ለየቅል" እያልን፤ አርቴፊሻሉን አበባ የተፈጥሮ ነው እያሉ ሲደልሉንም በሕዝባዊ ጨዋነት እየገሰጽናቸው እንዲታረሙ ማድረግ ድፍረት ሳይሆን መብት ነው። "መቼስ ምን ይደረጋል" ቁዘማ የትም ስለማያደርሰን ሕዝቤ ሆይ ለራስና ለራሳችን እንወቅበት። አገሬስ ሰማሽኝ!? ሰላም ይሁን!!

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

# ቂምና ገስባ...

መልካምሥራ አፈወርቅ



አዲስ አበባ ሀና ማርያም አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች ማገዶ ሲፈልጉ ጫካ መውረድ፤ ገበያ መሄድ አያሻቸውም። ቤታቸው ድረስ፣ ከመንደራቸው የሚያቀርቡ ደንበኞች አሏቸው። ደንበኞቻቸው የቡና ገለባን ከሌሎች ገዝተው ለእነሱ በጥሩ ዋጋ የሚሸጡ ናቸው።

የእዚህ መንደር እናቶች ገለባውን ለማገዶ በፈለጉት ጊዜ ጆንያ ተሞልቶ፣ ማዳበሪያ ተጠቅጥቆ ይመጣላቸዋል። ለሚያመጡላቸው ባለገለባዎችም የዋጋውን ከፍለው፣ ለሌላ ቀን ቀጥረው ይሸኛሉ። የቡና ገለባው እንጀራን በእሳት ለሚጋገሩ ሴቶች ሁነኛ መፍትሄ ነው። ከጥቂት እንጨት ተዳምሮ፣ ብዙ ግልጋሎት እየሰጠ አመታትን አሻግሯል።

በሀና ማርያምና አካባቢው የቡና ገለባን ሽያጭ እንጀራቸው ያደረጉ በርክተዋል። ገለባውን ቡና ከሚፈለፍሉ ድርጅቶች ተረክበው ማገዶ ለሚያደርጉት ደንበኞች ያከፋፍላሉ። ደንበኞቻቸው የእነሱን ገለባ ወስደው በሚከፍሏቸው ገንዘብ ኑሯቸውን ይመራሉ።

### የገስባው ጉዳይ...

ጌታቸው የተባለው ወጣት የቡና ገለባን ከአንድ ድርጅት እየገዛ ለሚፈልጉ ጠያቂዎች ያከፋፍላል። ጌታቸው እስከዛሬ ራሱን ለማስተዳደር ብዙ ሥራዎችን ሞክሯል። የቡና ገለባውን ማከፋፈል ከጀመረ ወዲህ ሥራው እንደሚያወጣው ገምቶ የራሱን ደንበኞች አፍርቷል። እየተዘዋወረ በሚሠራባቸው መንደሮች ተፈላጊነቱ እየጨመረ ነው።

ወጣቱ የቡና ገለባን ከሚወስድበት ድርጅት ጥሩ መቀራረብ ፈጥሯል። የእጁን ሸጦ ሲጨርስ ሌላ ጆንያ ይረከባል። የጆንያውን ሲያጠናቅቅ የተጠየቀውን ሊያመጣ ይሮጣል። ጌታቸው አብሮት ከሚሠራ ባልንጀራው ጋር ተሳስበው ያድራሉ። ነገን የተሻለ ለማድረግ፣ ሕይወትን በጥሩ ለመምራት በጋራ ይሠራሉ።

ለጓደኛሞቹ የቡና ገለባው እስከዛሬ ከሞከሩት ሥራ የተሻለ ነው። ውሎው ድካምና ልፋት እንዳለው ያውቃሉ። ያም ሆኖ ከሌላው ገቢ መልካም የሚባል ነው። እኩል ሠርተው በሚያገኙት ገቢ የድርሻቸውን ይወስዳሉ። ሁለቱም ዛሬን ብቻ አያስቡም። ሁለቱም ስለነገ ህልም አላቸው። አርቀው ያልማሉ። ከፍ ብለው ያስባሉ።

ሁለቱ ሳሪስ አካባቢ ከሚገኝ የግል ማከፋፈያ ገለባውን ሲረከቡ በክፉ የሚያይዋቸው ዓይኖች አልጠፉም። ሥራውን መተዳደሪያ ያደረጉ ጥቂቶች በእንጀራቸው የመጡ፣ በሕይወታቸው የገቡ ያህል ይቆጥሩታል። ከድርጅቱ እነሱ ብቻ መጠቀም የሚሹ አንዳንዶች ወጣቶቹን በርቀት እየቃኙ ጥርስ ይነክሱባቸዋል። እንጀራቸውን እንደነጠቁ፣ ሕይወታቸውን እንደተጋሩ ቆጥረውም ይገላመጣሉ።

ጌታቸውና ጓደኛው በሚኖሩበት አካባቢ የአንድ ሰው አስተያየት በተለየ ይረብሻቸው ይዟል። ሰጠኝ ልክ እንደነሱ ወጣትና በቡና ገለባ ሽያጭ የሚተዳደር ነው። እሱም በሥራው አመታትን ገፍቶ ደንበኞችን አፍርቷል። ገለባውን ሸጦ በሚያገኘው ገቢ ራሱን እየመራ ፍላጎቱን እየሞላ ነው። ገለባውን ከሚረከብበት ድርጅት ጓደኛሞቹ መገኘታቸውን ካወቀ ወዲህ ሰላም ተሰምቶት አያውቅም።

ሰጠኝ ባልንጀሮቹ የእሱን ደንበኞች፣ ደንበኛ ማድረጋቸውን ካወቀ በኋላ ቂም ይዞ ጥላቻ አፍርቷል። ሁለቱን በርቀት ካያቸው ደሙ ይፈላል። አጠገቡ ካሉ ሊጣላቸው ሊነቁራቸው ይፈልጋል። ሰጠኝ ሁሌም ልጆቹ ገለባውን ከድርጅቱ መረከባቸው ያስቀናዋል። ፍላጎቱ ይህ ብቻ አይደለም፤ ገዢዎችም ገለባውን ከእሱ እጅ ብቻ እንዲረከቡ ነው። ይህን ቢያደርግ ፣ የተሻለ ትርፍ ያገኛል። ገቢው ጨምሮ ሥራውን ያሰፋል።

አሁን ሰጠኝ ስሜቱ ከጥላቻ ተሻግሯል። ጓደኛሞቹን በግልጽ አግኝቶ መጣላት እየፈለገ ነው። እንጀራውን፣ መኖሪያውን እንደነጠቁት ተሰምቶታል። ይህ ስሜቱ ጫፍ በነካ ጊዜ ለድብድብ ይጋበዛል። ጓደኛሞቹ የሰጠኝ ሀሳብ ገብቷቸዋል። እሱ እንዳሰበው ገለባውን ከእጁ ተረክበው ለሌሎች ማስረከብ አይፈልጉም።

ሰጠኝ የጓደኛሞቹን ውሳኔ ካወቀ ወዲህ ማስፈራራትና መዛት ጀምሯል። ባገኛቸው ቁጥር ለድብድብ ይጋበዛል። አንዳንዴ የውስጡን ሀሳብ የሚናገረው በእርግጠኛነት ነው። እነሱን ገድሎ ሰላሳ ሺህ ብር ካሳ መክፈል እንደሚችል ሰው እየሰማው ጭምር ይናገራል።

ባልንጀሮቹ የቡና ገለባ ሥራቸውን አላቆሙም። ሰጠኝ ትጋታቸውን ባየ ጊዜ እልሁ ጨምሯል። ዛቻና ማስፈራራቱን፣ ልደባደብ፣ ልግደል ማለቱን ቀጥሏል።

### ምክክር ...

ሰጠኝ አብሮት ከሚያዘወትረው ጓደኛው ጋር ስለቡናው ገለባ እያወራ ይገባበዛል። የገለባው ነገር ከተነሳ የባልንጀራሞቹ ጉዳይ ሳይወራ አያልፍም። ዘወትር ስማቸውን እየጠራ የሚብከነከነው ሰጠኝ በእንጀራው እንደመጡበት የሚናገረው በተለየ ብሶት ሆኗል። ስሜቱን በወጉ የሚረዳው የቅርብ ጓደኛው በጉዳዩ እንዳይበሳጭ እየነገረ አብሮነቱን ያሳየዋል።

የሰጠኝ ጓደኛ በሰማው የገለባ ታሪክ ብስጭት ይዞታል። ጓደኛሞቹ ከፋብሪካ ብቻ ሳይሆን እርሱን አልፈው ከሌላ ሰው ላይም በተጨማሪነት እየገዙ መሸጣቸው እያናደደው ነው። ይህን ለማድረጋቸው የእጃቸውን እንዲያገኙ ጓደኛውን ማነሳሳት፣ ማደፋፈር ይዟል። ሰጠኝ ጓደኛው የሚለውን አምኖ ተቀብሏል። ሁለቱ ሰዎች ላደረጉት ድፍረትና ንቀት የእጃቸውን ሊያገኙ ይገባል።

ሰጠኝና ጓደኛው ብርጭቆ ይዘው በሚዝናኑበት ግሮሰሪ ሁሌም የሚያነሱትን ጉዳይ አይዘነጉም። በተለይ ጌታቸው የተባለው ወጣት ድርጊት ከልብ እያናደደ አልህ አስይዟቸዋል። የሰጠኝ ጓደኛ መፍትሄውን አመላክቶ መሆን የሚገባውን ጠቁሟል። ሰጠኝ እሱ ባለው ተስማምቶ ቀንና ጊዜ ለይቷል። ማድረግ ያለበትን፣ መሆን የሚገባውን አውቆ ራሱን አዘጋጅቷል።

### ነሐሴ 7 ቀን 2007 ዓ.ም...

ምሽቱ ገፍቷል። ወቅቱን ጠብቆ መጣል የጀመረው የነሐሴ ዝናብ አሁንም አላባራም። የሀና ማርያም ሰፈርና አካባቢው ነዋሪዎች በጊዜ ወደ የቤታቸው ገብተዋል። እንዲህ ጨለማና ዝናብ በሚሆን ጊዜ ለደህንነታቸው የሚሰጉ እግረኞች ጥቂቶች አይደሉም። ዝናብ ሲመጣ ጨለማው ይበረታል። ይህኔ ጊዜና ቦታ መርጠው ፣ የሰውን ብቸኝነት ለሚሹ ዘራፊዎች አጋጣሚው ያመቻል።

የሁለቱ ጓደኛሞች ልብ ግን ከዚህ ዓይነቱ ስሜት ርቋል። እነሱ ጨለማና ዝናቡን የፈለጉት ለተለመደው ዓላማ አልሆነም። ሰጠኝና አብሮት ያለው ሰው ወዳሰቡት ሰፈር ሲቃረቡ ውስጣቸው ብዙ እያቀደ እጃቸው ላሰቡት ድርጊት እየተዘጋጀ ነው። ምሽት ሦስት ሰዓት ሆኗል። እግራቸው የቆመበት ስፍራ እነሱ የሚፈልጉት ቤት ስለመሆኑ አረጋግጠዋል።

ከአንድ ግቢ ደርሰው የሚሹትን ሰው በዓይናቸው ፈለጉት። የጨለማው ብርታት የሚፈልጉትን አላሳጣ ቸውም። የመጡበትን አግኝተዋል። ተፈላጊው ሰው ከቤቱ ተቀምጧል። አዩት፣ አላያቸውም። ከዓይናቸው ሳይርቅ ወደ ፊት ገሰገሱ።

ግቢውን አቋርጠው ወደ ክፍሉ አመሩ። ተፈላጊውን ፊት ለፊት ተቀምጦ አገኙት። ማንነታቸውን እንዳወቀ ከልቡ ደነገጠ። በዚህ ሰዓትና በራሱ መኖሪያ ምን ሊያደርጉ እንደመጡ ግራገባው። ጥያቄ እስኪያቀርብላቸው አልጠበቁም። ያሰቡትን ፈጽመው፤ የልባቸውን ከውነው ከቤቱ ሲወጡ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ከሰላሳ ሆኖ ነበር።

### ድንገቴው ጥሪ ...

ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በድንገት የደረሰው የስልክ ጥሪ የዕለቱን የምሽት ተረኞች ጆሮ ያነቃው በፍጥነት ነበር። የስልክ ጥሪው መልዕክት የደረሰው ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01 ልዩ ስሙ ሀና ማርያም ከተባለ አካባቢ ነበር። ፖሊስ በስፍራው ሲደርስ የተባለው ግቢና አካባቢው በሰዎች አጀብ ተሞልቶ ነበር።

የምርመራ ቡድኑ አባላት ቦታውን እያስለቀቁ ወደ ተባለው ቅጥር ግቢ አመሩ። ወዲያው ከፊት ለፊት ያለው ክፍል በር በግማሽ ገርበብ ብሎ ተመለከቱ። ጥቆማውና ዋና ጉዳዩ የሚመለከተው ቤት ከፊት ለፊት የሚታያቸው ክፍል መሆኑን አውቀዋል።

የምርመራ ቡድኑ አባላት በሩን በርግደው ወደ ውስጥ ዘለቁ። ከቤቱ ወለል ላይ በስለት ተወግቶ በደም የተነከረው ወጣት በሕይወት አለመኖሩን ለማወቅ አልተቸገሩም። ስፍራውን በጥንቃቄ ከበው ምርመራቸውን ቀጠሉ። በዕለቱ በስፍራው የተገኙ ባለሙያዎች አስፈላጊውን አጠናቀው አስከሬኑን አነሱ።

ፖሊሶቹ የሟችን ማንነትና የተገደለበትን ምክንያት ለማወቅ መረጃዎችን ማሰበሳብ የጀመሩት ወዲያውኑ ነበር። ሟቹ በአካባቢው የቡና ገለባን እየሸጠ የሚተዳደር ወጣት ጌታቸው ስለመሆኑ ታውቋል። ከእሱ ጋር የሚሠራው ባልንጀራው አብሮት ባለመሆኑ የሆነውን ማስረዳት አልቻለም። ያም ሆኖ ለጉዳዩ ተጠርጣሪ የሚያደርገውን ግለሰብ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀም።

ፖሊስ የጌታቸውን ባልንጀራና ሌሎች እማኞችን በማስረጃነት መዝግቦ ድርጊቱን ይፈጽመዋል የተባለውን ሰጠኝ ታደሰን ማፈላለግ ያዘ። ሰጠኝ ወጣቱ ከተገደለበት ምሽት አንስቶ በአካባቢው አልታየም። አብዛኛው ጠቋሚ ተጠርጣሪው ሰጠኝ እንደሚሆን ገምቷል። ፖሊስ እሱን ጨምሮ አብሮት ነበር የተባለውን ግለሰብ ማፈላለጉን ቀጥሏል።

በምርመራው ወቅት ለፖሊስ የደረሰው አዲስ መረጃ ተጠርጣሪውን በጥብቅ እንዲፈለግ አድርጓል። የአንደኛው ተጠርጣሪ የቅርብ ጓደኛ ነው የተባለና ከዚህ ቀደም በነፍስ ማጥፋት ወንጀል ተፈርዶበት ዓመታትን በማረሚያ የቆየ ስለመሆኑ ተሰምቷል። ድርጊቱን ከሰጠኝ ጋር ሊፈጽሙት እንደሚችሉ የጠረጠሩ ጠቋሚዎች በየአቅጣጫው በፍለጋ፣ በክትትል ማሰስ ይዘዋል።

ዋና ሳጂን መንግስቱ ታደሰ የወንጀል ምርመራውን ሊያሳዩ የሚችሉ መረጃዎችን ማጣራት ይዟል። ወንጀሉ በማንና ለምን ተፈጸመ? በድርጊቱስ ማን ተጠቃሚ ይሆናል የሚሉትን ወሳኝ ሀሳቦች በተግባር ለመፈተሽ ጥረቱ ተጠናከረ።

የምርመራ ቡድኑ ተጠርጣሪዎቹ ይገኙባቸዋል በተባሉ ስፍራዎች በህግ ጥላ ስር ለማዋል ክትትሉን አጠናከሯል። ወንጀሉ በተፈጸመ በአራተኛው ቀን ለፖሊስ አንድ ጥቆማ ደረሰ። ዋናው ተጣርጣሪ ሰጠኝ ታደሰ በአንድ ጫካ ተደብቆ አምልጦ ለመውጣት መሞከሩ ተሰማ።

ፖሊስና የአካባቢው ነዋሪ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር አድርጎ በህግ ጥላ ስር አዋለው። ፖሊስ ሰጠኝን ለጥያቄ ሲያቀርብ የወንጀል ድርጊቱን መፈጸም ያለመፈጸሙን እንዲያረጋግጥለት ጠየቀው። ተጠያቂው ለምላሹ አላንገራገረም። ድርጊቱን በትክክል ለመፈጸሙ በሰጠው ቃል አረጋገጠ።

ፖሊስ ጥያቄውን አላበቃም። ለግድያው መፈጸም ምክንያትና ሰበቡን እንዲያስረዳ ዕድል ሰጠው። ሰጠኝ የጌታቸውን ሕይወት ለማጥፋት መነሻ የሆነው የቡና ገለባው ንግድና ያስከተለበት የቅናት መንፈስ ስለመሆኑ አስረዳ። ተጠርጣሪው በዚህ አላበቃም፤ ድርጊቱን የፈጸመው ሲሳይ ከተባለ ጓደኛው ጋር ስለመሆኑ አረጋገጠ።

### የፖሊስ ፍስጋ...

ፖሊስ የተጠርጣሪውን ሙሉ ቃል መዝግቦ እንደጨረሰ ሁለተኛውን ተጠርጣሪና ለወንጀሉ ተባባሪ ነው የተባለውን ግለሰብ ማሰስ ጀመረ። ሰጠኝ ድርጊቱ ከተፈጸመ ምሽት በኋላ ግለሰቡን እንዳላየው አረጋግጧል። ከአካባቢው በተገኘ መረጃ መሠረት ሲሳይ ይገኝበታል ከተባለው የሀና ማርያም አካባቢ ፍለጋው ተጠናከረ። በተፈላጊው ስምና አድራሻ የተገኘ ሰው አልነበረም።

ፖሊስ ባደረገው ጥብቅ ምርመራና አሰሳ ሲሳይ የሚባል ግለሰብ ያለመኖሩን አወቀ። ሰጠኝ የሕግን አቅጣጫ ለማሳት የፈጠረው ስያሜ መሆኑ ተረጋገጠ። የተፈላጊው ትክክለኛ ስም ሲሳይ ሳይሆን አበበ መርኔ ነው። ይህ ሲታወቅ የፖሊስ ዓይኖችና ጆሮዎች ነቁ። በተፈላጊው አበበ ላይ የሚደረገው ፍለጋ በተለየ ጥንቃቄ ተጠናከረ። ከፖሊስ እጆች የገቡት የአበበ ፎቶግራፎች ፍለጋውን ለማፋጠን አገዙ።

ጥቂት ቆይቶ ፖሊስ ግለሰቡ ከዚህ ቀድሞ በነፍስ ማጥፋት ወንጀል ተከሶ አስራ ስድስት ዓመት እንደተፈረደበትና ስምንት ዓመት ታስሮ በምህረት እንደተፈታ ደረሰበት። የእሱም መተዳደሪያ የቡና ገለባ ሽያጭ እንደነበር ታወቀ።

የሁለተኛውን ተጠርጣሪ ዱካ ለማግኘት ፍለጋውን የጀመረው ፖሊስ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ቀድሞ ታስሮበት ነበር ወደተባለው የደብረብርሀን ከተማ አቀና። በአካባቢው የተገኙት የምርመራ ቡድኑ አባላት ከስፍራው ደርሰው መረጃዎችን ሰበሰቡ። ግለሰቡ ወንጀሉን በፈጸመ ሰሞን በሕገወጥ የመሣሪያ ዝውውር እጅ ከፍንጅ ተይዞ በጊዜ ቀጠሮ ላይ እንደሚገኝ ታወቀ።

የምርመራ ቡድኑ አባላት በእጃቸው ያለውን ፎቶግራፍ ከፍርድቤት ማዘዣ ጋር ይዘው ደብረብርሃን ማረሚያ ቤት ደረሱ። እንደተባለው ሆኖ ተፈላጊው አበበ ከማረሚያ ቤቱ በእስር ላይ ሆኖ ተገኘ። ፖሊስ ህጋዊ አካሄዱን ተከትሎ ተጠርጣሪውን በእጁ ለማስገባት ጥረት አደረገ። የወንጀሉ ክብደትና ያለው መረጃ ሚዛን ደፍቶ ቡድኑ ተፈላጊውን ተጠርጣሪ ወደ አዲስአበባ ይዞ እንዲሄድ ተፈቀደለት።

አበበ በምርመራው ሂደት ቃሉን ሲሰጥ ከሟች ጌታቸው ጋር ከዓይን እይታ በቀር ትውውቅ እንዳልነበረውና ወንጀሉን የፈጸመው ለጓደኛው ሲል እንደሆነ ተናገረ። ፖሊስ የሁለቱን ተጠርጣሪዎች ቃል በበቂ ማስረጃዎች ሰንዶ በፎረንሲክና በቴክኒክ ማስረጃዎች በማጠናከር አዘጋጀ። ተጠርጣሪዎቹ ክስ ይመሰረትባቸው ዘንድም መዝገቡን ወደ ዓቃቢ ሕግ አስተላለፈ።

## ውሳኔ...

በበቂ ማስረጃዎችና መረጃዎች ተጠናክሮ የቀረበለትን ክስ ሲመረምር የቆየው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድቤት አራዳ ምድብ ችሎት በተከሳሾቹ ላይ የመጨረሻውን ፍርድ ለማሳለፍ በቀጠሮ ተገኝቷል። ፍርድቤቱ ቀደም ሲል ተከሳሾቹ በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ መሆናቸውን አረጋግጦ የክስ መከላከያቸውን እንዲያቀርቡ ዕድል ሰጥቷል። ሁለቱም ተከሳሾች ስለ ወንጀሉ ፈጽሞ አላስተባበሉም።

ፍርድ ቤቱ በዕለቱ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ሁለቱ ባልንጀሮች በቂም በቀል ተነሳስተው ላጠፉት የሰው ሕይወት እያንዳንዳቸው እጃቸው ከተያዘበት ጊዜ አንስቶ በሚታሰብ የሃያ ዓመት ጽኑ እስራት «ይቀጡልኝ» ሲል ውሳኔውን በማሳለፍ መዝገቡን ዘግቷል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ከዕቃው ዋጋ በላይ ለጫኝና አውራጅ…

**ዋለልኝ አየለ**

የጫኝና አውራጅ ሥራ ለጫኝ አውራጆችም ለመንገደኞችም ጥሩ ነገር ነው። ለጫኝና አውራጆች ሥራ ነው፤ ገቢ ያገኙበታል። ለመንገደኞች ደግሞ መያዝ የማይችሉትን ዕቃ የሚያስይዙበትና የቱን ይገዙ የቱን ልተወው ከማለት የሚወጡበት ነው። መጫንና ማውረድ ሥራና የበርካታ ዜጎች የኑሮ መሠረትም ነው።

የጫኝና አውራጅ ሥራ በአብዛኛው በመናኸሪያዎች፣ በእህልና መሰል በረንዳዎች በስፋት ይሠራል። በመሠረቱ ዕቃን ከመኪና ማውረድና ማውጣትን ሁሉም ሰው በቀላሉ ሊከውነው አይችልም። የተጓዦችን ዕቃ መጫንና ማውረድ፣ እህል፣ ሲሚንቶ፣ ወዘተም ካለ ጭኝና አውራጅ ሊሆኑ አይችሉም። ሥራዎቹ በዚህ ሥራ የተሠማሩ ሰዎችን ይፈልጋሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ከሥራ ዕድል ፈጠራ ጋር በተያያዘ ሥራው እየተስፋፋ ይገኛል። በአዲስ አበባ ከተማ የማስፋፊያ ስፍራዎች በተለይም እንደ ኮንዶሚኒየም ባሉ መንደሮች ተስፋፍቷል።

ይሁንና ጫኝና አውራጆች የሚጠይቋቸው የተጋነኑ ክፍያዎች፣ ሳይፈቀድላቸው ወይም በዋጋ ሳይግባቡ የንብረት ባለቤቶች ሳይፈልጉ እኛ ነን ማውረድም መጫንም ያለብን እያሉ የሚሉበት ሁኔታ ከባለንብረቶች ጋር አለመግባባት እንዲከሰት ከማድረጋቸውም በላይ ለግጭትም ሲዳርግ የሚችል ሁኔታ እየፈጠረ ነው የሚሉ ጥቆማዎች ይደመጣሉ። ወንጀሎች እየተፈጸሙ ስለመሆናቸውም መረጃዎች ያመለክታሉ። አሁንም በጫኝ አውራጆች ላይ ሮሮዎች በርክተዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ የማስፋፊያ መንደሮች በተለይም በኮንዶሚኒየሞች አካባቢ ወጣቶች ተደራጅተው ይህን ሥራ እንሠራለን በሚሉ ወገኖች፣ ዝርፊያ በሚመስል መልኩ እየተፈጸመ ያለው የክፍያ ጥያቄና ውዝግብም በእጅጉ ያሳስባል።

ይህን ሁኔታ ለማብራራት ከሁለት ዓመት በፊት ያስተዋልኩትን አንድ ገጠመኝ እጠቅሳለሁ። በ2012 ኅዳር ይሁን ታኅሣሥ ወር አካባቢ ነው። አንድ ጓደኛዬ ቱሉዲምቱ አካባቢ ወደ ተከራየው ጋራ መኖሪያ ቤት አካባቢ ሄድን። አካባቢው ገና እየደረስን እያለ ከ10 የማያንሱ ወጣቶች መኪናው ግርርር ብለው ሰፈሩበት። መኪናው ቦታው ደርሶ እንደቆመም ከባለንብረቱ ጋር ገና ንግግር ሳይጀመር ወጣቶቹ ጭነቱን መፍታት ጀመሩ። እኔ እንዲህ ዓይነት ነገር አጋጥሞኝ ስለማያውቅ የአካባቢው ሰዎች ለትብብር የመጡ መስሎኝ በቅንነታቸው ተገርሜም ነበር።

**ኮማንደሩ በዚህ ጉዳይ ሳይ በተሠሩ ወንጀሎች የታሰሩ፣ ጉዳያቸው በሕግ እየታየ ያሉ መኖራቸውን ጠቅሰው፤ በቀጣይ እንዲህ ዓይነት ጥፋቶችን ለማስቀረት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ይሄ እርምጃ ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት**

ጓደኛዬ አሠራሩን ስለሚያውቅ ከማውረዳቸው በፊት ዋጋ ለመደራደር ማባበል ጀመረ። ጫኝና አውራጅ መሆናቸውን ሳውቅ «እኛው እናወርደዋለን፤ አያስፈልግም!» አልኩ። እውነት ለመናገር አብዛኛውን ዕቃ በእኛው አቅም ሊወርድ የሚችል ነበር። ለእዚህም ጭምር ነው እኛ ለምን አናወርደውም ያልኩት። በመንገድና በአንዳንድ ፕሮጀክቶች የራስ ኃይል የሚባል ነገር እንዳለ ታውቃላችሁ፤ ሌላ ተቋራጭ የማያስፈልግበትን ሁኔታ ለማመልከት። እኔ በራስ ኃይል ለማውረድ ነበር ፍላጎቴ። በቤተሰብ አቅም።

ለካ በዚያ አካባቢ ዕቃውን በጫኝና አውራጅ ማስወረድ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ ነው። ጓደኛዬም ግዴታ መሆኑን ስለሚያውቅ መደራደሩን ቀጠለ፤ የሚገርመው ድርድሩም በልመና ነው። የሚገርመው ነገር በዋጋ ሳይስማሙ ግማሽ ያህል የሚሆነው ዕቃ ወርዷል። የእነርሱ ጥያቄ «ቤቱን አሳየን!» የሚል ብቻ ነው። እኔም ነገሩ ወዲያው ገባኝና የራሳቸው ጉዳይ ብዬ ዝም አልኩ። ሲጨቃጨቁ ቆይተው የሰጣቸውን ሰጥቷቸው ጉዳዩ ተቋጨ!

በኋላ በሚገባ ሲያስረዱኝ እኔ አጋጥሞኝ ስለማያውቅ እንጂ በየትኛውም የጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ነዋሪው ቤት ቀይሮ ሲገባ እንደዚሁ ነው። ለካስ በየአካባቢው ይህንኑ ሥራ የሚጠባበቁ ወጣቶች አሉ።

ችግሩ ከዚህም በላይ የከፋ እየሆነ ነው። ቤት ተከራይተው ወደ ኮዶሚኒየም መንደር የሚገቡ ሰዎች ይህን ውዝግብና ዘረፋ በመስጋት በውድቅት ዕቃቸውን ከነበሩበት ቦታ ጭነው በውድቅት ወደ አዲሱ ቤት እስከ መግባት ደርሰውም እንደነበር አውቃለሁ። አሁን እሱም መቻሉን እንጃ።

ነገሩን ያስታወሰኝ ከትናንት በስቲያ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የሚዲያ ዘርፍ ኃላፊ ምክትል ኮማንደር ማርቆስ ታደሰ ጫኝና አውራጅን በተመለከተ ለሸገር ኤፍ ኤም 102.1 የሰጡት መረጃ ነው። ምክትል ኮማንደሩ «ቁሳቁሶችን እኛ ብቻ ነን የምናወርደው፣ እኛ ብቻ ነን የምንጭነው» ብለው በሰው ንብረት ራሳቸው ይወስናሉ። በሌላ በኩል ተመጣጣኝ ክፍያ አይጠይቁም፤ የሚያስማማና የሚያቀራርብ ክፍያ አይጠይቁም። የሚገርመው ደግሞ እርስበርስ የሚጣሉበት ሁኔታም አለ። በዚህ መሃል ንብረት ይወድማል፤ የአካል ጉዳት ይደርሳል። ምንም በማይመለከተው ሰው ላይ ጉዳት ይደርሳል። ባለቤቶችን ያስጨንቃሉ፤ «እኛ ካላወረድነው እናወድመዋለን» እስከ ማለትም ይደርሳሉ ሲሉ ነበር ያብራሩት።

እንግዲህ ሰው በራሱ ንብረት ማዘዝ አልቻለም ማለት ነው። ይሄ ሥራ ሳይሆን ወደ ዘረፋነት የተጠጋ ነው። «እኛ ካላወረድነው እናወድመዋለን» ማለት ከውንብድናና ዘረፋ አይተናነስም። ሰውየው ምናልባት የጠየቁትን ገንዘብ መክፈል የማይችል ከሆነስ።

የተጋነነ ዋጋ መጠየቃቸው ሌላው ቅሬታ ነው። ዕቃው ከተገዛበት ዋጋ በላይ ክፍያ የሚጠይቁም እንዳሉ ይነገራል። ይህ ደግሞ ችግሩ ምን ያህል የከፋ እየሆነ እንደመጣ ያስገነዝባል። ይህን በግድ ለማስፈጸም ሲንቀሳቀሱ ባለቤቱም ቆሞ አይመለከትም፤ «እንዳትነኩ» የሚል እልህ መጋባት ውስጥ ይገባል።

ኮማንደሩ በዚህ ጉዳይ ላይ በተሠሩ ወንጀሎች የታሰሩ፣ ጉዳያቸው በሕግ እየታየ ያሉ መኖራቸውን ጠቅሰው፤ በቀጣይ እንዲህ ዓይነት ጥፋቶችን ለማስቀረት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል። ይሄ እርምጃ ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

ዕቃው የግድ ተሸካሚ የሚያስፈልገው ከሆነ እኮ እነሱን ከመጠቀም ውጪ ሌላ አማራጭ የለውም። መጫንና ማውረድ የግድ ጫኝና አውራጆችን ይፈልጋል። በተለይም በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ብዙ ወለሎችን መውጣት ሊኖር ስለሚችል ዕቃዎችን በቀላሉ ማውጣት የሚቻለው በእነዚህ ወገኖች ነው፤ ስለዚህ ጫኝና አውራጆች መፈለግ የምርጫ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን አስገዳጅም ነው። የሚያስፈልገው ወጣቶቹ ሥርዓት ይዘው የሚሠሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ብቻ ነው።

ጫኝና አውራጆች ሊፈልግ የሚገባው ግን ባለቤቱ እንጂ በጫኝና አውራጅነት እንሠራለን የሚሉት ወጣቶች መሆን የለባቸውም። ወጣቶቹም ተሸካሚ የማያስፈልገውን ዕቃ ሁሉ ካልያዝን እያሉ መጣላት ለራሳቸውም ለሥራቸውም አይጠቅማቸውም።

ስለዚህ ሥራው በስምምነትና በተመጣጣኝ ዋጋ መሠራት አለበት። ሁለቱንም ወገኖች የሚጠቅመው ይኸው ነው። ካለበለዚያ ግጭት ሊከተል ይችላል፤ ግጭቱን የሚመነዝሩ ወገኖች ደግሞ ሌላ ግጭት የሚፈጥሩበት ዕድል ይፈጠራል። እንዲህ ዓይነት ድርጊቶችን ፖሊስ በቅርበት ሊከታተል ይገባዋል።

በነገራችን ላይ እነዚህ ጫኝና አውራጆች ከእዚህ ሥራቸው ውጪም መንግሥትና ሕዝብን እየጠቀሙም መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል። በሕጋዊ መንገድ ቢሰሩ እና ጥሩ ለሰሩትም ምሥጋና እና ዕውቅና ቢሰጣቸው መልካም የሆኑ ጫኝና አውራጆችም አሉ። ምክትል ኮማንደር ማርቆስ ለሸገር እንደገለጹት፤ ብዙ ሕገ ወጥ ዕቃዎች ሲዘዋወሩ በእነዚህ ጫኝና አውራጆች ጠቋሚነት ተይዘዋል። የጦር መሣሪያ ወደ ግለሰብ ቤት ሲገባ እና ከግለሰብ ቤት ሲወጣ የማወቅ ዕድል ሊኖራቸው እንደሚችልም መገንዘብ ይገባል። በሕጋዊ መንገድ በኃላፊነት በሚያገለግሉት ጫኝና አውራጆች የጦር መሣሪያዎች ሲዘዋወሩ የተያዙበት ሁኔታም ለእዚህ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ይህም የጫኝና አውራጅ ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን የሚያስረዳ ሌላ መረጃ ነው።

እናም ጫኝና አውራጆች ሥርዓት ይዘው እንዲሠሩ ማድረግ ላይ አተኩሮ መሥራት ያስፈልጋል። ሕጋዊ የሆኑ እና ኃላፊነት የሚሰማቸው ጫኝና አውራጆች እንዳሉ ሁሉ አግባብ ባልሆነ መንገድ የሚሄዱ አሉና ከድርጊታቸው እንዲታረሙ ማድረግ ይገባል። የማይታረሙም ከሆነ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ ተገቢ ነው።

ኅብረተሰቡ ከሕገወጦቹ ጫኝና አውራጆች መታደግ ይገባል፤ አሁን ሮሮው በዝቷልና። ኅብረተሰቡን በመታደግ አብዛኞቹን ጫኝና አውራጆችንና ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል የፈጠረውን ይህን ሥራ መጠበቅም ይቻላል። ይህን ሥርዓት በማስያዝ በኩል ሥራውን የሚመራው መንግሥታዊ አካል ኃላፊነት አለበት። ፖሊስም ችግር ሲፈጠር ሪፖርት የሚደረግለት እንደመሆኑ ክትትሉን ማጥበቅ፤ የኅብረተሰቡን ቅሬታ አዳምጦ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

# ዓለም አቀፍ

## የሩሲያ ግዙፏ የጦር መርከብ በጥቁር ባሕር ሰመጠች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ለሩሲያ ትልቅ ብሔራዊ አርማና ብሔራዊ ኩራት ሆና የቆየችውና ሞስኮቫ በሚል ስም የምትታወቀው እጅግ ግዙፏ የጦር መርከብ በጥቁር ባሕር ሰመጠች።

የሩሲያ መከላከያ ሚኒስትር ባወጣቸው መግለጫ ሞስኮቫ የሰጠመችው ረቡዕ ዕለት በፍንዳታ ከተጎዳች ከሰዓታት በኋላ ነው።

ከፍንዳታው በኋላ ጥገና እንዲደረግላት ወደ ሰቨስተፖል ወደብ አካባቢ እየተጠጋች ነበር ተብሏል። ሆኖም የባሕር ወጀብ አንገላቷት መቋቋም ባለመቻሏ መስመጧን ሩሲያ አምናለች።

በሞስኮቫ የነበሩ ከ500 በላይ የሩሲያ ባሕር ኃይል አባላትም ወደ ሌላ መርከብ ተወስደው ሕይወታቸው መትረፉም ተነግሯል።

ዩክሬን በበኩሏ የዝነኛዋና ታሪካዊቷን መርከብ ሕይወት የቆረጥኩት እኔ ነኝ እያለች ነው። ሞስኮ ግን ይህን ታስተባብላለች።

ሞስኮቫ ዕድሜዋ 40 ዓመት ያለፈው ሲሆን በጥቁር ባሕር የጦር መርከብ የሩሲያ መተማመኛና ብሔራዊ ኩራት ተደርጋ የምትታይ ነበረች።

የዩክሬን ወታደራዊ አዛዦች ሞስኮቫን ኔፕቱን የሚባል ሚሳኤል በማስወንጨፍ ነው መርከቧ ላይ ጉዳት ያደረስነው ይላሉ።

ኔፕቱን ሚሳኤል ሩሲያ ክሪሚያን በ2014 እ.አ.አ ከያዘች በኋላ በጥቁር ባሕር አካባቢ ያለባትን የደኅንነት ስጋት ለመቅረፍ ዩክሬን ያመረተችው ተወንጫፊ መሣሪያ ነው።

አንዳንድ የጦር አዋቂዎች ኔፕቱን ሚሳኤል ሩሲያ በአካባቢው ያላትን ውስብስብ የአየር መቃወሚያ አልፎ ግዙፏን የጦር መርከብ ሞስኮቫን ሊመታ ስለመቻሉ ይጠራጠራሉ።

ያም ሆነ ይህ ሞስኮቫን ለዚህ የዳረጋት ምን እንደሆነ ከገለልተኛ ወገን እስከ አሁን የተባለ ነገር የለም።

ሞስኮቫ የጦር መርከብ በሶቭየት ኅብረት ጊዜ ተገንብታ ወደ ሥራ የተሠማራችው እንደ አውሮጳዊኑ በ1980ዎቹ ነበር።

ሞስኮቫ ግዙፍ ሚሳኤል ተሸካሚ የጦር መርከብ በሶሪያ ግጭት ጊዜ የሩሲያ ወታደሮችን በከፍተኛ ሁኔታ ማገዟ ይነገራል።



እጅግ ውስብስብና ግዙፍ የጦር መሣሪያዎችን መሸከም የምትችለው ሞስኮቫ ከ12ሺህ ቶን በላይ ክብደት አላት።

እንዲህ ዓይነት ግዙፍ የጦር መርከብ ሲሰጥም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ሞስኮቫ የመጀመሪያዋ ናት።

## የሰሜን ኮሪያ መረጃ መንታፊዎች 615 ሚሊዮን ዶላር ዋጋ ያለው ክሪፕቶከረንሲ መዝረፋቸውን አሜሪካ ገለጸች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሰሜን ኮሪያ መረጃ መንታፊዎች የጌም ኩባንያዎችን ኢላማ በማድረግ 615 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ክሪፕቶከረንሲ መዝረፋቸውን አሜሪካ አስታውቃለች።

በሰሜን ኮሪያ የሚደገፉ የሳይበር መረጃ መንታፊዎች ባለፈው ወር ከታዋቂው የኦንላይን ጌም ‘አክሲ ኢንፊኒቲ’ 615 ሚሊዮን ዶላር ዋጋ ያለው ክሪፕቶከረንሲ መዘረፉን ነው አሜሪካ የገለጸችው።

የመንታፊዎቹ ኢላማ የሆነው ይህ የጌም ኩባንያ ጌሙን ለሚጫወቱ ወይም ለሚገበያዩ ሰዎች ክሪፕቶ የሚያገኙበትን ሥርዓት ዘርግቷል።

ታዲያ ይህ የሰሜን ኮሪያ ጠላፊዎች ዝርፊያ በክሪፕቶከረንሲው ዓለም ትልቁ ነው ተብሏል።

የአሜሪካ ባለሥልጣናት ይህ ዘረፋ የተፈጸመው በሰሜን ኮሪያ ዋና የስለላ ቢሮ ቁጥጥር ሥር እንደሆነ በሚታመነው “ላዛረስ” በተባለ ቡድን ነው ብለዋል።

ኤፍቢአይ ትናንት ባወጣው መግለጫ፣ ከሰሜን ኮሪያ መንግሥት ጋር ግንኙነት ያላቸው ላዛረስ እና ኤፒቲ38 የተባሉ የሳይበር መረጃ መንታፊ ቡድኖች ለስርቆቱ ተጠያቂ መሆናቸውን በምርመራ ማረጋገጥ ችያለሁ ብሏል።

ላዛረስ የተባለው ቡድን እንደ አውሮፓውያኑ በ2014 የሶኒ ፒክቸርስ የመረጃ መረብን ጥሶ በመግባት ምስጢራዊ መረጃዎችን በአደባባይ መዘርገፉ ከተሰማ በኋላ ታዋቂነትን አግኝቷል።

ቡድኑ ይህንን ድርጊት የፈጸመው በወቅቱ የሰሜን ኮሪያውን መሪ ኪም ጆንግ ኡን ለመግደል የሚደረግ ሙከራ ላይ የሚያጠነጥን ይዘት ያለው ‘ዘ ኢንተርቪው’ የተባለው ፊልም እንዳይለቀቅ ሲጠይቅ ነበር።

በሰሜን ኮሪያ ላይ የተጣለውን ማዕቀብ የሚከታተለው የተባበሩት መንግሥታት ቡድን ፒዮንግያንግ የተዘረፉ ገንዘቦችን የኒውክሌር እና የባላስቲክ ሚሳኤል




ፕሮግራሞቿን ለማጠናከር እና ማዕቀቧቹን ለመቋቋም እንደምትጠቀምባቸው አሳውቋል።

ሰሜን ኮሪያ የሳይበር ወንጀሎችን ጨምሮ በሕገ ወጥ ተግባራት ላይ የምትሳተፍበት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደሆነ እና ትርፉንም ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎቿ እና ባሊስቲክ ሚሳኤል መርሃ ግብሯቿን ለማጠናከር እያዋለች መሆኑን የአሜሪካ ግምጃ ቤት መግለጹን ቃል አቀባዩን በመጠቀስ ሮይተርስ ዘግቧል።

እንደ አውሮፓውያኑ በ2020 የወጣው የአሜሪካ ወታደራዊ ሰነድ የሰሜን ኮሪያ የሳይበር ጥቃት ተግባር ቢያንስ በ1990ዎቹ አጋማሽ እንደጀመረ እንዲሁም ቢሮ 121 ተብሎ የሚጠራ እና ወደ 6 ሺህ የሚጠጋ ጠንካራ የሳይበር አባላት እንዳለው አሳይቷል።

ይህ ቡድን ቤላሩስ፣ ቻይና፣ ሕንድ፣ ማሌዥያ እና ሩሲያን ጨምሮ በበርካታ አገራት እንደሚሠራ አመላክቷል።

ብሎክቼይን የሚተነትን ኩባንያ ባወጣው መረጃ መሠረት የሰሜን ኮሪያ መረጃ መንታፊዎች ቢያንስ 400 ሚሊዮን ዶላር ዋጋ ያለው ዲጂታል ገንዘብ እንደ አውሮፓውያኑ በ2021 ባደረሷቸው ቢያንስ ሰባት ጥቃቶች ዘርፈዋል።

ይህም በእሲያ አገራት ውጤታማው እና እጅግ ስኬታማ ከሆኑት የሳይበር ምንተፋዎች አንዱ ነው ብሏል።

# መጋቢ አዕምሮ

# በወኔ፤ ከወኔ!

በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ

በገጠሩ የአገራችን ክፍል ዛሬም ድረስ የዘለቀ የማህበራዊ ሕይወታችን ማሳያዎች መካከል ቡናን እየተጠራሩ አብሮ የመጠጣት ባህላችን ይገኝበታል። ተከታታይ ፊልም እያዩ እቤት ውስጥ ከመቀመጥ ተራብተራ እየዞሮ ከጎረቤት ጋር ቡና መጠጣት ከፍያለ ትርጉም መሆኑን የሚያሳይ ባህል። በየቀኑ አብሮ ከጎረቤት ጋር ቡና የሚጠጣበት፤ አብሮ የሚኖርበት መድረክ።

በየጊዜው በመድረኩ ላይ ብዙ ሃሳቦች ተነስተው ይጣላሉ። ሰዎች ለውሳኔ የሚረዳቸውን ምክር ይቀያየራሉ፤ የፈራው እንዲበረታ፣ የተሳሳተውን ለማረቅ የሚሆን ምክር ከአንዱ ወደሌላው ይተላለፋል። በብዙ ጉዳዮች ላይ የመረጃ ልውውጥም ይደረጋል። በአጭሩ አብሮነት ትርጉም የሚሰጥበት ስፍራ ልንለውም እንችላለን።

በየሰፈሩ ካሉ የጎረቤታሞች መድረኮች ወደ አንዱ ዛሬ ጎራ ብለን ከሚለዋወጡት የሃሳብ መዓድ ለራሳችን የሚጠቅመንን ለመውሰድ አስበናል። የውይይታቸው መነሻ ግብጽ ስትሆን መዳረሻቸው ደግሞ ኢትዮጵያ ያካደረጉ ጎረቤታሞች። 'ግብጽ በኢትዮጵያ ላይ የነደፈችው፤ ኢትዮጵያን በብዙ አቅጣጫ አዳክሞ የህዳሴው ግድብ ፕሮጀክት እንዳይሳካ የማድረግ ውጥን አለ' በሚል ውይይት ተጀምሮ የጦፈ ክርክር ላይ ደርሷል።

የክርክሩ ተካፋይ የሆነ አንዱ ጎልማሳ ሃሳብ በቁጭት እየሰጠ ነው፤ «ግብጽ ይህን ሁሉ ነገር በአዙሪት ለማድረግ ከምትሄድ ለምን በአጭሩ ጦርነት አትገጥመንም? ኢትዮጵያ እስከመቼ ድረስ የግብጽ ሰለባ ሆና ትኖራለች? በቃ ጦር ተማዘን ይለይልን፤ የምን ፈራተባ ነው!» አለ። የጎልማሳውን ሃሳብ ተከትሎ ሌሎች ጎረቤታሞችም የየራሳቸውን መስነዘር ቀጠሉ። «ምን ሆነሃል፤ ግብጽ ቀጥተኛ ጦርነት ምን ያደርግላታል? እኛን እርስበእርስ እንድንባላ ካደረገች እኛ የእርሷን ጦርነት እየተዋጋን ስለሆነ ለምን ጠመንጃ መዛ ዜጓቿን ታስጨርስ? እኛ ነን እንጂ የእርሷ መጠቀሚያ ስንሆን ቆመን መመልከት ያልቻልነው» ሲል በቁጭት ተናገረ።

ሌላይቱ የቡናው ህብረት ተካፋይ የሆነች የልጆች እናትም ቀጠል አድርጋ «እኔ የማይገባኝ ነገር እውን በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ ከሌላ አገር ጋር ጦርነት ውስጥ ብትገባ ከዚህ ቀደም ጣሊያንን በተዋጋንበት ወኔ የምንዋጋ ይመስላችኋል? አሁን ይህ ወጣት ወኔ ኖሮት የውጭ ወራሪ ኃይልን መመለስ ይችላል? እርስ በእርሳችን ለመጨራረስ ካልሆነ እንደው ማን ይሙት ተደራጅቶ የሚመጣን የውጭ ኃይል ለመመከት የሚያስችል አቅም አለን? በተለይ የወኔ አቅም፤ የአገር መውደድ አቅም። ያሰቡትን ካላሳካሁ እምቢ የሚያስብል አቅም፤ በግለት ውስጥ ሆኖ ለመስዋዕትነት የመቅረብ አቅም። ይቅርታ አድርጉልኝና አይደለም ለጦርነት የሰፈራችንን ጽዳት ለመጠበቅ የሚያስችል ወኔ የለንም» አለች። የቡና መድረኩ ክርክር ከግብጽ ተነስቶ ስለ «ወኔ» ሆነ።

ቡና የማቀበሉን ኃላፊነት ወስዳ ቡና እያቀረበች ያለች ታዳጊ የአስራሁለት አመት የስድስተኛ ክፍል ተማሪዋ ስለ ወኔ የተነገረው ውስጧን ከነከነው። በትምህርት ቤት የተማረችው ኢትዮጵያውያን የውጭ ወራሪ ኃይልን መክተው መመለሳቸውን፤ ጣሊያንን ማንበርከካቸውን፤ ዓድዋ የነፃነታቸው ምልክት አድርገው መኖራቸውን ወዘተ። ዛሬ በቡናው መድረክ ላይ የሚሰማው ነገርግን ትናንት የተማረችው ተረትተረት የሆነ መሰላት። በትናንት እና በዛሬ መካከል ግጭት በውስጧ ተፈጠረባት። ነገ መምህሯን ለመጠየቅ ራሷን አዘጋጀች። ወኔ ስለከዳው ትውልድ፤ እርስበእርሱ እየተባላ እንደሆነ ክስ ስለሚቀርብበት ትውልድ ጠይቃ ትናንትንና ዛሬን ለማስታረቅ አሰበች። በወኔ እርስበእርስ ለመጣላት ምክንያት የሚፈልግ፤ በወኔ ግን አንዳች ቁምነገር መሥራት አይችልም የተባለው ትውልድ አካል በመሆኗም ቅሬታ ተሰማት። በውስጧ ያለው ህልም አንዳች ቁምነገር መሥራት ነውና።

### ወኔ፤

ዛሬ ስለ ወኔ እናንሳ። ወኔ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ያሰበውን ለማሳካት በሚያደርገው ጉዞ ውስጥ አቅም የሚሰጥ ኃይል አድርገን ልንተረጉመው እንችላለን። አነቃቂው ቡና እና የአካባቢ ሰዎች የሚፈጥሩት መነቃቃት በወኔ ብዙ ነገሮች እንዲሉ አድርጓቸዋል። ከቡናም ሆነ ከሌሎች አነቃቂ ነገሮች ባሻገር በራዕይ በኩል አድርጎ የሚፈጠረው ወኔ ያለውን ፋይዳ እያሰብን ስለ ወኔ ነጥቦችን እናነሳለን። አስቀድመን ዙሪያችን ብንቃኝ ሁለት ሰዎችን እናገኛለን። ወኔ ያላቸው እና ከወኔ የተፋቱ ሰዎች። ሁልጊዜ ችግርን የሚያወሩ የወይኔ ሰዎችና ለመፍትሔ የሚኖሩ በወኔ የሚነሱ ሰዎች። ዛሬ እንደ ማህበረሰብ ለውጥ የምንፈልግባቸው አንድ ሺ አንድ ጉዳዮች ቢኖሩንም ይህን ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ወኔ ያላቸው ሰዎችን መቁጠር ብንጀምር ግን የምንቆመው ብዙም ሳንርቅ መሆኑን ማሰብ አይከብድም።

«ትውልዱ ወኔው የተሰለበ ነው» የሚለውን ክስ በጥሞና ብናስበው ሁላችንንም የሚመለከት መሆኑ እርግጥ ነው። ማናችን ስለማን አስተያየት እየሰጠን እንደሆነ ግልጽ ስለሆነ። ራሳችን ስለራሳችን እንደ ትውልድ መሆኑ ሊጠፋን ስለማይችል፤ ወይንም ሊጠፋን ስለማይገባ። ትውልዱ በለውጥ መንፈስ ተነሳስቶ አካባቢውን ቀይሮ፤ በድምሩ አገሩን ወደ ተሻለ አቅጣጫ አስገብቶ ማየትን ህልም ያደረገ ሰው በትውልዱ መክሰር ብዙ ቢል ሊፈረድበት አይችልም።

### ከግለሰብ እስከ ...፤

ወኔን ከግለሰብ ጀምሮ እንዲኖር ማስቻል የተገባ መሆኑን እንረዳለን። የውስጥ መነቃቃትና ያሰቡትን ለመፈጸም የሚያደርግ ኃይል ስለሆነ በግለሰብ ደረጃ ካልተገኘ ከግለሰብ በላይ ባለ የትኛውም ስብስብ ሊገኝ አይችልም። እንደግለሰብ በውትድርና ውስጥ ያለፉ ሰዎች ወኔያቸው ከሌላው ማህበረሰብ የተለየ ሆኖ መገኘት ወኔን በግለሰብ ደረጃ ለማምጣት የሚያስፈልገውን ሥራ በግልጽ ያሳያልና። ወታደሩም በወታደርነት ከመጠቀሱ በፊት እንደ ማንኛውም ተራ የማህበረሰቡ አባላት መካከል ስለነበረ።

ውትድርና ያለ ወኔ የሚታሰብ ባለመሆኑ በውትድርና ሳይንሱ አማካኝነት ሊሰጠው የሚገባ ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራበታል። ምክንያቱም ውትድርና በቀጥታ ከሞት ጋር መገናኘትን የሚጠይቅ ስለሆነ፤ ሞትን መድፈር ደግሞ ያለወኔ ሊታሰብ የሚችል ባለመሆኑ። ጠንካራ ወኔ ያለው ብዙ የታጠቀውን ትጥቅ ማስፈታት የሚያስችል አቅም ኖሮት በጦርነት ታሪኮች ውስጥ ተጽፎ ስለሚገኝ።

በመሆኑም በጦርነት ውስጥ በወኔ የደረጁ ጀግኖችን ማየት ቀላል ነገር ነው፤ ምክንያቱም ሥራው የሚጠይቀው በመሆኑ በየቀኑ የሚሠራበት ሥራ በመኖሩ። በውትድርናው በጀግንነት የሚጠቀሱትን ያህል ግን በንግድ፣ በመንግሥት ሥራ ውስጥ እንዲሁም በሌሎች እንቅስቃሴዎች ውስጥ በወኔ የሆኑ ሰዎችን ማግኘት ቀላል ሥራ አይደለም። በአንድ ድርጅት ውስጥ መሠረታዊ ለውጥን ለማምጣት የሚደረግን ሥራ በምናይበት ጊዜ የመጣው ለውጥ በመሪው በወኔና ድፍረት የተሞላ ውሳኔ ውጤት መሆኑን እንረዳለን። የመሪነት የሥራ መደብ ለመሪው ድፍረትን አይሰጥም ነገርግን ድፍረት ለመሪው የመሪነት የሥራ መደብን ያሰጠዋል እንጂ። ከግለሰብ እስከ አደባባይ ወኔ ያለው ትርጉም ትልቅ የሆነውም በዚህ ምክንያት ነው።

አንባቢ ሆይ፤ ሕይወትህን በተበረታታ፣ በተነቃቃና በወኔ እየመራህ ነው? ካልሆነ ለምን ብለህ ጠይቅ? ሥራህም ሆነ ማህበረሰባዊ አገልግሎትህንም እንደእዚያው። በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በርካታ ፕሮጀክቶች ተጀምረው ወደ ውጤት የማይመጡበትን ምክንያት ስንፈትሽ ልንዘረዝረው የምንችለው ብዙ ነገር ቢኖርም የወኔ መጉደል የራሱ ድርሻ ሊኖረው እንደሚችል ግን ሊካድ አይችልም። ሰዎችን በፍቅር የማገልገል ወኔ የሌለው ሰው በትንሽ ነገር ሰውን ወደ ማመናጨቅ ሊገባ ይችላል። ትልቅ ህልም ያለው ሰው ህልሙን እውን ለማድረግ የሚያስችል ወኔ ከሌለው እንዲሁ መዳረሻው የሃሳብ ዝርዝር ብቻም ይሆናል።

ስለሆነም ወኔ ያለውን ቦታ በአግባቡ ተረድተን ስለ ወኔ የምናነሳቸውን ነጥቦች አንባቢው ለትምህርቱ እንዲሆነው አንድ ብለን እንጀምር። ጥቂት ነጥቦችን በወኔ እናቀርባለን፤ አንባቢው በወኔ አንብቦ አብሮን "በወኔ፤ ከወኔ" ይበል።

### 1. የወኔ መገኛው ስፍራ የትነው? ግቡስ?

ወኔ የት እንደሚገኝ ጠይቅና ምላሽ አግኝ። ወኔ ከውጫዊ ሰውነትህ ላይ ቢፈለግ አይገኝ። ወኔ በውጫዊ አካልህ ላይ በተለያዩ መንገዶች የሚገለጥ ሊሆን ይችላል እንጂ በተጨባጭ ያለው ግን በውስጥህ ነው። እንደ መሪ የምትጋፈጠው ማንኛውም ፈተና የሚጀምረው ከውስጥህ ነውና በውስጥ ወኔ ሊፈጠርም ሆነ ሊሞት እንደሚችል መረዳቱ ይኑርህ። ወኔህን የሚፈትነውም ፈተና ከእዚህ የተለየም አይደለም። ፈተና ሲመጣ ከሚሠራቸው ሥራዎች መካከል ተስፋን መንጠቅ፤ ወኔን መስለብ፤ ጽናትን መሸርሸር ነው። የሳይኮቴራፒስት ባለሙያ የሆነው ሼልደን ኮፕ የተባለው ሰው ሁሉም ከባድ የሚባሉ ጦርነቶች ክፍያቸው ከውስጥ ነው ብሎ መናገሩ ለዚህም ይመስላል። ከውስጥ የሚሆን ከፍያ!

የወኔን ግብ ስናስብ ፍርሃትን እናነሳለን። በወኔ የምትጋፈጠውን ነገር እንዳትጋፈጥ ፊትአውራሪ ሆኖ የሚመጣው ፍርሃት ስለሆነ። ወኔ ማለት የፍርሃት አለመኖር ማለት አይደለም፤ ነገርግን የምትፈራውን ነገር ማድረግ ማለት ነው። ስለፈራህ ወኔ የለህም ማለት አይደለም፤ የፈራኸውን በማድረግ ውስጥ ወኔህ ሥራውን ይሠራል ማለት እንጂ።

የሰብዓዊ መብት ተሚጋቹ ማርቲን ሉተር ኪንግ እንዲህ ሲል አወጀ ትልቁ የሰው ልጆች መለኪያ በምቾት ጊዜ የሚገኙበት አቋም ሳይሆን በተግዳሮትና ግራአጋቢ ወቅቶች የሚቆሙበት ስፍራ ነው። እያልን ያለነው አሁን ግልጽ ነው፤ በጣም ግለጽ። ወኔ ግብ ልታደርግ የሚገባህን ነገር ማለትም ፍርሃትን አውልቀህ ጥለህ ማድረግ እንድትችል የሚያደርግ መሆኑን የሚያስረዳ። ግራአጋቢ በሆኑ ወቅቶች ማድረግ ያለብንን ከማድረግ እንዳንመለስ የሚያደርግ ኃይል መሆኑን የሚገልጽ።

ወኔ የሚመራው በመርህ እንጂ በይሆናል አይደለምና ከመከራው ባሻገር የሚታኝበት ቅኝት አለው። ስለምን ጉዳይ ምን አቋም መያዝ እንዳለብህና አቋምህን እንዴት እንደምታራምድ ማሰብ እንድትችል ልትሆን ይገባል። ስለምን ጉዳይ አቋም ይዘህ እንደምትቆም የማታውቅ ከሆነ ውጤታማ ሰው ልትሆን አትችልም። ሕይወት በአቋም የምትኖርለት ነገር ውስጥ የምትደምቅ በመሆኑ። በጽናት ስለምትቆምበት ነገር የሚኖርህ መሰጠት በሌሎች ፊት ጠንካራ ሆነህ የምትሳልበትን አቅም የሚጨምር ነው። ለዚህ ደግሞ ወኔ የሚኖረው ድርሻ ከፍተኛ ነው። ወኔ በግለሰብ ደረጃ ታጥሮ የሚቀመጥም ሳይሆን የሚባዛም የሆነ ለእዚሁ ነው።

### 2. የወኔ ብዜት

ስለ ወኔ ማሰብ ያለብን ሌላኛው ነጥብ ወኔ የሚባዛ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ወኔ ይባዛል፤ ከአንዱ ወደሌላው። የአበበ በቂላ በባዶ እግር ሮጦ አሸናፊ መሆን በአገራችን አትሌቲክስ ላይ ያለው ተጽእኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ማራቶንን በባዶ እግር ሮጦ ለመጨረስ መወሰን የሚፈልገው ውሳኔ በወኔ ውስጥ ብቻ ካልሆነ በምን ሊገኝ ይችላል? ወኔ ከአንድ ሰው ወደሌላ ሰው፤ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ የሚዘዋወርነው። ወንጌላዊ ቢሊ ግራም እንደተናገሩት ወኔ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የሚተላለፍ ነው። በአንድ ሰው ላይ የሚታይ ወኔ በሌሎች ላይ ያለውን ያበረታታል። በመሪዎች ላይ የሚታይ ወኔ ተከታዮችን ያነቃቃል፤ ሰዎችም መሪያቸውን እንዲከተሉም ያነሳሳቸዋል።

አብዛኛው ሰው በሕይወቱ ውስጥ ቦታ ካላቸው ሰዎች ጋር መሞጋገት እምብዛም አይፈልግም ማለትም ከሠራተኛ፣ የሥራ ባልደረባ፣ ቤተሰብ ወዘተ ጋር። ነገርግን መጋፈጥ ባለብህ ቦታ ስትጋፈጥ ለእውነት፤ ለመርህ፤ ለሕግ የሚገዙ ሰዎችን እያበዛህ ነው፤ ወኔ የሚባዛ ስለሆነ። ይህ በአንተ ሕይወት ውስጥ እውነት ከሆነ ያመለጡህን በወኔ ያልተመለከትካቸውን ነገሮች ቁጠርና ዛሬ ስለመፍትሔው ተነሳ።



### 3. ወኔ በሕይወታችን ውስጥ ምንያህል ይለካል?

ወኔ በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ድርሻ ለክተን በቁጥር ማስቀመጥ ብንችል ምንኛ ዕድለኛ በሆን ነበር። ያንን ማድረግ ባንችልም ማሰብ ግን የምንችልባቸው ቀዳዳዎች አሉ። ስለ ሕይወትህ ምን ያህል የተነሳሳህ ነህ? በሥራ ቦታ፤ በቤተሰብ ውስጥ፤ በግል ሕይወትህ ወዘተ ውስጥ ያለውን መነሳሳት መነሻ በመፈተሽ ምላሽ መፈለግ ይቻላል። ምናልባትም የሥራ ባልደረቦችህን እና የትዳር አጋርህን በመጠየቅ ወደ ምላሹ መቅረብ ይቻላል።

በእኔ እምነት ግን ነገሮችን በወኔ ማድረግ በሕይወታችን ያሰቡትን ማሳካት ግማሽ መንገድ ነው። በእያንዳንዱ ሰው ጉዞ ውስጥ ተጽእኗቸው ከፍተኛ የሆኑ ብዙ ነገሮች መኖራቸው ባይካድም ወኔ ግን ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚሰለፍ ነው።

ፍርሃት የሰውን ጉዞ እርቀት የመወሰን አቅሙ ለውይይት አይቀርብም። ወኔ ፍርሃትን ገፎ ያሰቡትን ለማሳካት አስቸጋሪ የሆነውን መንገድ ደልዳላ ያደርጋል። የሮማን የታሪክ አዋቂ እንደጻፈው ምቾትን የመጠበቅ መሻት የታላቅና ምርጥ ድርጅቶች ፈተና ነው። ነገርግን ወኔ ያለው ተጽእኖ በተቃራኒው ነው፤ በርን የሚከፍት እናም ዋናውን ምርጥ ጥቅምን የሚያመጣ፡ በማለት ይገልጻል። ወኔ በሕይወታችን ውስጥ ያለው ልኬት የሕይወታችን ጉዞ መወሰን የመቻል ያህል ነው ብለን ምላሽ ብንሰጥ አንሳሳትም።

ወኔ መልካም ጅማሬን ብቻ ሳይሆን የተሻለ ነገንም የሚሰጥ ነው። መልካም ጅማሮን የሚያደርጉ ብዙ ሰዎች አሉ፤ ነገርግን እንደጅማሬያቸው ነገዎቻቸው ሳይሆኑ የሚቀሩ። ምክንያት ከተባለ የሚገኘው መልስ የወኔ ማነስ ሆኖ ስለሚገኝ።

አንባቢ ሆይ በወኔ ለማደግ ካለህበት ሁኔታ ወጥተህ ለመዘርጋት ሞክር። ብዙ ሰዎች ለማድረግ የሚፈሩትን በሰዎች ፊት ቀርበህ ንግግር አድርግ። የምትሠራው ሥራ ምንም ይሁን ምን ፍርሃትን የሚፈጥር ነገር መጋፈጥህ ነውና ዋናው ነገር አድርገው።

ወደ አዲስ የሥራ ሕይወት ለማምራት ፍርሃት ሊሰማህ ይችላል። ሥራህን መተውና አዲስ የሥራ መስመር ውስጥ መግባት እንዳለብህ የምታምን ከሆነ አሁን የምትጋፈጥበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። በሚገባ በሁኔታው ላይ ለማሰብ ጊዜን ውሰድ። ከትዳር አጋርህ፣ ከግል-መካሪህ እናም ከታማኝ ጓደኛህ ወይንም ጓደኞችህ ጋር አውራበት። ይህን ማድረግ ትክክለኛው ተግባር ከሆነ አድርገው።

በወኔ ነገርህን ብትፈጽም ወደ ድል ትደርሳለህ። የምትከተላቸውን መሪዎች መከተል ከመጀመርህ በፊት ከወኔ አንጻር ገምግማቸው። በወኔ የራስህን ሥራ መሥራት፤ ከወኔ አንጻር የምትከተለውን መወሰን። መዳረሻህ በሕይወትህ ያሰብከውን አሳክቶ ማለፍ ስለሆነ ወኔ ትክክለኛው መነጽር ነው። ዛሬም በወኔ፤ ከወኔ።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ንቁ አእምሮ፤ ለሥራ የተጉ እጆች ለውጤት ያበቃሉ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አሁን አሁን አብዛኛው ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ባህላዊ አልባሳት አምረው፣ ተውበውና ደምቀው መታየታቸው የተለመደ ሆኗል። በተለያዩ መድረኮች ላይም ባለስልጣናት ሳይቀሩ በዚሁ በባህል አልባሳት ደምቀው ይታያሉ። ባህላዊ አልባሳቱን የሚጠቀመው ሰው ቁጥር ዕለት ዕለት እየጨመረ በመምጣቱም በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የባህል አልባሳት በዘመናዊ መልኩ ለገበያ እየቀረቡ ይገኛሉ።

አልባሳቱ በስፋት እየተለመዱ በመምጣታቸው በዘርፉ ለተሰማሩ በርካታ ባለሙያዎች ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር ከማስቻላቸው ባለፈም ባህሉን ለማስተዋወቅ ትልቅ ዕድል መፍጠር ችለዋል። በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ከተፈጠሩ የተለያዩ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች መካከልም በጨርቃ ጨርቅ ዘርፍ ተሰማርተው የባህል አልባሳትን ጨምሮ የተለያዩ አልባሳትን የሚያመርቱ በርካታ ኢንተርፕራይዞች ተፈጥረዋል።

መንግሥት ለኢንተርፕራይዞች የፈጠረውን ዕድል ተጠቅሞ ውጤታማ መሆን የቻሉ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የተደራጁ በርካታ ማህበራት በተለያዩ ክልሎችና የክልል ከተሞች ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል ከፍተኛ የንግድ ልውውጥ የሚካሄድባት በደቡብ ክልል በጌዲኦ ዞን የምትገኘው የዲላ ከተማ አንዷ ናት። የዝግጅት ክፍላችን በዲላ ከተማ በነበረው ቆይታ በከተማዋ ከሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት መካከል በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ተሰማርተው ውጤታማ መሆን የቻሉ የቤተሰብ አባላትን የመጎብኘት ዕድል ገጥሞታል።

የመንግሥት ሰራተኛ የነበሩት አቶ ዳዊት ሞገስ እና የቤት እመቤት የሆኑት ባለቤታቸው ወይዘሮ ገነት ሳሙኤል ነዋሪነታቸው በዲላ ከተማ ነው። ኑሮን ሲጀምሩ ቀላል የነበረ ቢሆንም ልጆች ተወልደው የቤተሰቡ አባላት ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ ግን ኑሯቸው እየከበደ በመምጣቱ በአንድ ሰው የወር ደመወዝ የሚገፋ አልሆነም ይላሉ።

ለኢኮኖሚ ጥያቄያቸው ምላሽ ለመስጠትና ኑሯቸውን አሸንፈው ለማሻሻል ያስችለናል ያሉትን የስፌት ሥራ በአንዲት ሲንጀር መኪና አንድ ብለው ጀመሩ። በዚህ እርሾ የተጀመረው ሥራ በአሁኑ ወቅት ሃብት ለማፍራት አብቅቷቸዋል። ኑሯቸው የተሻለ ሆኗል። ልጆቻቸውን አስተምረዋል። ከዚህ ባለፈም ለበርካቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል። የመሥሪያ ማሽኖቻቸውም ቢሆኑ ውጤታማ ለመሆናቸው አይነተኛ ምስክሮች ናቸው።

‹‹ወደ ልብስ ስፌት ሥራ ለመግባት ትልቅ ድርሻ ያላት ባለቤቴ ናት›› የሚሉት አቶ ዳዊት፤ ባለቤታቸው ወይዘሮ ገነት ከወላጅ አባታቸው የወረሱትን አንዲት ሲንጀር የስፌት መኪና እንዲሁም የሴቶች ቀሚስ የመስፋት ሙያ ይዘው በመኖሪያ ቤታቸው ደጃፍ ላይ ለሥራ ሲወጡ እርሳቸው የመንግሥት ሥራ ይሰሩ እንደነበር አጫውተውናል።

በመንግሥት ሥራ ረጅም ጊዜ ያሳለፉት አቶ ዳዊት፤ ባለቤታቸው በቤት ውስጥ የጀመሩት የልብስ ስፌት ሥራ ዕለት ከዕለት መሻሻል እያሳየ መምጣቱን ተረድተው ወደ ሥራው በመቀላቀል በጋራ ለመሥራትና ሥራውን ለማስፋፋት ወስነው የመንግሥት ሥራቸውን ለቀዋል። ሙሉ ጊዜያቸውን ከባለቤታቸው ጋር በማድረግ ዘርፉን ተቀላቅለዋል። ሥራቸውን እያስፋፉ ሲመጡም መንግሥት ያቀረበውን የመደራጀት ዕድል ተጠቅመው በጥቃቅንና አነስተኛ በመደራጀት ኖጺቾ ልብስ ስፌት ኢንተርፕራይዝን አቋቋሙ።

በወቅቱ ሥራውን ለማስፋፋት በቂ ገንዘብ ስላልነበራቸው በአካባቢው ከሚገኝ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም መነሻ ካፒታል 25 ሺ ብር በመበደር ሥራውን አስፋፍተው ቀጠሉ። ብድሩ ለሁለት ዓመት የነበረ ቢሆንም ሥራው ውጤታማ በመሆኑ ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መመለስ ችለዋል። በተጨማሪ ጠቀም ያለ ብድር ለሁለተኛ እና ለሶስተኛ ጊዜ በመበደር የተለያዩ ማሽኖችን በመግዛት ሥራውን አስፋፍተዋል ።

በአሁኑ ወቅትም ከተለመደው የስፌት ሲንጀር ማሽኖች በተጨማሪ ዘመኑ የደረሰበትን ኢምብሮደር ማሽን ከውጭ በማስገባት የተለያዩ አልባሳትን እያመረቱ ይገኛሉ። የዘመኑ ስልጣኔ ጥግ የተባለው ይህ ማሽን



አቶ ዳዊት ሞገስ በአሁኑ ወቅት ከተለመደው የስፌት ሲንጀር ማሽኖች በተጨማሪ ዘመኑ የደረሰበትን ኢምብሮደር ማሽን ከውጭ በማስገባት የተለያዩ አልባሳትን እያመረቱ ነው፤



በሶፍትዌር የተለያዩ ዲዛይኖች እና የተለያዩ ክሮች የሚሰጡት ሲሆን ማሽኑ ክሮቹን ተጠቅሞ የሚፈለገውን ዲዛይን በከለርም ሆነ በቅርጽ አትሞ የሚያወጣ ነው።

ከአንድ ሲንጀር መኪና በመነሳት 50 ዘመናዊ ሲንጀሮችን እንዲሁም የዘመኑ ቴክኖሎጂ የደረሰበትን ኢምብሮደር ማሽን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የቻሉት አቶ ዳዊት፤ የሚጠቀሙበት ዘመናዊ ማሽን የሰው ፣ የአበባ አልያም የእንስሳት እንዲሁም የሌላ የተፈለገውን ማንኛውም መልክ ማሽኑ በተሰጠው ጨርቅ ላይ ክሮቹን ተጠቅሞ ማተም የሚያስችለው የራሱ የሆነ ሶፍትዌር ያለውና በፍላሽ የሚሰጠው ሲሆን ማሽኑ እራሱ ፍላሹን አንብቦ በሚጎርሰው 12 አይነት ክር እና 12 መርፌ ተጠቅሞ ወደ ክር ይቀይረዋል።

በዚሁ ዘመናዊ ማሽን የሚገኘው ውጤት የተፈለገውን አይነት ሁሉ ሲሆን ለአብነትም አደይ አበባ፣ መስቀል፣ ኃይማኖታዊ ጥቅሶችና የተለያዩ ባህላዊ አልባሳትን ጥልፍ አስመስሎ ያመርታል። ከዚህ በተጨማሪም ጋርመንት ፕሪንቲንግ ማሽን ገዝተው ለመጠቀም በዝግጅት ላይ ሲሆኑ ይህም ቲሸርቶችን በብዛት ማምረት የሚያስችል መሆኑን ይናገራሉ። ኢምብሮደር የተባለው ማሽን በቀን ከ200 እስከ 300 የሚጠልፍ ሲሆን ጋርመንት ፕሪንቲንግ ማሽን ደግሞ በከፍተኛ መጠን በቀን 3000 ቲሸርቶችን ማምረት የሚያስችል ነው ። ይህን ማሽን ወደ ሥራ ለማስገባት ታድያ በአሁኑ ወቅት የግዢ ሂደቱን አጠናቀው ማሽኑን ለመረከብ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ።

ድርጅቱ በዚሁ ማሽን ማምረት ሲጀምር ታድያ በአሁኑ ወቅት ከፈጠረው 52 የሥራ ዕድል በተጨማሪ ከ20 እስከ 30 ለሚደርሱ የአካባቢው ወጣቶች ተጨማሪ የሥራ ዕድል በመፍጠር የላቀ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ይሆናል። የሚያመርታቸውን ምርቶችም ለጅምላ አከፋፋዮች በማስረከብ በችርቻሮ ከመሸጥ ሥራ የሚወጣ እንደሆነ አቶ ዳዊት አንስተው ይህም የሚከፈተውን የሥራ ዕድል ሰፊ የሚያደርገው መሆኑን አንስተዋል።

በአሁኑ ወቅት በአካባቢው ብሎም በአገሪቱ አሉ የተባሉና እጅግ ዘመናዊ የሆኑ ማሽኖችን ከውጭ አገር በማስመጣት የተለያዩ አልባሳቶችን በጥራት እና በብዛት እያመረተ የሚገኘው ኖጺቾ የልብስ ስፌት ኢንተርፕራይዝ በዲላ ከተማ ቀዳሚ ኢንተርፕራይዞች መካከል አንዱ ነው። ዘመኑን የዋጀ ማምረቻ ማሽን ያለው ይህ ድርጅት የተለያዩ አልባሳትን በአይነትና ቅርጽ እያመረተ ለገበያ የሚያቀርብ ሲሆን፤ የገበያ መዳረሻውም ከዲላ እስከ አዲስ አበባ ከተማ መሆኑን አቶ ዳዊት ይገልጻሉ። በዲላ ከተማ ብቻ ሶስት የመሸጫ ሱቆች እንዳሏቸውና በከተማዋና በከተማዋ ዙሪያ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ መሆን እንደቻሉ ተናግረዋል። ከዚህ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ ባላቸው አንድ የመሸጫ ሱቅም በተለይም ባህላዊ አልባሳትን ለገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ።

ለገበያ ከሚያቀርቧቸው ባህላዊ አልባሳት መካከል የጌዲኦ ባህላዊ አልባሳት የወንዶችና የሴቶች እንዲሁም የህጻናት አልባሳት በስፋት ይገኙበታል። በተለይም ሚኒስትሮችን ጨምሮ የተለያዩ ባለስልጣናት የሚለብሱት የጌዲኦ አልባሳትን ያመርታሉ። ከባህል አልባሳቱ በተጨማሪም በተለምዶ አምባሳደር የሚባለውን ሙሉ ልብስም በዘመናዊ ጨርቅ ያመርታሉ። ከዚህ ባለፈም የመዘምራን አልባሳትን በማምረትም በስፋት ይታወቃል።

በአንድ ሲንጀር መኪና እና በ25 ሺ ብር መነሻ ካፒታል የተጀመረው የጨርቃ ጨርቅ ኢንተርፕራይዝ በአሁኑ ወቅት የመሥሪያ ማሽኖቹን ሳይጨምር 10 ሚሊዮን ብር መድረስ ችሏል። ድርጅቱን አሁን ስኬታማ መሆን ያስቻለው ከባለቤታቸው በተጨማሪ ከልጆቻቸው ጋር መሥራት በመቻላቸው እንደሆነ የገለጹት አቶ ዳዊት፤ ባለቤታቸው በቤት ውስጥ የስፌት ሥራውን ከጀመሩበት ወቅት ጀምረው ልጆቻቸው እናታቸውን በማገዝ ሙያውን መልመድ እንደቻሉ አጫውተውናል።

ወላጅ እናታቸውን ለማገዝ በሚል በመኖሪያ ቤታቸው ደጃፍ ላይ የልብስ ስፌት ሙያን እየተመለከቱ ያደጉት አምስት ልጆቻቸውም ሥራውን ለመልመድ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖላቸዋል። ከወላጅ እናታቸው ከደጃቸው የቀሰሙትን ሙያም በዘመናዊ ትምህርት በማስደገፍ ዘርፉን በተሻለ ጥራት ተቀላቅለው ውጤታማ እንዲሆን የላቀ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ከአምስት ልጆቻቸው ጋር ተደራጅተው የሚሰሩት እነዚህ ጥንዶች በቀጣይም ዘርፉን ከዚህ በበለጠ የማስፋፋትና ሰፊ የሥራ ዕድል የመፍጠር ዕቅድ አላቸው። በፋሽን ዲዛይን ሰልጥነው ድርጅቱን በሙያ እያገዙ ከሚገኙት አምስት ልጆች መካከል አንደኛዋ በፋሽን ዲዛይን ውድድር ከክልሉ የዋንጫ ተሸላሚ መሆንዋን አቶ ዳዊት አጫውተውናል።

‹‹ቤተሰብ በጋራ መሥራት ሲችል በእጅጉ ተጠቃሚና ውጤታማ መሆን ይችላል ።ለዚህም እኛ ምሳሌዎች ነን›› የሚሉት አቶ ዳዊት፤ ከቤተሰብ ጋር ተናቦ መሥራት ወጪን ለመቆጠብም ሆነ ተቀማጭ በማድረግ ውጤታማ ለመሆን የጎላ ድርሻ አለው። በተለይም ኢትዮጵያውያን በጋራ የመመገብ ልምድ ያለን በመሆኑ በጋራ የመሥራት ልምድንም ማጠናከር ከተቻለ በቀላሉ ማደግ መለወጥ ይቻላል የሚል እምነት አላቸው ። ልጆቻቸውም በጋራ ተናበው በመስራታቸው ለድርጅቱ ትልቅ አቅም መፍጠር የቻሉ እንደሆነና እነሱ ቢደክሙ እንኳን ልጆቹ ሥራውን ማስቀጠል የሚያስችል ከፍተኛ ፍላጎት ከአቅም ጋር ያላቸው መሆኑን አጫውተውናል።

ከፋሽን ዲዛይን ባለሙያ ልጆቻቸው ጋር የተደ ራጁት አቶ ዳዊት በኖጺቾ የልብስ ስፌት ኢንተርፕራይዝ የሚመረቱትን ሶስት አይነት አልባሳት በሶስት የመሸጫ ቦታዎቻቸው ላይ ለይተው የሚሸጡ እንደሆነ ተናግረ ዋል። ይህም አልባሳቱ የተለያዩ በመሆናቸው ደንበኞች ምርቱ በቀጥታ ከሚገኝበት ሱቅ በቀላሉ የፈለጉትን ምርት ማግኘት እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።

በዘመናዊ ጨርቅ የሚሰራውን ሙሉ ልብስ፣ ለእምነት ተቋማት የሚያገለግሉ የተለያዩ አልባሳትና ዘመናዊ በሆነው በኢምሮደር የሚመረተውን የህትመትና የጥልፍ ምርቶች እያንዳንዳቸው በተለያዩ ሱቆች ለገበያ የሚቀርቡ ሲሆን አንደኛ ልጃቸው ከማምረቱ ሥራ በተጨማሪ በሽያጩም ላይ ተሰማርታ ትገኛለች።

የቤተሰብ ካምፓኒ በማቋቋም የጨርቃ ጨርቅ ዘርፉን በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ የመሸጋገር ዕቅድ ይዘው የሚተጉት ቤተሰቦች በቀጣይ ከአገር ውስጥ ባለፈ ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ አቅደው እየሰሩ ይገኛሉ። የሚያመርቷቸውን የተለያዩ የአገር ባህል እና ዘመናዊ አልባሳት በጥራትና በስፋት በማምረት ወደ ውጭ ገበያ የመላክ ዕቅዳቸውን ለማሳካት በቅድሚያ ተወዳዳሪ ሆነው በአቅራቢያቸው በሚገኘው ሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ መግባት ያለባቸው መሆኑንና ለአገር ውስጥ በስፋትና በጥራት በማቅረብ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን አልባሳት ለማስቀረት እየሰሩ ያሉበት ሁኔታ መኖሩን አቶ ዳዊት ያስረዳሉ ።

በአሁኑ ወቅትም እያመረቱበት ካለው 400 ካሬ ሜትር የማምረቻ ሼድ በተጨማሪ አዲስ ለሚያስገነቡት ማሽን ተጨማሪ 400 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ሼድ ከመንግሥት በኪራይ ተረክበው የማሽን ተከላ ለማካሄድ በዝግጅት ላይ ናቸው።ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻር ድርጅታቸው በተለያዩ መንገድ ለአካባቢው ማህበረሰብ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

አጠቃላይ የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ የተመለከተው የዲላ ከተማ አስተዳደርም ድርጅቱ ቀድሞ ይሰራበት በነበረ ቦታ ላይ 150 ካሬ ሜትር ቦታ ጨምሮ ደረጃውን የጠበቀ ባለ አራት ፎቅ ህንጻ እንዲገነባ ፈቃድ ሰጥቷል። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የግንባታ ሥራውን በመጀመር ሂደት ላይ ይገኛሉ። ህንጻው የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ሲሆን በዋናነት ምርቶቻቸውን ለማሰራጨት የሚጠቀሙበት እንደሆነና በቀጣይ በአቅራቢያቸው ወዳሉ ከተሞች ለሚያደርጉት ማስፋፊያ የካፒታል ምንጭ እንደሚሆናቸው ነው የጠቀሱት ። እኛም ዕቅዳቸው ተሳክቶ ፍሬ ያፈራ ዘንድ በመመኘት ጥንቅራችንን አበቃን!

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ለመስኖ ልማት ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ተስፋ የተጣለበት መመሪያና ስታንዳርድ

**መላኩ ኤሮሴ**

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው በግብርና ሥራ የተሰማራ ቢሆንም በአገሪቱ ውስጥ የሚመረተው ምርት የአገር ውስጥ የምግብ ፍጆታ ሊሸፍን ባለመቻሉ በአገር ውስጥ ሊመረቱ የሚችሉ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ከውጭ አገራት ታስገባለች። ለመስኖ ምቹ የሆነ መሬት እና የውሃ ሀብት ባለቤት ብትሆንም የአገሪቱ አርሶ አደሮች በክረምት በሚዘንበው ዝናብ ላይ በአመዛኙ ጥገኛ በመሆን የአገሪቱ አርሶ አደሮች የድካማቸውን ያህል ፍሬ ሳያገኙ ዘመናት ተቆጥረዋል።

በአገሪቱ ውስጥ የሚስተዋለውን የግብርና ምርት እጥረት ለመቋቋም የግብርና ምርቶችን በከፍተኛ ውጭ ምንዛሬ እየገዛች ወደ አገር ውስጥ እያስገባለች ትገኛለች። ይህንን ሁኔታ ለመቀየር መንግሥት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለመስኖ ልማት ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው። ከለውጥ መንግሥት ወዲህ በአገሪቱ ያለውን ለመስኖ ምቹ መሬትና ውሃ ወደ መስኖ ለመመለስ ጥረት እየተደረገ ነው ። በተለይም በበጋ መስኖ ልማት ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ይገኛል።

የለውጡ አመራር ወደ ስልጣን ከመምጣቱ አስቀድሞም የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት መጠነኛ ጥረት ሲደረግ የነበረ ቢሆንም የመስኖ ልማት በተለያዩ ችግሮች የተበተበ ነበር። የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በተባለላቸው ጊዜ እና በጀት የመጠናቀቅ ችግር ይስተዋልባቸው ነበር። አገር በቀል ብሔራዊ የመስኖ ፕሮጀክቶች ዲዛይን ጥናትና ግንባታ ስታንዳርድና የአሠራር መመሪያ አለመኖር ፕሮጀክቶች በሚፈለገው ፍጥነት እንዳይጠናቀቅ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል። በዚህም ምክንያት አገሪቱ ከመስኖ ልማት ማግኘት ያለባትን ምርት ሳታገኝ ቆይታለች።

በመስኖ ዲዛይን፣ ጥናትና ግንባታ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለመድፈን የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የመስኖ ዲዛይን፣ ጥናትና ግንባታ ስታንዳርድና ሥራ መመሪያ ለማዘጋጀት እንቅስቃሴ ጀምሯል። የሥራ መመሪያውን እና ስታንዳርዱን ለማዘጋጀት በቅርቡ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክርም አካሂዷል።

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ብዙነህ ቶልቻ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ከአሁን ቀደም አገር በቀል የመስኖ ልማት ዲዛይን፣ ግንባታና ቴክኖሎጂ ስታንዳርድና የአሠራር መመሪያ አልነበራትም። መስኖ ዲዛይን፣ ግንባታና ቴክኖሎጂ ስታንዳርድና መመሪያ ያልተዘጋጀበት ምክንያት ደግሞ የመስኖ ዘርፍን በባለቤትነት የሚመራ አካል ባለመኖሩ ነው። በዚህም ምክንያት መስኩ ተዘንግቶ ነው የኖረው። መስኖ አንዴ በውሃና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ስር ሌላ ጊዜ ደግሞ ከየትኛውም ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ስር ሳይካተት የቆየ እጅግ ወሳኝ ነገር ግን የተዘነጋ ዘርፍ ነበር።

ሆኖም አልፎ አልፎ ግን አንዳንድ ተቋማት የመስኖ ዲዛይን፣ ግንባታና ቴክኖሎጂ ስታንዳርዶችን ሊያዘጋጁ ጥረት ሲያደርጉ ነበር። አንዳንድ ሙከራዎች ቢኖሩም የሚፈለገውን ያህል ሊሄድ አልቻለም። ለምሳሌ የተፋሰስ ልማት ባለስልጣን የመስኖ ልማት ሥራ በቀጥታ ባይመለከተውም እንኳን የመስኖ ግንባታ፣ ቴክኖሎጂ እና ዲዛይን ስታንዳርድ እና የሥራ መመሪያ አዘጋጅቶ ነበር። ሆኖም የሚጎድሉት ነገሮች ስላሉ ሙሉ አይደለም። በመሆኑም እንደሚፈለገው ሊሰራበት አልተቻለም። በመሆኑም የተዘጋጀውን መመሪያን ስታንዳርድ በባለቤትነት ወስዶ በሥራ ላይ የሚያውል አካል አልነበረም።

> **የመስኖ ግንባታና ዲዛይን በሚሠራበት ወቅት ከዚህ ውጪ መውጣት አይቻልም፣ በዚህ መሠረት መሠራት አለበት፣ በዚህ መሠረት መሠራት የለበትም የሚል አገር በቀል ስታንዳርዶች የሉም ። የሚሠሩ የግድብ ሥራዎችም አገር በቀል ስታንዳርድ እና መመሪያ ላይ መሠረት ያደረጉ አልነበሩም**

እስከ ዛሬ የመስኖ ሥራን የራሴ ነው ብሎ የሚሠራ ተቋም አለመኖር የመስኖ ግንባታ፣ ዲዛይንና እና ቴክኖሎጂ የአሠራር መመሪያና ስታንዳርድ እንዳይኖር ምክንያት ሆኖ መቆየቱን የጠቆሙት አቶ ብዙነህ፤ በቅርቡ የተቋቋመው የመስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር የመስኖ ሥራን እንደ አገር አቀፍ ደረጃ በባለቤትነት እንዲሠራበት በመደረጉ የስታንዳርዱና መመሪያው እንዲዘጋጅ በር ከፍቷል። የዚህ መመሪያ እና ስታንዳርድ ዝግጅት መጀመር ለዘርፉ እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ይጠበቃል።

እንደ አቶ ብዙነህ ማብራሪያ እስካሁን ድረስ አገር በቀል ስታንዳርድና የሥራ መመሪያ አልነበረም ማለት የመስኖ ግንባታ እና የጥናት ሥራዎች ያለምንም ስታንዳርድ እና ሥራ መመሪያ ይሠሩ ነበር ማለት ግን አይደለም። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሠራባቸው እስታንዳርዶችና መመሪያዎች ሥራ ላይ ሲያውሉ ነበር። መሐንዲሶች የእንግሊዝ፣ የህንድ እና የአሜሪካ ስታንዳርዶችና መመሪያዎች ሲጠቀሙ ነበር። ከዚያ ባሻገር መሐንዲሶች ከትምህርት ቤት ጀምሮ በተማሯቸው ትምህርቶች ባገኙት እውቀት የሚሠሩበት አለ። እነዚህ መመሪያዎች በአመዛኙ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ አልነበሩም።

ባለሙያዎች ዓለም አቀፍ የሌሎች አገራት መመሪያዎችን እና ስታንዳርዶችን ወደ ኢትዮጵያ አምጥተው ሥራ ላይ በሚያውሉበት ወቅት የመስኖ ሥራ ወጥነት እንዳይኖረው እንቅፋት ሆኖ ነበር። ባለሙያዎች የፈለጉትን ነው ሲጠቀሙበት የነበረው። አንዳንዶቹ የአሜሪካንን መመሪያዎችና ስታንዳርዶችን ሲጠቀሙ ሌሎቹ ደግሞ፤ የእንግሊዝ፣ ሌሎቹ ደግሞ የህንድ መመሪያዎችንና ስታንዳርዶችን ሲጠቀሙ ነበር። እነዚህ አገሮች ስታንዳርዶቹንና መመሪያዎቹን ለኢትዮጵያ ብለው ያዘጋጁት አይደለም። የራሳቸውን አገራት ነባራዊ ሁኔታዎችን ታሳቢ አድርገው ያዘጋጁት ነው።

እነዚህን መመሪያዎች እና ስታንዳርዶችን መጠቀማቸው ዲዛይን፣ ግንባታና ሌሎች ነገሮች ወጥነት እንዳይኖረው እንቅፋት ሆኖ ነበር። የሌሎች አገራትን መመሪያዎችና ስታንዳርዶችን ሥራ ላይ ማዋላቸው እንደ አገር የመስኖ ሥራ ላይ ክፍተት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኖ መቆየቱን የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

ስታንዳርድና የአሠራር መመሪያው እንደ አገር አንድ ወጥ ሆነው ሲዘጋጁ እንደ አገር ሁሉም አገር በቀል የአሠራር መመሪያ እና ስታንዳርድ ተከትለው ለመስራት እንደሚገደዱ የጠቆሙት አቶ ብዙነህ፤ በዘርፉ በሚሠሩ ሥራዎች ላይ ገባ ወጣ አይኖርም። በመላ አገሪቱ ተመሳሳይ ስታንዳርዶች እና መመሪያዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስገድድ ይሆናል።

የሥራ መመሪያ እና ስታንዳርዱ ሥራ ላይ ሲውል የመስኖ ግንባታ እና ዲዛይን እንዲቀላጠፍ የበኩሉን እንደሚያበረክት የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ ጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታው መቀላጠፍ የሚገነቡ የመስኖ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው በጀትና ጊዜ እንዲጠናቀቅ በማድረግ የጊዜ፣ የገንዘብና የጉልበት ብክነትን ለመቅረፍ ይረዳል ብለዋል።

እንደ ኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የመስኖ ግንባታና ዲዛይን በሚሠራበት ወቅት ከዚህ ውጪ መውጣት አይቻልም፣ በዚህ መሠረት መሠራት አለበት፣ በዚህ መሠረት መሠራት የለበትም የሚል አገር በቀል ስታንዳርዶች የሉም። የሚሠሩ የግድብ ሥራዎችም አገር በቀል ስታንዳርድ እና መመሪያ ላይ መሠረት ያደረጉ አልነበሩም።

በቅርቡ ምክክር የተደረገበት አገር በቀል የመስኖ ግንባታ፣ ዲዛይንና ቴክኖሎጂ ስታንዳርድ ግድቦች ስታንዳርድን ያሟሉ እንዲሆኑ፣ የመስኖ ግድቦች ሂደቱ ራሱ ምን መሆን አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ ያተኮረ ነው። የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የስታንዳርዱንና መመሪያውን አስፈላጊነት፤ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ምደባ ኢንስቲትዩት ደግሞ ስታንዳርዱን ያሟላ ነው የሚባለው የትኞቹን ደረጃዎች ያሟሉ እና ሂደት የተከተለ ሲሆን ነው የሚለውን ሀሳቦችን አቅርቧል። ከተጠቀሱት ባሻገር የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ስታንዳርድ እና መመሪያ ዝግጅት ላይ የሚሳተፉ ይሆናል።

ከኢንተርናሽናል ዋተር ማኔጅመንት ኢንስ ቲትዩት፣ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከአማካሪዎች፣ ከአገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶች አገር አቀፍ ኮሚቴ በማዘጋጀት ወደ ሥራ ለመግባት እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን አቶ ብዙነህ ጠቁመዋል። በተያዘው በጀት ዓመት ወይም በቀጣይ ዓመት የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛው ሩብ ዓመት ውስጥ ስታንዳርድና የሥራ መመሪያ ዝግጅቱን ለማጠናቀቅ እቅድ ተይዟል። በታሰበለት ጊዜ ለማጠናቀቅም ርብርብ እየተደረገ ነው።

በስታንዳርድ እና መመሪያ ዝግጅት ዙሪያ ምክክር በተካሄደበት መድረኩ ላይ የተገኙት የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሐመድ፤ አገራዊ ስታንዳርድ እና መመሪያ መዘጋጀት ከመስኖ ግንባታና ዲዛይን ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችል እንደመሆኑ የመስኖ ፕሮጀክቶች በፍጥነት እንዲጠናቀቁ ስለሚያስችል አገሪቱ በዓመት አንድ ጊዜ ከማምረት በዓመት ሦስት ጊዜ ወደ ማምረት ለመሸጋገር ለሚታደርገውን ጥረት እውን ለማድረግ ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው መናገራቸውን የሚኒስቴሩ የኮሙዩኒኬሽን ክፍል በፌስቡክ ገፁ ላይ ባሰፈረው ዘገባው አመላክቷል።

ኢትዮጵያ፤ ለመስኖ ሊውል የሚችል ከፍተኛ መጠን ያለው መሬትና ውሃ የታደለች አገር ብትሆንም እስካሁን ድረስ በአግባቡ ሳትጠቀምበት ቆይታለች። በዚህም ምክንያት ወንዞቻችን ለጎረቤት አገራት ሲሳይ ሆነው ቆይተዋል። አገሪቱ ውስጥ በመስኖ ሊለማ ከሚችል መሬት ውስጥ አንድ ሦስተኛውን ማልማት ቢቻል እንኳን አገሪቱ በምግብ ራሷን ለመቻል የሚታደርገውን ጥረት ማሳካት እንደምትችል የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ። በዝግጅት ላይ የሚገኘው የመስኖ የሥራ መመሪያ እና ስታንዳርድ አገሪቱ ወንዞቿን ለማልማት ለምታደርገው ጥረት እውን እንዲሆን ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ነው።

በምክክር መድረኩ ላይ የተገኙት በሚኒስቴሩ የመስኖ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ብርሃኑ ሌንጂሶ እንደተናገሩት፤ «ኮዶች እንደ አገር በመስኖ ዘርፍ የሚስተዋሉ የአሠራር ብልሽቶችን ለመቅረፍ ጠቀሜታቸው ጉልህ ነው ፤ እንደ መስኖ ደግሞ የውኃ ሀብታችንን በአግባቡ ለመጠቀም ኮዶችና ስታንዳርዶች መዘጋጀታቸው ቁልፍ ሥራ ነው» ብለዋል።

በመስኖም ሆነ በሌሎች ግድብ ግንባታ ወቅት የጥራት ጉዳይ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ሲሆን አገር በቀል መመሪያ እና ስታንዳርድ መዘጋጀት መጀመሩ ለጥራት መጠበቅ እገዛ ይኖረዋል። በስታንዳርድና ሥራ መመሪያ ዝግጅት ላይ ከሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት እንዱ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ሲሆን፤ የኢንስቲትዩት የስታንዳርድ ዝግጅት ዳይሬክተር ተወካይ በበኩላቸው ስታንዳርዱና መመሪያው የሚሠሩ የመስኖ ግድቦች ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ያስችላል ብለዋል «የሚሰሩ ግድቦች ጥራት እንዲኖራቸውና ውጤታማ እንዲሆኑ የአሠራር ማሻሻያ ኮዶችን ተግባራዊ ማድረግ ይገባል» ሲሉ አክለው ተናግረዋል።

የአሠራር መመሪያ እና ስታንዳርድ ዝግጅት በአጭር ጊዜ ተጠናቆ ወደ ሥራ እንዲገባ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ርብርብ ሊያደርጉ ይገባል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዕይታችን ከዛሬ መከራዎቻችን ባሻገር ያሉ ተስፋዎቻችንን እውን ማድረግ ላይ ይሁን!

በአስተውሎት እና በፈተና መጽናት በእምነት ሲደገፉ የሰው ልጆች ብርቱ መደገፊያዎች፤ ዛሬን ከድካም ጋር ተጋፍጦ ማለፊያ ምርኩዞች ናቸው፡፡ እምነት፣ በፈጣሪ መታመንንና ስለ ነገ ተስፋ አድርጎ መራመድን፤ አስተውሎትም፣ የእምነታችንን ፍሬ ለማግኘት የምንሄድበትን መንገድ እና የምንጓዝበትን ርቀት ቀድመን ተገንዝበን ለዚያ የሚሆን ሙሉ ዝግጅት ማድረግን፤ በፈተና መጽናት ደግሞ ተስፋ ያደረግንበት ቦታ በመድረስ ሂደታችን የሚያጋጥሙንን ፈተናና ችግሮችን ተቋቁሞ ማለፍን፣ ስለ መዳረሻችን እያለምን የዛሬው መከራ ያልፋል ብሎ በጽናት መገስገስን ያላብሱናል፡፡

ዛሬ ላይ ኑሮ ሕዝቡን በእጅጉ ፈትኖታል፤ የመንግሥት አገልግሎት መስጫ ተቋማትም ከአገልግሎታቸው ይልቅ እንግልታቸው ገዝፎ አሳሩን ያሳዩታል፤ እንዲያስተዳድሩት የሾማቸው ሹማምንቶቹም ሆነ ምንዳ ከፍሎ እንዲያገለግሉት በተቋማት የቀጠራቸው ባለሙያዎች ጉዳዩን ያለ እጅ መንሻ ላለመፈጸም ተማምለው ያደሙበት እስኪመስል የከፋ የመልካም አስተዳደርና የሙስና ችግር ደቅነውበታል፡፡ ይህ አልበቃ ብሎ ደግሞ ድርቅ ችግሩን ሲያከፋበት፤ የሰላም እጦት ወጥቶ የመግባት፣ ሠርቶ ንብረት የማፍራት ቀርቶ ያፈራውን ንብረት የመጠቀም ዋስትናው አደጋ ላይ የወደቀበት ወቅት ነው፡፡

የኑሮ ውድነት፣ የመልካም አስተዳደር እጦትና ሌብነት፣ ሰላምና ደህንነት፣ ወዘተ. ችግሮቻችን ተደራርበውና ገዝፈው ሲታዩን፤ ከዕለት ዕለት መሻሻልን ስንጠብቅ ጭነታቸው ሲበረታብን የነገ መዳረሻችንን ትተን ዛሬው ላይ ልናተኩር፤ ስለነጋችን መስራትን ቸል ብለን የዕለታዊ ጉዳዮቻችን ላይ ጊዜ እንድናጠፋ ሊያደርጉን ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ ወደ ሕልማችን የምናማትርበት ማስተዋላችን እንዲሸፈን፣ በጉዟችን ላይ ለሚያጋጥሙን ፈታኝ ሁኔታዎች በቀላሉ ተሸንፈን እጅ እንድንሰጥ ያደርገናል፡፡ ሆኖም እኛ በፈተናዎች የምንሸነፍ ሳንሆን ፈተናዎችን በድል በመሻገር ለነገ ተስፋችን የምንደርስ መሆናችንን አምነን መቀበል፤ እምነት፣ ማስተዋልና ጽናትን መላበስ አለብን፡፡

በሰሞኑ የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ንግግር እንደተደመጠውም፤ እኛ የራዕያችን መንገደኛ እንጂ የችግሮቻችን እስረኛ መሆን የለብንም፡፡ እኛ ችግር እየያዘ የሚያስረን ሳንሆን፤ ራዕያችን የሚያስሮጠን መሆን አለብን፡፡ በዚህ መልኩ የችግሮቻችን እስረኛ ሳንሆን ወደ ራዕያችንና ሕልማችን ለመድረስ ደግሞ፤ ብርቱ መደገፊያ የሚሆነንን እምነት፤ ጽናትን የሚያጎናጽፍ ማስተዋልን፤ በዛሬ መፈተን ውስጥ የሚያጋጥሙንን ብርቱ ውጣ ውረዶች እንደ አቅም መፍጠሪያና መስፈንጠሪያ ዕድል ቆጥረን ልንጠቀምባቸው ይገባል፡፡

ምክንያቱም ማስተዋላችን፣ ከከፉ ነገር ሁሉ ይጋርደናል፤ ይጠብቀናል፡፡ ጉዟችን በማስተዋል፣ ምግባራችን በጥበብ የተመራ ሲሆን፤ ስለ ዛሬው ፈታኝ ሁኔታ ሳይሆን ስለነጋችን ብሩህ ቀን እናልማለን፤ ስለ ዛሬው ቅስም ሰባሪ መከራና ችግር ሳይሆን ስለነጋችን የተሻለ ደስታና ሃሴት እንጓጓለን፤ ዛሬ ላይ አላራምድ ካሉን የኑሮ ውድነትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች አሻግረን ነገ ስለምንጎናጸፈው ሁሉን አቀፍ ብልጽግና እንናፍቃለን፡፡ የእነዚህ የማለም፣ የመጓጓትና የመናፈቅ ድምር ውጤቶች ደግሞ ለመንገዳችን ስንቅ፣ ለእርምጃችን አስተውሎትን ይቸሩናል። ምክንያቱም ሕልምና መሻቶቻችን እንዲመክኑ፤ በዛሬው ፈተናችን፣ በትናንቱ ትዝታችን ታስረን መቅረትን አንሻምና ነው፡፡

ይሄን ማድረግ ሳንችል ከቀረን ግን እንደ ሎጥ ሚስት ትተነው የምንወጣው፣ ጥለነው የምንሄደው ነገር እያሳሳን፣ ሃጢያትና ጥፋት መሆኑን እያወቅንም ቢሆን ከሁነቱ መላቀቅ የሚያባባን ሆኖ የፊታችንን ትተን የኋላችንን የምንመለከት ሲሆን፤ ለፊቱም ሳንበቃ፣ የኋላውንም ደግመን ላናገኘው ከመሃል ላይ የጨው አምድ ሆነን መቅረታችን፤ ለራሳችንም ለአገራችንም ለሕዝባችንም የሚጠቅም አንዳች ጠብ የሚል ነገር ሳናበረክት ባክነን እንቀራለን፡፡

በመሆኑም እምነታችንን ይዘን ጉዞ እንደጀመርን፣ ጉዟችንንም በማስተዋል ለመምራት እንደቻልን ሁሉ ለፍጻሜው የምናደርገው ግስጋሴም ፈተናዎችን ማለፍ፣ ችግሮችን መቋቋም የሚያስችል ጽናትን መላበስ የግድ ይለናል፡፡ ምንም እንኳን መከራን መጋፈጥ መራር፣ ችግርን መሻገር ከባድ መስሎ ቢታየንም፤ በብዙ ፈተናዎች ታጅበን፣ በበረከቱ ችግሮች ተከብበን የምናደርገው ጉዞ ፍጻሜው ያማረ፣ ፍሬውም የጣፈጠ መሆኑ እሙን ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ መከራን በመከራነቱ ብቻ ሳይሆን መካሪነቱንም ሳንዘነጋ፤ በሚያጋጥሙን መከራዎች፣ በሚፈትኑን ችግሮች ውስጥ ሁሉ መከራና ችግሮቹን ለነገ የተሻለ ነገር መትለሚያ



ዕድል፣ የነገን ሌላ ችግርና ፈተና መሻገሪያ ድልድይ አድርገን ልንጠቀምባቸው ይገባል፡፡ ይህ ሲሆን ጉዟችን ባመንነው ፈጣሪ የተመራ፣ ሂደታችን በማስተዋል የተቃኘ፣ ችግሮቻችንም በጽናት የሚታለፉ ይሆናሉ፡፡ እኛም ነገን ከማለም ባሻገር፤ የነገ ሕልማችን መዳረሻ መንገዳችንን አውቀን የምንጓዝ፤ ፈተናዎችም አደናቅፈው የማይጥሉንና ከጉዟችን የማይገቱን እንሆናለን፡፡ ምንም እንኳን ዛሬ ላይ በብዙ ችግርና መከራዎች፣ በከፉ ዋይታና ሰቆቃዎች ውስጥ ብንሆንም፤ እነዚህ ሁሉ አላፊ እንጂ አብረውን ኗሪ አለመሆናቸውን በመገንዘብ ዕይታችን ከዛሬ ችግሮቻችን ባሻገር ባሉ የነገ ተስፋዎቻችንን እውን ማድረግ ላይ ሊሆን ይገባል፡፡


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# የሕግ ገመድ ሲላላ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ብዙዎች ርቆ የተሰቀለን ተስፋ፣ ተደብቆ በተቀመጠ ዳቦ ይመስሉታል። በእነሱ እምነት የተደበቀውም ሆነ፣ የተሰቀለው ጉዳይ በጊዜው ከጥቅም ካልዋለ ፋይዳ ቢስ ይሆናል። እውነታውን እንመርምር፣ እንየው ካልን ደግሞ የእነሱ እሳቤ ከአንድ ጥግ ሊያደርስን ግድ ይላል። አዎ! የተሰቀለውም ይሁን፣ የተደበቀው ነገር ጊዜውን ጠብቆ ከታሰበው ካልዋለ ውጤቱ እነሱ እንዳሉት ፋይዳ ቢስ ይሆናል።

መነሻችንን ሳንዘነጋው ርዕሳችንን ርቆ ከተሰቀለው ተስፋ ላይ እናድርግ። ወደሰሞንኛው ኢኮኖሚያዊ ጉዳያችን። ማጋነን አይሁንብኝና፤ ዛሬ አብዛኛው ብቻውን እያወራ የሚሄድበት እውነት የኑሮ ጫናውና የመጪው ጊዜ ስጋቱ ነው ለማለት ያስደፍራል። እንዲህ ኑሮ ሽቅብ ወጥቶ ሕይወት ቁልቁል ሊደፋ በቀረበበት አፍታ ይህን ማሰቡ ላያስገርም፣ ላያስደንቅ ይችላል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በየጊዜው ጣራ የሚነካው የሸቀጦች ዋጋ «ባለህበት ቁም» የሚለው እንኳን ጠፍቶ የዋጋው መጠን ከተሰቀለበት መውረድ ቀርቶ ባለበት መርጋት ሲያቅተው ማየታችን ቀጥሏል። ይሁን እንጂ ሁሌም እንደሚሆነው ልማድ ዛሬም ሽቅብ የተሰቀለውን ወቅታዊ የዋጋ ንረት ከነበረበት ለማውረድ የሚተጋ ወሳኝ አካል አልተገኘም። ዛሬም አዲስ ችግር፣ አሁንም የኑሮ ውድነት፣ ሁሌም ሀሳብና ብሶት ልማዳችን ሆኗል።

እውነት፣ እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ኅብረተሰቡ በየጊዜው ለሚቀልዱበት ሕገወጦች ብርቱ ክንድ መፍጠር አልተቻለውም። ዛሬም እንደትናንቱ የሚጠየቀውን እየከፈለ፣ የተሰጠውን እየተቀበለ በኑሮ ጫና መንገዳገዱን ቀጥሏል። ለመኖር መብላትን፣ አቅምን የመጠነ ገቢና ወጪን ይጠይቃል። ሆኖም ኑሮ እጅግ ፈታኝ በሆነበት ጫንቃ ሰፊው ኅብረተሰብ ከገቢው ያልተመጠነ፣ ከአቅሙ ያልተናበበ ሕይወትን ሊመራ ተገዷል። የዳቦ ሲሉት የዘይት፣ የእህል ዋጋ ሲባል የቤት ኪራይ፣ የትምህርትቤት፣ የትራንስፖርት፣ የየዕለት ሸቀጦችና ሌሎችም ፍጆታዎች ሁሌም ሊያልፋቸውና እንደዋዛ ሊተዋቸው የማይቻለው ግዴታዎች ናቸው።

ማንኛውም ሰው ለኑሮው የሚያሻውን ፍላጎት አቅሙ በፈቀደው መጠን የማሟላቱ እውነት የተለመደና የነበረ ሂደት ነው። በሕይወት ጉዞ ማንም ሰብአዊ ፍጡር ለራሱና ለቤተሰቡ የሚበጀውን ማድረግና ማሟላቱ አዲስ ሆኖ አያውቅም። እንዲህ ሲሆን ግን በአቅሙ የሚሸከመውን፣ በፍላጎቱም የሚችለውን እየለካ መሆን ይኖርበታል። አሁን ላይ እየሆነ ያለው ግን ከዚህ በተለየ ነው።

ዛሬ ተጠቃሚው የምኞቱን ቀርቶ የፍላጎቱን እያገኘ አይደለም። ለዕለት ጉርሱ «ሞላሁ፣አሟላሁ» ሲል የቤት ኪራዩ ሸክም ይሆነዋል። እሱን ተወጣሁት ባለ ጊዜም በየአፍታው ሽቅብ የሚወጣው የዕለት ፍጆታ ወጪው ይፈትነዋል። ቀዳዳውን ሞልቶ ዛሬን ሲያመስግን ደግሞ የነገው ሕይወት በስጋት ተሞልቶ ይቆየዋል።

ቀደም ሲል በነበሩ ተሞክሮዎች የገበያው ሁኔታ ምክንያትና አጋጣሚዎችን የሚከተል ነበር። የዛኔ ወቅቱን ያልጠበቀ የምርት አቅርቦት ሲኖር፣ ዋጋ መጨመሩ ብርቅ አልነበረም። አውደ ዓመት ሲቃረብና ነዳጅ ጨመረ ሲባልም የተወሰነ ልዩነት መፈጠሩ የተለመደ ነው። ከዓመታት አንዴ ጠብ የምትለው የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ ጭማሪም ሰበብ ሆኖ ለገበያው የዋጋ ልዩነት እንደምክንያት ይጠቀስ ነበር። እንዲህ ዓይነቶቹን አጋጣሚዎች እንደነጋዴው ሁሉ ሸማቹም ሲለማመዳቸው ቆይቷል። እስከዛሬም በአቅሙ እየሸመተ፣ በፍላጎቱ እየመጠነ፣ የኑሮውን መልክ ሲያስተካከል ቆይቷል። የዘንድሮው እውነታ ግን ከመቼውም ጊዜ የተለየ ነው። ጊዜና ምክንያትን እያሳበበ እንደግዴታ ጥቂት እያሰለሰ የሚጨምረው ዋጋ ለጆሮ እስኪከብድ መጋነኑን ቀጥሏል። የነፃ ገበያን አጋጣሚ ተንተርሰው እንዳሻቸው ዋጋን የሚቆልሉ ነጋዴዎች ዛሬም «ይብቃችሁ» ባይ አላገኙም። የተጠየቀውን ከፍሎ በሚገዛቸው ሕዝብ ላይ ያሻቸውን እያሸከሙ ያሰቃዩታል።

ከሰሞኑ ለሁሉም አነጋጋሪ የሆነው የምግብ ዘይት ዋጋ መናር ብቻ አልሆነም። የአውደዓመትን መዳረስ ተከትሎ «መጣሁ» የሚለው የቅቤ፣ የዶሮና ስጋ ጉዳይም በእጅጉ አሳሳቢ ሆኗል። በቅርቡ ከሰነበተው ዋጋ በእጥፍ የጨመረው የሽንኩርት ገበያ ምክንያትና ሰበብ አልተበጀለትም። ከነበረው ቆይታ ተስፈንጥሮ ድንገት ዋጋው ሲያሻቅብም እንደተለመደው ለምንና እንዴት ባይ አልተገኘም። አሁንም አትራፊዎች ይቸበችባሉ። ዛሬም ተጠቃሚው ይበዘበዛል። ትናንት በአስርብር የሚገዛው አንድ እስር ጎመን፣ ዛሬ መጠኑ ቀንሶ፣ ዋጋው በእጥፍ ጨምሯል። ዱቄት፣ ስኳር፣ ፍራፍሬ፣ የሕፃናት ምግቦችና ሌሎችም በነበሩበት ዋጋ ውለው አላደሩም። በአቅምና በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ኑሮ የተረሳ ያህል እንደታሪክ መቆጠር ይዟል፤ «ነበር» በሚል ትውስታ።

ትናንት በኪሎ እየመዘነ፣ በሊትር እየለካ ወር የሚያደርስ ሁሉ ዛሬ ወደ ችርቻሮ፣ ባስ ሲልም ወደ እፍኝ ቋጠሮ ግዢ ሊገባ እየተገደደ ነው። አሁን ልጆች ይዘው ቤተሰብ ለሚመሩ፣ ነገን ለሚያስቡ በርካቶች ሕይወት፣ ፈታኝና አዳጋች ሆናባቸዋለች። በየቀኑ የዋጋ ማሻቀቡ ልማድና ግዴታ በሆነበት በአሁኑ ጊዜ የሕገወጦች ህልምና ዕቅድ መለምለም ይጀምራል። በየሰፈሩ ተወሽቀው ከሕግ ዓይኖች የሚደበቁ አንዳንዶች በርካሽ ዋጋ የሚገዙትን ሸቀጥ ደብቀው ማቆየት ልማዳቸው ነው። እንዲህ ዓይነቶቹ ራስ ወዳድ ነጋዴዎች የኑሮ ውድነት በደራበት፣ ችግሩ መነጋገሪያ በሆነበት ሰሞን ከዋጋ ጭማሪ ጋር ብቅ ማለት ልማዳቸው ነው። ያም ሆኖ ለነዚህ ስግብግቦች መላና መፍትሄው ርቋል። ይህን ማሰቡ ነውር ይመስል ድርጊታቸው ሕጋዊ የሆነ ያህል አመታትን ቆጥሯል።

ይህ ዓይነቱ ልማድ ከኅብረተሰቡና ከሚመለከታቸው አካላት ዓይን የተሰወረ አይደለም። ይሁን እንጂ ሁሌም በሕገወጦቹ ላይ ትርጉም ያለው ርምጃ ሲወሰድ አይስተዋልም። ዛሬም እንደዋዛ የሚሰቅሉትን የዋጋ ጭማሪ በነበረበት ጸንቶ እንዲቀጥል የእጅ አዙር ስምምነቱ ይጸድቅላቸዋል። በየጊዜው የሚጫንበትን የኑሮ ውድነት የሚሸከመው ነዋሪ ስለነገው የሚሆነውን በስጋት እያሰበ ኑሮውን ቀጥሏል። በየቀኑ ሽቅብ የሚወረወረውን የዋጋ ጭማሪ በአግርሞት ከማስተዋል ባለፈም መፍትሄ የማፍለቅ አቅሙን ተገፏል። በተለይ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ በርካቶች ስለወደፊት የሚሆነውን አያውቁም። ዛሬን ጎርሰው፣ ነጋቸውን በተስፋ ያልማሉ። ለእነሱ ሕይወት ማለት በፈተና የታጠረ፣ በኑሮ ውድነት የታበሰ ግዴታ ሆኗል።

አሁን ላይ መንግሥት የቤት ተከራይና አከራዮችን አስመልክቶ ከወራት በፊት የተገበረውን አሠራር ዳግም ተመልሶበታል። ለሦስት ወራት ያህል አከራዩ በተከራዩ ላይ ዋጋ እንዳይጨምር፣ «ቤቴን ለቃችሁ ውጡ» እንዳይል ጭምር ገደብ አስቀምጧል። ይሄም የመንግሥት ፍላጎትና ሀሳብ የኑሮውን ውድነት ለማቃለልና ገደብ የለሹን የቤት ኪራይ ጭማሪ ፈር ለማሳያዝ በመሆኑ እንዲህ ማድረጉ አይከፋም። መንግሥት ለብዙኃን ጥቅም አስቦ መተሳሰብን ማስተማሩ እሰዬው የሚያስብል ነው። ይሁን እንጂ ከዚህ አሠራር ጀርባ ሊፈጠር የሚችል ተጽዕኖን ከግምት ማስገባቱ ደግሞ አስፈላጊ ይሆናል።

ገደቡ በተጣለባቸው ወራት በነበሩ ተሞክሮዎች እንደታየው ተከራዮች ለጊዜውም ቢሆን ከአከራዮቻቸው የዋጋ ጭማሪ ተጽዕኖ መላቀቅ ችለዋል። በየምክንያቱ ኪራይ እንጨምር ለሚሉትም ቢሆን የጊዜ ልጓም ተበጅቷል። እውነታው ግን እንዲህ መሆኑ ላይ ብቻ አይደለም። የጊዜ ገደቡ በተነሳባቸው ጥቂት ጊዜያት ነባሩ የቤት ኪራይ በእጥፍ ጨምሮ ኢኮኖሚን አናግቷል። ይህ ያልተለመደ አጋጣሚም የበርካቶችን አቅም ፈትኖ ለችግር አጋልጧል። ሁኔታውን እንደግዴታ ተቀብለው የቆዩ አንዳንድ የቤት ባለቤቶች እንደዕቅዳቸው ያልተጠቀሙባቸውን ጊዜያት በሚያካክስ ስሌት ጥቅማቸውን ሲያስመልሱ ተስተውሏል።

ይህ ሁሉ ሲሆን የኑሮ ጫናው የሚከብደው በብሶተኛው ነዋሪ ላይ መሆኑ ግልጽ ነው። ዛሬ ላይ ቆም ስለነገው አዳር የሚጨነቀው ተጠቃሚ በየቀኑ በሚያጋጥመው የኑሮ ውድነት ሕይወትን መግፋት፣ ኑሮን መቋቋም ይሳነዋል። በቤት ኪራይ ፍለጋ፣ በዕለት ፍጆታዎች የዋጋ ንረት መከራን እንዲገፋ ይገደዳል። ይህ ሁሉ ሲሆን ታዛቢና ሀይ ባይ ከጠፋ ደግሞ መተዛዘን ይሉት ልማድ፣ ነገን ማሰብ ይባል ዕቅድ ትርጉም የለሽ ይሆናል። ነገን በጋራ እንገነባታለን፣ ሕይወትን በእኩል እንጋራባታለን የምንላት አገራችን መመኪያችን መሆኗ ቀርቶ ስደትና ራስን መጥላት ይከሰታል። ዛሬ ላይ በእጅጉ መልኩን የቀየረው የኑሮ ውድነትና ያለመተሳሰብ እውነት መዳረሻው ከብሶት ጥግ ይሆናል። ታዛቢ ዓይኖች ሲጠፉ፣ የሕግ ገመድ ሲላላ፣ ሕገወጥነት ይሰፋል። መንግሥት ለዚህ ዓይነቱ ግልጽ ችግር እጁን ሊዘረጋ፣ ዓይኖችን ሊከፍት ግድ ይላል። ሕገወጦችን ከመታዘብ ባለፈ በሕግ አግባብ መዳኘቱ ለአገር ለወገን ይበጃል። አገራችን የጋራችን፣ ችግሩም የሁላችን ነውና።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የህይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## መሐንዲሱ ጥበቃ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ኀዘን ሰው በሕይወት ጉዞው ውስጥ ከሚያጋጥሙት ክስተቶች መካከል አንዱ ነው። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባለ ባህል ውስጥ ትልቅ ክብደት የሚሰጠውና ሕይወትን የሚቀማ ጭምር ሊሆን ይችላል። በቁምም ብዙ ዋጋ የሚከፈልበት እንደሆነ በብዙ መልኩ ይታያል። ቤተሰብ ሞቶ ቶሎ መጽናናት አይወደውም እስከ መባል ድረስም የሚያደርስ ነው። ነገሩ ክብደት የሚሰጠው ደግሞ በአንድነት የሚደረጉ ነገሮች መበርከታቸውና ግንኙነቱ መጠንከሩ ነው። ነገር ግን ድንገት ይህ የከረረ ቅርርብ በቋሚነት ሲቋረጥ ያንን ለመቋቋም አስቸጋሪ ይሆናል።ኀዘንን ለማሸነፍም ብዙ ትግልን ይጠይቃል።

አዲሱን እውነታ ለመቀበል ያስፈራንና በችግሩ ውስጥ ሆነን ዓመታት ይቆጠራሉ። ያ ደግሞ በሥራችን እንድንዳከም ያደርገናል። ባልተስተካከለ የኀዘን ሰለባ ውስጥ የመቆየታችን ምስጢርም ይኸው ነው። በብዙ መንገድ አኗኗራችን ፈተና የሚገጥመውም በዚህ ምክንያት ነው። ብዙዎች መሥራትና መለወጥ ሲችሉ፤ ነገሩን መቀበል አቅቷቸው ያልተገባ ችግር ውስጥ ሲዘፈቁ የምናያቸውም ይህ ነገር ስላለ ነው። የዜናው ህመም ሕይወታቸውን ጭምር ያበላሽባቸዋል። ከዚያ መጀመሪያ ራሳቸውን ይክዳሉ፤ ቀጥለው ደግሞ አካባቢያቸውን ይጠሉታል። አለፍ ብለው አገራቸውን ጭምር እስከመጥላትና ማማረርም ይደርሳሉ። «መኖር ለምኔ?» እንዲሉ ሊያደርጋቸው ይችላል። ምክንያቱም «ኀዘኑን መርሳት አይቻልም፤ አሸናፊነቴ መቼም አይመጣም» ብለው ደምድመዋልና።

ሕይወታቸው ኪሳራ ገጥሟቸውም ቢሆን ከስህተታቸው መማርን አይፈልጉም። ሁልጊዜም መተከዝና ማማረር ብቻ ልማዳቸው ይሆናል። ከነበሩበት የባሰ ሕመም ውስጥ ቢገቡም ማዘኑን መተው አይፈልጉም። መፍትሄው እነርሱም ተከታይ መሆናቸውን አውቀውና አምነው ሟቹን መርሳት ቢሆንም ማሰብ የሚፈልጉት ግን የነበረውን ግንኙነታቸውንና ፍቅራቸውን ብቻ ነው። ሀሳቦችን ማስወገድ እነርሱን መርሳት እንደሆነ ስለሚያምኑ ይህን ማድረግ ከባድ ይሆንባቸዋል። ውስጣዊው ዓለማቸው እውነታውን መቀበል ይሳነዋል። በዚህም ያልተገባ ዋጋ ይከፍላሉ። ከእነዚህ መካከል አንዱ ኢንጅነር ብርሃኑ ጉደታ ሲሆኑ፤ አብዝተው በማዘናቸው የማይወጡት መከራ ውስጥ አስገብቷቸው ነበር። መሐንዲስ ቢሆኑም ጥበቃና የቀን ሠራተኛ አድርጓቸው ነበር፤ ጎዳና አዳሪም ሆነው ነበር።

ዛሬም ቢሆን በመቄዶንያ የአረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል ውስጥ የአጭር የጽሑፍ መልዕክት (SMS) ተቀባይ የሆኑት የአዕምሯቸው ጉዳይ ችግር የገጠመው ስለነበርና ሌላ ቦታ ለመቀጠርም ሰው የሚፈልጋቸው ጊዜ ላይ ስላልሆኑ ነው። ኀዘን በተለይም ለኢትዮጵያውያን ሕይወትን የሚፈትን ስለሆነ ብዙ የሚመክሩት ነገር አላቸው። ምን ያህል ዋጋ እንደከፈሉም በሚገባ አሳይተውናል።

ኢንጅነር ብርሃኑ የተወለዱት በአዲስ አበባ ከተማ፣ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ ነው። አስተዳደጋቸው ግን በዚያው ሰፈር አልነበረም። ያደጉት በወላጆቻቸው ቤትም አይደለም። እናትና አባታቸውን በልጅነታቸው በሞት በመነጠቃቸው የወታደር ልጅ ነበሩና በወታደር ልጆች ማሳደጊያ ውስጥ ነው ያደጉት። እቅፍ ድግፍ ተደርገው በብዙ እንክብካቤ ውስጥ የማደግ እድል ገጥሟቸዋል። ሞግዚት ኖሯቸው፣ የሚማሩበት ነገር ተመቻችቶላቸው ጎዶሏቸውን ሳያስቡ ልጅነታቸው እስኪጠናቀቅ ኖረውበታልና ደስተኛ ናቸው። ስለዚህም ይህንን ማሳደጊያ መኖሪያ ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን መፈተሻ፣ ታናናሾችን መንከባከቢያ፣ ራስን መጠበቅን እንዲሁም ማንበብና መማርን ማወቂያ ጭምር እንደነበረላቸው ያስታውሳሉ። ከሁሉም በላይ በፍቅር መኖርና ሰውን መውደድ ያስተማራቸው ቤት ስለሆነላቸው ሁሌም ይወዱታል።



ፎቶ- ኢያሱ መሰለ

ኢንጅነር ብርሃኑ ጉደታ

ማሳደጊያው ፍላጎታቸውንና ችሎታቸውን ለማወቅ እንዳገዛቸውም ያስረዳሉ። በዚህም ምን መሆን እንደሚፈልጉ አውቀዋል፤ የተለያዩ ሂሳብ ነክ ትምህርቶችን በብዙ መልኩ እንዲወዱ የሆኑትና የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በዘርፉ የሠሩትም በዚህ ምክንያት እንደነበር ነግረውናል።

ኢንጅነር ብርሃኑ ትምህርታቸውን አሃዱ ያሉት በዚያው በማሳደጊያ ተቋሙ ውስጥ ሲሆን፤ አምስተኛ ክፍል ድረስ ተከታትለውበታል። ቀጣዩን ደረጃ ደግሞ ምሥራቅ በር ትምህርት ቤት ተምረዋል። ከአስረኛ ክፍል በኋላ ደግሞ ወደ ኩባ በማቅናት እስከ 12ኛ ክፍል የተማሩ ሲሆን፤ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውንም በዚያው በኩባ በሳይበርኔቲክስ ማቲማቲክስ ማጥናት ችለዋል። ተጨማሪ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ዕድል ያገኙት ደግሞ ምሥራቅ ጀርመን ሲሆን፤ ምህንድስና ያጠኑበት ትምህርት ቤት ነው።

ከኩባም ሆነ ከጀርመን መልስ አገራቸውን በተለያዩ ተቋማት ላይ ያገለገሉት ኢንጅነሩ፤ ሥራን አሀዱ ያሉት ከኩባ በጥሩ ውጤት ተመርቀው ሲመለሱ በትምባሆ ሞኖፖል ድርጅት ነው። የሂሳብ ሠራተኛም እንደነበሩ ያስታውሳሉ። ለ10 ዓመታት ያህልም በቦታው ላይ አገልግለዋል። ከዚያ የምህንድስናውን ትምህርት ተከታትለው ከመጡ በኋላ ደግሞ ጥቁር አባይ ኮንስትራክሽን ውስጥ በመግባት ለ15 ዓመት ያህል መሥራት ችለዋል። በተመሳሳይ ግብርና ምርምር ውስጥም ለሦስት ዓመታት የመሥራት ዕድል ነበራቸው። በአጠቃላይ ለ28 ዓመታት ሠርተዋል። ነገር ግን በኀዘን ሰቆቃ ምክንያት በአንድ አጋጣሚ ነገሮች ሁሉ ተመልሰው ከማይወጡበት ጉድጓድ ውስጥ ተቀብረዋል።

ለነገሩ መነሻው ልጃቸውንና ሚስታቸውን በአንድ ቀን ማጣታቸው ነው። አስተዳደጉ በማሳደጊያ ተቋም ለነበረ ሰው ደግሞ ዳግም ያገኘውን ፍቅር ማጣት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ የነበረበት ያውቀዋል። ኢንጂነር ብርሃኑ በትዳር ሕይወታቸውን ብሩህ ለማድረግ አስበው ነበር የወደዷትን መርጠው ያገቡት። ልጅ ሳይኖራቸውም ከ10 ዓመታት በላይ አሳልፈዋል። ቤታቸው የበለጠ እንዲሞቅ ደግሞ ልጅ ይፈልጉ ነበር። አጥብቀው አምላካቸውንም ይማጸናሉ። ያሰቡትም እውን ሊሆንላቸው ሚስት አረገዘች። መውለጃ ቀኗም ደረሰና ወደ ሆስፒታል ገባች። ነገር ግን እርሷም ሆነች ልጇ በወሊድ ችግር ምክንያት ሕይወታቸው ስላለፈ ወደ ቤት አልተመለሱም።

ዳግመኛ የፍቅር ኑሮን በቤተሰብ ለማሳመር የጣሩት ኢንጅነር ብርሃኑም ባዷቸውን ቀሩ። ቤቱ እንኳን አቅፌ እስመዋለሁ ብለው የተመኙትን አዲሱን እንግዳቸውን ይቅርና ለዓመታት ያውቋት የነበረችውን ባለቤታቸውንም አላስገባላቸውም። ያ በደስታ የሚያውቁት ቤታቸው አፍ አውጥቶ ሊበላቸው ደረሰ። እያንዳንዱ ነገር እርሷን እያስታወሳቸው ሕመማቸውን ጨመረባቸው። እናም ስብራታቸው በቀላሉ ሊጠገንላቸው አልቻለም። ይህንን የብቸኝነት ሕይወት ብቸኝነትና ባላስለመዳቸው ቤት ውስጥ ማሳለፍ ሰቆቃው ቀላል አልሆንልህ አላቸው።

የእናትና የአባትን ፍቅር ሳይቀምሱት የቀሩት ሰው የሚስትን ጣዕም ከልጅ ጋር አጣምረው ለማጣጣም ቢመኙና ቢጓጉም አልቻሉም። ይህ ደግሞ ለሌላ ዳግመኛ ቅጣት አዘጋጃቸው። ይህም ሥራቸውን በአግባቡ መስራት ስላልቻሉ መስሪያ ቤት መሄድ ያቆሙበት ነው። በእርግጥ ይህም ቢሆን በቅጽበት የተፈጸመ አልነበረም። መስሪያ ቤቱ በተለይም ትንባሆ ሞኖፖል በብዙ መልኩ አግዟቸዋል። በፈለጋቸው ጊዜ እየገቡ ሲሠሩ ደሞዛቸውን ጭምር ሳይቆርጡባቸው ሲደግፏቸውና ሲያጽናኗቸው ነበር። ነገሩ ከአቅም በላይ ሲሆን ነው ከመስሪያ ቤት እንዲለቁ የተደረጉት። ያም ሆኖ የመስሪያ ቤቱ ባልደረቦችና ጓደኞቻቸው እስከመጨረሻው አግዘዋቸዋል። ያሳደጋቸው ድርጅትም እንደደገፋቸው ነግረውናል። ኑሮን ግን ቀላል አልሆነላቸውም ነበር።

የዕለት ጉርሳቸውን ከአንዳንድ ጓደኞቻቸው በሚያገኙት ገንዘብ ቢሞሉትም የሚከፈላቸው ደመወዝ በመቋረጡ የቤት ኪራይ ግን መክፈል አልቻሉም። ይህም ሆኖ ወዲያው እጅ አልሰጡም ነበር። ከማንም እጅ ገንዘብ ተቀብለው ላለመኖር በብዙ መንገድ ኑሯቸውን ለመደጎም ተፋልመዋል። የተማሩበት ሙያ በብዙዎች ዘንድ ያስከበራቸው ነውና እርሱን ላለማዋረድም ጥረዋል። ነገር ግን እስከመጨረሻው አላዘለቃቸውም። እናም ከማሳደጊያ ውጪ የነበሩ እህትና ወንድም እንዲሁም እንጀራ እናት ነበሩና መቀላቀል ባይፈልጉትም ይህንን ማድረግ ውዴታቸው ሳይሆን ግዴታቸው እንደሆነ አመኑ። በቀጥታም ወደ እነርሱ ቤት አቀኑ።

የቤተሰባቸው መኖሪያ ፈረንሳይ አካባቢ ሲሆን፤ ከእነርሱ ጋርም ቢሆን ብዙ አልቆዩም። ባለባቸው ጭንቀት ምክንያት መስማማት አልቻሉም። የሚሏቸውንም አይሰሟቸውም። በእያንዳንዱ ጉዳይ በንግግር የሚግባቡ አልሆኑም። ስለዚህም ከጭቅጭቃቸውና አለመግባባታቸው የተነሳ ጎዳና ቤቴ ብለው ወደ ጎዳና ወጡ። ማየት የማይገባቸውን ስቃይም አሳለፉ። እርቧቸው የሚያድሩባቸው ቀናት ብዙ ነበሩ። የውርጬና የፀሐዩ ነገር'ማ አይወራም። ከሁሉም በላይ ደግሞ የተወለዱበት አካባቢ ላይና የሚያውቋቸው ሰዎች መካከል ሆነው የቀን ሥራ መስራት አንገት ያስደፋ ነበር። ከእነርሱ እጅ ለምኖ መመገብም እንዲሁ። ግን ዛሬን ለማለፍና ነገን ለማየት ይህ ያስፈልጋልና አድርገውታል።

ኢንጅነር ብርሃኑ በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ስለነበሩ ሁሉም የፈረንሳይ አካባቢ ነዋሪ ይረዳቸው ነበር። እናም «የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግ ሕዝብ ነውና ሁልጊዜም ይኑርልኝ» ይላሉ። ሕዝቡ ባይደግፋቸው ኖሮ የዛሬ የመቄዶንያ ኑሮም እንደማይታሰብ ይናገራሉ። ጎዳና ወጥተው ለ10 ዓመታት ቆይተዋል። በዚህም የዕለት ጉርሳቸውን የሚሞሉት በቀን ሥራ ነበር። መስራት በሚችሉት ዕድሜ ላይ እያሉ ሙያቸውን ሳይሆን ጥበቃ፣ የጉልበት ሠራተኛ መሆናቸው ሁሌም የሚቆጩበት ነገር ነው። ኀዘን ባያበዙና ስሜታቸውን ቀደም ብለው ተቆጣጥረውት ቢሆን ኖሮ የት እንደሚደርሱ ያውቁታል።

ስሜታቸውን ለመቋቋም ሀብታቸውን ጨረሱ፣ ችሎታ እንደሌለውም ሆኑ። ብስጭታቸው እየጨመረ በመምጣቱም በጎዳና ላይ የተለያዩ መከራዎችን አሳለፉ። ይህ ደግሞ ከሰውነት ጎዳና አወጣቸው፤ ዝቅም አደረጋቸው። «አትችልም» ጭምር አስባላቸው። ይሁን እንጂ «ሳይደግስ አይጣላ» እንዲሉ በጓደኛቸው ጥቆማ መሠረት መቄዶንያን ተቀላቀሉ። መጀመሪያ የአዕምሮ ህክምና ተደርጎላቸውም ከማዕከሉ ሳይወጡ በጥበቃ ክሊኒኩ ውስጥ እንዲያገለግሉ ሆኑ። ቀጥለውም ወደሌላ ክፍል ተዛወሩ። ይህም በዚያው በመቄዶንያ ውስጥ የፋይናንስ ክፍል ጥበቃ የሆኑበት ነው። በመሆን ማገልገል ጀመሩ። አሁን ደግሞ የአጭር የጽሑፍ መልዕክት (SMS) ተቀባይ ናቸው። አገግመው በሥራ ላይ ከተሰማሩ አምስት ዓመታት ተቆጥረዋል።

«ሕይወት ሸክላ ናት፤ ቶሎ የምትሰበርበት ብዙ ምክንያት አላት። ከተሰበረች ደግሞ መመለሻዋ ቀላል አይሆንም። ዳግም ለማገገም ወይም ለመጠገን ብዙ ዋጋ ታስከፍለናለች። ስለዚህም ዋስትናውን ቀድመን ማስቀመጥ ያስፈልገናል። ውድቀታችን የእኛ ብቻ እንደማይሆንም ማመን አለብን። የቤተሰብ ከዚያም አልፎ አርአያ የሆናቸው ሰዎች ሁሉ ይሆናል። እናም በእውነት ነገሮችን መቀበልና ለችግሮቹ እልባት በጊዜው ማግኘት አማራጭ ሳይሆን ግዴታ ሊሆን ይገባል» የሚሉት ባለታሪካችን፤ «ችግር የገጠመው ሰው በተለይም ከኀዘን ጋር ተያይዞ ጭንቀቱን የሚያበዛ ሰው ሊወስደው የሚገባው የመጀመሪያ እርምጃ ቶሎ መጽናናት ነው። ሆኖም ራሱን የሚያውቀው ራሱ ነውና ለመኖርና ሌሎችን ለመጥቀም ካሰበ መጀመሪያ ራሱን ማከም ያስፈልገዋል። አለበለዚያ ግን የማይወጣው አዘቅት ውስጥ ይገባል» ሲሉ ይመክራሉ።

«ሕይወት በተመረጠላት መንገድ የምትጓዝ ናት። ጠማማውን ከመረጥነው የተጣመመ ጉዞ ውስጥ ትከተናለች። የተቃናውን መስመር ከያዝን ግን ታንገዳግደን ይሆናል እንጂ መቼም አትጥለንም። ብዙዎች ከዚህ አንጻርም ተሳክቶላቸዋል ወይም ወድቀዋል። በተለይ በሕይወት ላይ ተስፋ መቁረጥ ስኬታማ የሆነውን እንኳን ሊያሳጣን እንደሚችል ከእኔ ሕይወት መማር ይቻላል» ይላሉም።

ኢንጅነር ብርሃኑ፤ የኀዘን ማብዛት አዕምሯዬን ከንቱ አድርጎ ከመሐንዲስነት የቀን ሠራተኛ እንዲሁም ጥበቃ አድርጎኝ ነበር። በሙያዬ ብቻ ሳይሆን በኑሮዬም የማስተምረውን ሰው እንዳላፈራ አድርጎኛል። እናም ሰዎችም ይህ በሕይወታቸው እንዳይሆን ቀድመው ስለራሳቸው ማሰብ አለባቸው፤ ቋሚ መሆናቸውን መጀመሪያ ሊቀበሉት ይገባል። በዚያው ልክ ተከታይ እንደሆኑም አስበው በቆዩበት ጊዜ ውስጥ የማይጠፋውን አሻራቸውን ማኖር ይኖርባቸዋል። ለዚህ ደግሞ ከሁሉም የራቀ የሚያደርገውን ኀዘንን ርግፍ አድርገው መተውም ይጠበቅባቸዋል መልዕክታቸው ነው።

እውነታዎችን ለመለወጥ የማያስችሉን ነገሮች «ቢሆን ኖሮ»ን ዳግም መኖራችንና «ምን ይከሰት ነበር?» ከሚለው ተስፋ አለመውጣታችን እንደሆነ የሚያነሱት ኢንጅነሩ፤ ጸጸት የኀዘን ዳርቻ የለውም። ምክንያቱም ሁልጊዜ አሰላሳይ ያደርጋል። የወደፊቱን ለመመልከት እና ዕቅዶችን ማውጣት አያስችለንም። ምንም ነገር አያስደስተንም ወይም አያነሳሳንምም። በዚህም ሥራችን የዕለት ጉርሳችንን መሙላት ብቻ ነው። እናም ሁለት ነገሮችን አይቶ ውሳኔ መስጠትን ካልለመድን አወዳደቃችን የከፋ ይሆናል ይላሉ።

የመጀመሪያው «ራሳችንን መውቀሳችን ምን ሰጠን» የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ «ከዚያ በኋላ ምን መጣ» የሚለው ነው። ባደረግነውና ባላደረግነው መካከል ያለውን ልዩነት ማጤን ተገቢነት አለው። ያን ጊዜ መልሱን እናገኘዋለን። ብዙ ጊዜም ዋጋ የከፈልንለት ከወደቅን በኋላ የምናየው መሆኑን እኔ ምስክር ነኝ። ዛሬ ላይ የቀደመውን ባስበው ምንም ላመጣ አልችልም። ትናንት ግን አስቤው ቢሆን ኖሮ እዚህ ቦታ ላይ አልገኝም ነበር። ስለሆነም ትናንት በትናንት መሠራት አለበት እንጂ ትናንት በዛሬ መኖር የለበትምና ይህንን አስባችሁ በሕይወታችሁ ተንቀሳቀሱም ሲሉ ይመክራሉ።

# ስፖርት

## በውሃ ዋና ሻምፒዮና አማራ ክልል አጠቃላይ አሸናፊ ሆነ

**ቦጋለ አበበ**

ካለፈው ቅዳሜ ጀምሮ በቢሾፍቱ ከተማ መኮንኖች ክበብ የመዋኛ ገንዳ ሲካሄድ የቆየው የ2014 ዓ.ም የኢትዮጵያ ውሃ ዋና ሻምፒዮና ትናንት ተጠናቋል። በዚህም አማራ ክልል በሁለቱም ጾታ አጠቃላይ አሸናፊ በመሆን የውድድሩ ልዩ የዋንጫ ተሸላሚ ሆኗል።

በውድድሩ ከተሳተፉ ጥቂት ክልሎች አንዱ በመሆን በርካታ ልዑካንና ተወዳዳሪዎችን ይዞ የቀረበው አማራ ክልል በበርካታ ፉክክሮች በግልና በቡድን የሰበሰባቸው ሜዳሊያዎች አጠቃላይ አሸናፊ አድርገውታል። ክልሉ ቀዳሚ ሆኖ ለማጠናቀቅ የቻለው አስራ ስምንት የወርቅ፣አስራ አንድ የብርና ሁለት የነሐስ ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ ነው።

አማራ ክልልን ተከትሎ ኦሮሚያ ፖሊስና ቢሾፍቱ ከተማ ሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃን ይዘው እንዳጠናቀቁ የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ካወጣው የነጥብ አሰጣጥ ደረጃ ለመረዳት ተችሏል።

አማራ ክልል አጠቃላይ አሸናፊ ሆኖ እንዲያጠናቅቅ የተለያዩ ተወዳዳሪዎቹ በግልና በቡድን የሰበሰቡት በርካታ የወርቅ ሜዳሊያ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በተለይም በተለያዩ ርቀቶች በግሉ አስር የወርቅ ሜዳሊያዎችን የሰበሰበው አትሌት ጥላሁን አያል በቅብብል ውድድርም ሶስት የወርቅ ሜዳሊያዎችን ከቡድን አጋሮቹ ማሳካቱ ተጠቃሽ ነው። ለዚህም አስደናቂ ብቃቱ የውድድሩ ኮኮብ ሆኖ እንዲመረጥ አስችሎታል።

በተመሳሳይ በውድድሩ ተካፋይ ከሆኑ ጥቂት ክለቦች አንዱ የሆነው ዳዊት ሕንጻ ተቋራጭ አትሌት የሆነችው ብርሃን ደመቀ በርካታ ውድድሮች ላይ በመሳተፍና አስደናቂ ብቃት አሳይታ ያስመዘገበቻቸው ውጤቶች የውድድሩ ኮኮብ በመሆን ልዩ ተሸላሚ እንድትሆን አድርጓታል።



**በሻምፒዮናው ተሰጥኦ ያላቸው ወጣቶች ጠንካራ ተፎካካሪ መሆን ችለዋል፣**

የአማራ ክልል አጠቃላይ አሸናፊ እንዲሆን ያስቻሉት አሰልጣኝ ማንደፍሮ ተገኝ ከልዩ ተሸላሚዎቹ አንዱ ሆነዋል። የኦሮሚያ ፖሊስ ደግሞ የጸባይ ዋንጫውን አሸናፊ ሆኗል።

ውድድሩ ትናንት ሲጠናቀቅ በተለያዩ ርቀቶች የፍጻሜ ውድድሮች ተከናውነዋል። በተለይም ኢትዮጵያ ኦሊምፒክን ጨምሮ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ውድድሮች በብዛት የምትሳተፍበት የሃምሳ ሜትር ነጻ ቀዘፋ ውድድር በብዙዎች ዘንድ የሚጠበቅ ነው።

ቀደም ባሉት ውድድሮች በርካታ ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ አስደናቂ ብቃት ማሳየት የቻሉ ዋናተኞች በዚህ ተጠባቂ ውድድር ድል ሳይቀናቸው ቀርቷል። እንደ ጥላሁንና ብርሃን የመሳሰሉ ኮከብ ተብለው የተመረጡ ዋናተኞች በሃምሳ ሜትር ነጻ ቀዘፋ ያሸንፋሉ ተብሎ ቢጠበቅም አልተሳካላቸውም። በወንዶች ኢትዮጵያን በተለያዩ ዓለም አቀፍ ውድድሮች በመወከል ብዙ ልምድ ያካበተው አቻላ ያኮቤ አሸናፊ ሆኗል። በተመሳሳይ በሴቶች በቶኪዮ 2020 ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን የወከለችው ራሄል ፍሰሐ አሸናፊ መሆን ችላለች።

ሻምፒዮናው በዋና ስፖርት ተወዳዳሪዎች መካከል የልምድ ልውውጥ የተደረገበትና ለ2022 አህጉራዊና ዓለም አቀፍዊ ሻምፒዮናዎች ኢትዮጵያን በመወከል የሚወዳደሩ ምርጥ ስፖርተኞች የተገኙበት መሆኑን የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰረት ደምሱ በተለይ ለአዲስ ዘመን በስልክ በሰጡት ቃለመጠይቅ ገልጸዋል።

በውድድሩ የአማራ፣ የጋምቤላ እና የሲዳማ ክልሎች ተሳታፊ ሲሆኑ የድሬዳዋ ከተማ እና የቢሾፍቱ ከተማ ተወዳዳሪዎችም በተለያዩ ፉክክሮች ተሳታፊ ናቸው።በክለብ ደረጃ ዳዊት እምሩ የሕንፃ ተቋራጭ፣ ሳምሶን ውሃ ዋና ስፖርት ክለብ እና ኦሮሚያ ፖሊስ የተሳተፉ ሲሆን፣ አቻላ ያኮቤ በግል ተወዳዳሪ በመሆን አቅርቧል።

"ስፖርት ለሰላም ለሕብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል የተካሄደው የ2014 ዓ.ም የክልሎች እና የክለቦች የውሃ ዋና ሻምፒዮና እስከ ትናንት ድረስ በተለያየ የውድድር አይነቶች የተካሄደው ይህ ሻምፒዮና፣ በርካታ ፉክክሮች የተስተናገደበትና አሸናፊዎቹ የተለዩበት ሆኗል።

ሻምፒዮናው በዋና ስፖርት ተወዳዳሪዎች መካከል የልምድ ልውውጥ የተደረገበት ፣ ለ2022 አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሻምፒዮና በመወከል ምርጥ ስፖርተኞች የሚመረጡበት እንደሚሆን ታውቋል።


## Re-Invitation for Bids (IFB)

**Date:** 11 April 2022
**IFB Title: -** Procurement of Mobile Veterinary Clinic, Vehicles and Motorcycles,
**Project Name: -** Regional Fund for Strengthening Drought Resilience Program in East Africa-Ethiopia Project (RF/SDR/KfW),
**Grant Number:** BMZ ID 2011 67 006
**Procurement Reference Number:** MoA/KfW-SDR/G/ICB-08/2021
**Procurement Method: -** International Competitive Bidding (ICB)

1. Ministry of Agriculture has received financing from KfW/German Government Development Bank, towards the cost of the project - Regional Fund to strengthen drought resilience (RF-SDR). It is intended that part of the proceeds of this finance will be applied to eligible payments under the contract for the Procurement of Goods and Related Services.
2. Bidding will be conducted by means of the International Competitive Bidding procedure with qualification as specified in KfW's Procurement Guidelines ("KfW Guidelines"); and is open to all bidders from Eligible Source Countries.
3. Ministry of Agriculture now invites sealed bids from eligible bidders for the supply and delivery of the following items

| Lot No. | Description | Measurement | Quantity | Bid Security in ETB |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Mobile Vet Clinic | No. | 2 | 100,000 |
| 2 | Station Wagon Hard Top, LWB, 4WD, | No. | 2 | 80,000 |
| 3 | Motorcycles | No. | 8 | 20,000 |

4. Interested eligible bidders may obtain further information and inspect the bidding documents at the address given below in the morning from 8:30 AM to 12:00 PM and in the afternoon from 01:30PM to 5:00 PM Monday to Friday.
5. A complete set of Bidding Documents in English language may be purchased by interested bidders upon payment of a non-refundable fee of ETB 200.00 (Two Hundred Birr) or an equivalent amount in foreign currency.
6. Bids must be delivered to the address below on or before 27 May 2022 GC at 10:00 AM EAT and will be opened in the presence of the bidders' representatives who choose to attend at 10:15AM EAT on the same date of closing.
7. Electronic bidding will not be permitted and late bids will be rejected.
8. All bids must be accompanied by a Bid Security with an amount stated above in Ethiopian birr or an equivalent amount in foreign currency.
9. The Purchaser reserves the right to reject the bid fully or partially.

**Ministry of Agriculture (MoA)**
**Drought Resilience and Sustainable Livelihoods Program (DRSLP)**
**Procurement Directorate, CMC Road, Behind Ethiopia Geological Survey**
**Block-B 2nd floor Room No. 201, Tel. +251-116-677753/118-332348,**
**Addis Ababa, Ethiopia**



## ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

የወ/ሮ ስኂን ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ለ2014ዓ.ም ለትምህርትና ስልጠና ለማምረቻ ዩኒት እንዲሁም ለቢሮዎች አገልግሎት የሚውል 1. የህንፃ መሳሪያና የቧንቧ እቃዎች 2. የአውቶ እቃዎች 3. የጽዳት እቃዎች 4. ለቴክስታይልና ጋርመንት የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች 5. የኤሌክትሪክ እቃዎች 6. ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች 7. የጽህፈት መሳሪያዎች 8. የሰራተኞች የደንብ ልብስና ጫማ 9. ለከተማ ግብርና ስልጠና ዘርፍ አገልግሎት የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል።

ስለዚህ ከዚህ በታች መስፈርቱን የምታሟሉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ብር 50.00 በመግዛት መወዳደር ትችላላችሁ።

1. በዘመኑ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው እና በንግድ ዘርፉ የተሰማሩ፣
2. የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣
3. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/TIN/ ያላቸው፣
4. የግዥው መጠን ብር 200,000.00 /ከሁለት መቶ ሺህ ብር/ እና በላይ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ VAT/ ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
5. ተጫራቾች በጨረታ ለመሳተፍ ከላይ በተ.ቁ 1- 4 የተጠቀሱትንና የሚመለከታቸውን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው።
6. የሚገዙትን የእቃዎችን ዓይነትና ዝርዝር መግለጫ/ስፔስፊኬሽን /ከጨረታ ሰነዱ ማግኘት ይቻላል ፣
7. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 50.00 /ሀምሳ ብር/ በመክፈል ከወ/ሮ ስኂን ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ቢሮ ቁጥር 204 /አዲሱ ህንፃ / ማግኘት ይቻላል።
8. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ለሚወዳደሩበት የእቃውን ጠቅላላ ዋጋ 1% በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትእዛዝ /ሲ.ፒ.ኦ/ ወይም በጥሬ ገንዘብ የከፈሉበትን ማስረጃ መያዝ አለባቸው።
9. ተጫራቾች የጨረታ መክፈቻ ዕለት ኦርጅናል ንግድ ፈቃድና ቫት ሰርተፊኬት የግብር መክፈያ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/TIN/ ሲጠየቁ ማሳየት አለባቸው። ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ሞልተው በታሸገ ኤንቨሎፕ ኦርጅናልና ኮፒ በማድረግ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15ኛው ተከታታይ ቀን 11፡30 ሰዓት ድረስ በወ/ሮ ስኂን ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ቢሮ ቁጥር 204/አዲሱ ህንፃ /በመገኘት የጨረታ ሰነዱን መግዛት የሚችሉ ሲሆን በቀጣዩ ቀን በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን እስከ 4፡00 ሰዓት የጨረታ ሰነዱን በተዘጋጀው ሳጥን ማስገባት ይችላሉ። ሳጥኑም በዚህ ሰዓት ይታሸጋል በዚሁ ቀን በ4፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል። እለቱ የስራ ቀን ካልሆነ ጨረታው የሚዘጋውና የሚከፈተው በሚቀጥለው የስራ ቀን ይሆናል።
10. ኮሌጁ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
11. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ስለ ጨረታው ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ ቢሮ ቁጥር 204 ድረስ በአካል በመገኘት ወይም በስልክ ቁጥር 033-111-10-10 በመደወል ማግኘት ይችላሉ፣

**የወ/ሮስኂን ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ግ/ፋ/ን/አስ/ደ/የስራ ሂደት**

ደሴ